ማስታወሻ፤

ያስተውሉ! ይህ ጽሁፍ የቀረበው ምርጫ-97 ከመካሄዱ ከሁለት ዓመታት በፊት **እ.ኢ.አ. ሰኔ 15 ቀን 1995 ዓ.ም. (በጎርጎሳዊያን አቆ. June 22, 2003)** ነው። በወቅቱ ጽሁፉ ባገር-ቤት በ"ኢትኦጵ" መጽሄት፤ በዳያስፖራው ደግሞ በ"ሐዋርያ" ጋዜጣ በ1995/2003 ዓ.ም. በተከታታይ ተዝግቧል።

ይህ ጽሁፍ መልሶ ማንበብ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም፣ ይህ ከምርጫ-97 ቀደም ብሎ የቀረበው ጽሁፍ፣ አሁን እየሆኑ ካሉት ነገሮች በተጨማሪ፣ በወቅቱ ተስፋ ተጥሎበት የነበረው የህብረት ("ኢዴኃህ") ምስረታ መጨናገፍና በምርጫው ማግስት የተከሰተው የተቃዋሚው ጎራ መፈረካከስ ሰበቡ ምን እንድሆነ በብዙ መልኩ ፍንትው አድርጎ ስለሚያሳይ ነው። ከዚህ በተጭማሪ ጽሁፉ በሩቅና በቅርብ ጊዚያቶች የተፈጸሙ ሌሎች ክስተቶችን አስመልክቶ ለመዳሰስ ይጠቅማል። ለአብነት ያህል በጽሁፉ ከተጠቀሱ "ከተተነበዩ" ጉዳዮች አንዳንዶቹን መጥቀስ ይቻላል፡-

- ከምረጫ-97 በኋላ ወያኔ ጦሩን ወደ ሶማሊያ ማስገባቱን፤
- በአርበኞች ግንባር (እጀግ የዘገየና ውጤታማነቱ አጠራጣሪ ቢሆንም) ጸረ-የትግራይ ህዝብ የሆኑት የግንባሩ አመራር ግለ-ሰቦች ተወግደው እንከን በሌላቸው ሰዎች መተካታቸው፤
- የኤርትራና የትግራይ ህዝብ ለማጋጨት አበክሮ ሲሰራ የቆየውና፣ ወያኔና ሻዕቢያ በእውር ፍቅር ተለክፈው በነበሩበት ወቅት፣ ወያኔ የኤርትራ አየር-ኃይል አብራሪዎችን እንዲያሰለጥን የላከው፣ በግጭቱ ማግስት የዓይደርን ህጻናት በቦምብ በመፍጀት ለወያኔ ጠቃሚ ነዳጅ ያቀበለው ኮሎኔል በቅርቡ በቁጥጥር ስር መዋሉ፤
- አሁን ተጋኖ እየተነገረለት ያለው ጉዳይ - ማለትም ወያኔ ሻዕቢያን ለማስወገድ የመቁረጡን ጉዳይ - አዲስ ክስተት ያለመሆኑን፣ ጉዳዩ የወያኔ ቋሚ ፖሊሲ/አጀንዳ መኖሩና አሁንም መሆኑ፣ ምርጫ-97 ወያኔን አፈር ላይ አንከባሎት ስለቆየ አቧራውን የማራገፍና ቤት የማጽዳቱ ዘመቻ አስኪጠናቀቅ አጀንዳው በይደር ተይዞ መቆየቱን፣ ባለፈው ምርጫ-2002 ውጤት የቤት ማጽዳቱ የቤት-ስራ በሚያስገርም ሆኔታ በመጠናቀቁ በይደር ተይዞ የቆየው የኤርትራ አጀንዳ አሁን ተራውን ጠብቆ መምጣቱን፤ ወዘተ. . .።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ በምርጫ-97 ማግስት ያሰራጨሁት (ያንዳንዶቹን ጸጉር ያስነጨ) ዳጎስ ያለ መጣጥፌ አገር እንዳይተራመስና ቅንጅቶችም እንዳይወድሙ ፓርላማ ገብተው (የአዲስ-አበባን አስተዳደር ጥቅልል አርገው ተቆጣጥረው ማለት ነው) ለቀጣዩ ምርጫ ይህን-ይህን ስሩ የሚል ወንድማዊና ወገናዊ ምክር ያዘለ ነበር። ሆኖም ከነሱ በቀር ነገሮችን ለመገመገም ብቃት ያለው ሰው የማይመስላቸው የዋሆቹ የቅንጅት "የሰላም" ታጋዮች፣ "አልጋ ቢሏት አመድ..." እንዲሉ የፓርላማን ወንበር ተጠይፈው በቃሊቲ ወህኒ ሲሚንቶ ላይ መንከባለልን መረጡ። ችግራችን የመደማመጥ ባህል ስላልታደልን የተጻፈንና የተነገረውን ነገር በጥሞና አጣጥሞ ማገናዘብ አቃተን እንጂ፣ በምርጫ-97 ማግስት ያቀረብኩት መጣጥፍ ይህ አሁን በድጋሚ እያቀረብኩት ባለው ጽሁፍና ሌሎችም በህብረቱ (ኢዴኃህ) ምስረታ ዋዜማ በተከታታይ በጻፍኳቸው ጽሁፎች ላይ በሰነዘርኳቸው ሃሳቦች ላይ የተመሰረተ ነበር። ስለዚህ፣ በምርጫ-97 ማግስት የቀረበው መጣጥፌ ለማጣጣም የ1995 ዓ.ም. መጣጥፌ ካሁን በፊት ያላነበቡትም ሆነ ያላነብቡት ቢጎበኙት ጠቃሚ ነው። [ለህብረቱ (ኢዴኃህ) ምስረታ መሳካት በዚህ ጽሁፍም ሆነ ይህንን ጽሁፍ ተከትለው በወጡ የተለያዩ ስራዎቼ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፤ ይሁን እንጂ፣ በወቅቱ እኔ የአመራር አባል የሆንኩለት "የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህዴን)" በህብረቱ ምስረታ ላይ ለመሳተፍ በጽሁፍ ጠይቆ የተከለከለበት ምክንያት፣ ይህ እኩይ ድርጊትም ተመሰረተ የተባለው ህብረት/ኢዴኃህ የውሃ ሽታ ሆኖ እንዲቀር በአንጻሩ ደግሞ ቅንጅት ጎልቶ እንዲውጣ ማድረጉን ለወደፊቱ በስፋት የምመለስብት መሆኑን እዚች ላይ ጠቁሜ ማለፍ እወዳለሁ]

ይህን ካልኩ በኋላ፣ በዋናነት አሁን የ1995 ጽሁፌ እንዳለ እንደገና እንዳሰራጨው የፈለግሁበት ምክንያት፣ ከቅርብ ቀናት በፊት ጠ/ሚ. መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ወቅታዊ ሆኔታ - በተለይ ኤርትራን በማስመልከት - እና ባሁኑ ወቅት በአፍሪካና በመካከለኛ ምስራቅ አካባቢ የተነሳውን የፖለቲካ ማዕበል አስመልክቶ የሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫና ይህንን ተከትሎ በብዙ ወገኖች ስለዚሁ መግለጫ - በተለይ የኤርትራውን ጉዳይ በሚመለከት - እየተደረገ ያለው ውይይት ነው። እኔም በዚህ ውይይት የበኩሌን ሃሳብ ለመሰንዘር አንድ ጽሁፍ በማዘጋጀት ላይ እገኛለሁ። በዚህ ውይይት ለመሳተፍ በማዘጋጀው ስራ ካለፉት ስራዎቼ አንዳንድ ነገሮች ለመጥቀስ ፈልጌ ሰራዎቼን ተመልሸ ስመለከት እ.ኢ.አ. ሰኔ 15 ቀን 1995 ዓ.ም. (በጎርጎሳዊያን አቆ. June 22, 2003) ያቀረብኩት ጽሁፍ በቁንጽል የሚቀርቡ ጥቅሶች ያዘለ ብቻ ሳይሆን ይዘቱ እንዳለ መልሶ ማሰራጨቱ አስፈላጊ መሆኑን ተረዳሁ።

"የኤርትራ መንግሥት እናስወግደዋለን" ለሚለው የመለስ መግለጫ ከተቃዋሚው ጎራ ወገኖች በኩል እየተሰጠ ያለው ትርጉም አንድ ዓይነት ነው። ይኸውም፣ "መለስ ባሁኑ ወቅት ይህንን መግለጫ ለመስጠት የተገደደው በአፍሪካና በመካከለኛ ምስራቅ አካባቢ የተነሳውን የፖለቲካ ማዕበል አስደንግጦት የህዝባችንን ቀልብ አቅጣጫ ለማስለወጥ ነው" የሚል ነው። ይህ አባባል እንዳለ ውድቅ የሚደረግ ባይሆንም፣ የመለሱ መግለጫ ግን ከዚሁ የገዘፈና የረቀቀ ይዘትና ትርጉም ያለው ነው። ይህ ግዙፍና ረቂቅ ትርጉም አሁን እያዘጋጀሁት ባለው ጽሁፌ አማካኝነት በዝርዝር የሚቀርብ ይሆናል።

በዚህ አጋጣሚ ለማመልከት የምፈልገው፣ ተቃዋሚዎች ከአቶ መለስ ጋዜጣዊ መግለጫው ተነስተው እየሰጡት ያለው ድምዳሜ ጠ/ሚሩ ለአገር ወስጥ ሚዲያዎች ባማርኛ ቋንቋ ለውጭ ሚዲያዎች ደግሞ በእንግሊዝኛ ከተነፈሰው በመነሳት ነው። ይህ መንደርደሪያ ችግር የሌለበት ቢሆንም የጉዳዩ ሙሉ ስዕል ግን አይሰጥም። ስለዚህ፣ እኔ በቅርቡ የማቀርበው ጽሁፍ ጠ/ሚ. መለስ - በብዙ ኤርትራውያን እጅግ ተቀባይነትና ተደማጭነት ላለው - ለ"አሰና" ሬዲዮና ድረ-ገጽ ዋና አዘጋጅ ለሆነው ለአቶ አማኑኤል ኢያሱ (ከሁለት ሰዓታት በላይ ወሰዶ) የሰጠውን ሰፊ ቃለ-መጠይቅ መሠረት በማድረግ ይሆናል።

መልካም ንባብ!

አብርሃም ያየህ

መጋቢት 16 ቀን 2003 ዓ.ም. (March 25, 2011)

---

# በኢትዮጵያና በኤርትራ ህዝብ መካከል ሌላ ጦርነት መቀስቀሱ አይቀሬ ነው!

## ይህ እንዳይሆን ምን መደረግ አለበት

## ግልጽ የመፍትሄ ሓሳብ

**ከአብርሃም ያየህ**

**ሰኔ 15 ቀን 1995 ዓ.ም. (June 22, 2003 )**

## መ ግ ቢ ያ

**ይህ የመፍትሄ ሓሳብ የኔ የግሌ ሃሳብ ሲሆን፣ በይዘቱ ማንኛውም ሌላ ሰው ወይም ድርጅት ተጠያቂ ሊሆን አይችልም። በተለይ፣ እኔ የማዕከላይ ኮሚቴ መስራች አባልና የውጭ ጉዳይ ሃላፊ የሆንኩለት «የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህዴን)» ድርጅታዊ ሃሳብ ወይም አቋም እንዳልሆነም ሊታወቅ ይገባል።**

**ይህ የመፍትሄ ሃሳብ በግሌ የማቀርብበበት ብዙ ምክንያቶች አሉኝ። ዋናው ምክንያት ግን፣ ምንም እንኳ፣ በተለየ ምክንያት ለጊዜው ያንድ በብሄር የተደራጀ ድርጅት ያመራር አባል ብሆንም፣ ካሁን በፊት በኢትዮጵያ የትግል መድረክ በግሌ ከተጫወትኩት ሚና አኳያ ከህዝብ ጋር ካለኝ ሰፊ ትውውቅ አንፃር፣ ባሁኑ ወቅት ባጠቃላይ የኢትዮጵያን ህዝብ የሚጎዳ አደጋ ሊደርስ መሆኑን እያወቅሁ ይህንኑ ለህዝብ ይፋ ለማድረግ ምንም ዓይነት የድርጅት ሊቸንሳ/ፈቃድ የማያስፈልገኝ በመሆኑ ነው።**

**ካለኝ የህይወትና የፖለቲካ ተሞክሮ በመነሳት፣ በኢትዮጵያው ወገንም ይሁን በኤርትራው ወገን ያሉ ኃይሎችና ግለሰቦች ይህንን የኔን የመፈትሄ ሓሳብ የማይጥማቸው ወይም በበጎ ዓይን የማይመለከቱት ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል የሚል ግምት አለኝ። ሆኖም ግን፣ ይህንን እኔን ፈጽሞ የሚያሳስበኝ አይደለም። ምክንያቱም፣ በሁሉም ነገሮች ሁላችንም አንድ ዓይነት አመለካከት ሊኖረን አይችልም፤ አንድ ዓይነት አመለካከት እንዲኖረን ማስገድድም አይገባም። እንደ አንድ ተቆርቋሪ ዜጋ፣ ጠቀመም አልጠቀመ፣ ተወደደም ተጠላ፣ በዜግነቴ ስለ አገሬ ጉዳይ ሓሳብ ከማቅረብና ምክር ከመለገስ መቆጠብ ግን አልችልም።**

ለማሌሊት/ወያኔ መሪዎች ምክር መለገስ ድሮም አላስፈለገንም፤ ዛሬም አያስፈልገንም። ድሮ ያልተፈለገው፣ እነ መለስ ሆን ብለው አቅደው የተነሱለት አገርን የመሸጥና የኢትዮጵያን ህዝብ የመበተን ዓላማ እነደነበራቸው ስለምናውቅ ነበር። እሱን አታድርጉ ብሎ ለነመለስ ምክር መለገስ ብዙ ሰዎችን ያስፈጀ ስለሆነም፣ ለማይሆንልን ነገር «ማን ይሞታል» በማለት እርግፍ አርገን የተውነው ጉዳይ ነው። ዛሬ ደግሞ በነሱ የጦርነት ባቡር ተሳፍረን አብረናቸው ወደ ገሃነም ለመውረድ ካልፈለግን በቀር፣ የነዚህ ሰዎች መካሪና አስመካሪ ለመሆን እቅዱም ሃሳቡም ሊኖረን አይችልም። መክረን የምንለውጠው ነገር ያለም አይመስለንም። ለሌሎች ኢትዮጵያዊያንም ሆኑ ኤርትራዊያን ወገኖቻችን ግን አይገቡ ገብተን በተለያየ መንገድ ስንመክር ኖረናል። እስካሁን ድረስ በጥሞና ያዳመጠን ግን የለም።

ብዙ ኤርትራዊያኖች፣ እኔ የወያኔን አመራር ስለጠላሁና ስለተቃወምኩ ብቻ፣ አልሆነላቸውም እንጂ ገድለውኛል። ብዙ የትግራይ ሰዎች ወያኔን በተገኘው መድረክ በሰላማዊ መንገድ ስላጋለጥኩ መለስና ካድሬዎቹ ባወጡልኝ የፈረስ ስሞች ጠርተውኛል፤ አንዳንዶቹም፣ አልሆነላቸውም እንጂ፣ ይሙት በቃ ፈርደውብኝ ገድለውኛል። ይህ ሁሉ ግን የወያኔ አገዛዝ ፀንቶ የሰራበትና የደከመለት በመሆኑ ውጤቱ ሁላችንም ጎዳ እንጂ፣ ከውጤቱ ማንም ተጠቃሚ አልሆነም።

ባለፉት አስራ አራት ዓመታት በትክክል የተገነዘብኩት ሃቅ ቢኖር፣ «የተማርኩ የተመራመርኩ ኢትዮጵያዊ ነኝ» ባዩ ያሁኑ የኢትዮጵያ ትውልድ ከራሱ አልፎ ሌላ ጠላት እንደሌለውና፣ የኢትዮጵያ ህዝብም ከራሱ ምሁራንና ኤሊቶች በላይ ሌላ ችግር የሌለው መሆኑን ነው። ለዚህ ድምዳሜ ካደረሱኝ ብዙ ምክንያቶች አንዱ፣ ባሁኑ ወቅት ይህ ትውልድ የተከናነበው ውርደትና ኪሳራ ምንጩ «ከኛ በላይ የሚያውቅላችሁ የለም» የሚሉት ዘመነኞች በሚፈጥሩት ችግርና የወገናቸውን ጥልቅ ምክርና ማስጠንቀቂያ ለማዳመጥ ያልተዘጋጁ መሆናቸውን በሚገባ ስለምረዳ ነው።

በደርጉ ዘመን ከሰጠሁት ጠቃሚ ማስጠንቀቂያ ይልቅ እጅግ የሚቆጨኝ ቢኖር፣ የማሌሊትና የኤርትራ ግጭት በተከሰተ ማግስት፣ (ሚያዝያ 8 ቀን 1990 ዓ.ም.) «አስቸኳይ መግለጫ» በሚል ባቀረብኩት 14 ገጾች ባካተተ ጽሁፍ አማካኝነት ያስተላለፍኩት ወሳኝ ጥሪ በድጋሚ ያልተደመጠ መሆኑ ነው። በዚያው መግለጫየ ላይ፣ የግጭቱ ትክክለኛ መንስኤ ምን እንደሆነ ከዘረዘርኩ በኋላ፣ በማጠቃለያው ላይ ካቀረብኳቸው የጥሪ ነጥቦች መካከል ዋናዎቹ ምን እንደነበሩ ለማስታወስ ያህል እዚሁ ልጥቀሳቸው። የጥቅሱ መጀመሪያ፤

> «ከዚህ በላይ በቀላል አባባልና አቀራረብ በተለይም በጣም ወሳኝ የሆነው ሰፊው ኢትዮጵያዊ ወገናችን ሊረዳው በሚችለው መንገድ ያቀረብኩት ዝርዝር መቋጨት ያለበት ‹ምን መደረግ አለበት › በሚል ጥያቄና ይህንንም ጥያቄ ለመመለስ በሚረዱ ጥቆማዎች መሆን እንደሚገባው አይታበልም። በኔ በኩል ‹ምን መደረግ አለበት › የሚለውን ለመመለስ፣ ከብዙ በጥቂቱ የምለው ቢኖር፤
>
> «1. የሚደመጥ ሃሳብ ሲኖር በሚገባ ለማዳመጥ መቻል ይኖርብናል። ከብርጭቆ፣ ከጠርሙዝ፣ ከጫጫታ ርቀንና በስሜት ብቻ ሳንወጠር ሰከን ብለን መደማመጥ ያስፈልገናል።
>
> «2. ያለ ምንም መጠራጠርና ማመንታት በትግራይ ህዝብና በኢትዮጵያ ሰራዊት ጎን የቆምን መሆናችንን በተግባር ማረጋገጥ ይኖርብናል።
>
> «3. የአገሪቱና የህዝቧ ጉዳይ ይመለከተናል፣ ያንገበግበናል የሚሉ የተደራጁ ኃይሎች፣ ያልተደራጁ ዜጎችና ታዋቂ ግለሰቦች ሃብታቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ጊዚያቸውንና እውቀታቸውን አስተባብረው በሦስት ወራቶች ውስጥ ባንድ አማካኝ ስፍራ ተገናኝተው አገሪቷን ለማዳን የሚያስችል መላምት ለማፈላለግ በጥልቅ መምከር ይኖርባቸዋል።
>
> 4. ባለፈው ጊዜ «ደርግ ይቅደም» በሚል የኩርፊያ ፖለቲካ ከተፈጸመው ስህተት ተምረን አሁንም «ወያኔ ይቅደም» የምንልበት አመቺ ሆኔታ ያለመኖሩን በጥሞና ማመዛዘን መቻል ይጠበቅብናል።
>
> 5. የትግራይ ህዝብና የህወሓት ሰራዊትም ከውስጥ ሆነው ለሻዕቢያ የሚሠሩትን የውስጥ አርበኞች በጥንቃቄ እየመከተ፣ አሁን በኢትዮጵያ የሚታየውን የውዥንብር አየር ለማጽዳት አመቺ ሆኔታ ለመፍጠር ይቻል ዘንድ፣ ለውዥንብሩ መፈጠር ቀንደኛ መሃንዲስ የሆነውን መለስ ዜናዊን አውርዶ፣ ስውር ዓላማ የሌላቸውና ባሁኑ ጊዜ በትግራይ ህዝብና በሌሎች ኢትዮጵያዊያን ዘንድ አንፃራዊ ተቀባይነት እያገኙ ካሉት የህወሓት የአመራር አባላት ውስጥ፣ ይበጃሉ በሚባሉ ሰዎች በመተካት የውስጥ ቡርበራውን ለማስወገድ ያላሰለሰ ጥረት

ይጠበቅበታል። በደርጉ ዘመን ሰራዊቱ ተፍረክርኮ የተበተነው የኢትዮጵያ ህዝብ ሠራዊቱን ይመራ በነበረ አመራር ላይ በማምረሩና ድጋፉን ለተዋጊው ሰራዊት በመንፈጉ ነው። ዛሬም የኢትዮጵያ ህዝብ፣ መለስ በቤተ መንግሥት ተቀምጦ እያለ፣ በአራት ማዕዘን ለተከበበው የኢህአዲግ ሰራዊት ደጀን ለመሆን እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን መረዳት አያዳግትም። ህዝብ ያልደገፈው ሠራዊት ደጀኑ ያደመበትና ያደፈጠበት ሠራዊት ምንጊዜም ድል ያገኛል ማለት ደግሞ ፈፅሞ አይቻልም። ስለዚህ መለስ በፈቃደኝነት ወይም ተገዶ ገለል እንዲልና ህዝቡን ለማስተባበር የሚቻልበትን ሆኔታ ለማመቻቸት ይቻል ዘንድ ግፊት መደረግ ይኖርበታል።» የጥቅሱ መጨረሻ።

ያኔ በጥድፊያ አዘጋጅቼ በበተንኩት በዚሁ መግለጫየ ላይ ከጠቀስኳቸው የጥሪዎቼ ነጥቦች ውስጥ አንኳሩ ነጥብ «አቶ መለስ ወደ መቀሌ ይመለስ» የሚለው ነው። እዚህ ዝርዝሩን ማቅረብ ባያስፈልገኝም፣ በወቅቱ ይህንን ማድረግ ግን የሚቻል ነበር። በኋላ ራሳቸው የተበሉት የወያኔ መሪዎች «መለስ ወይም ሞት» ብለው ባይደርቁ ኖሮ፣ ህዝባችን፣ «በመለስ ለሚመራ ጦርነት ድጋፍ አልሰጥም» ብሎ ድጋፉን በመከልከል ብቻ ብዙ ቁምነገር በተሰራ ነበር። «ያለ ህዝብ ድጋፍ ጦርነቱን መምራት አይቻልም» በሚል ክርክር ሳቢያም፣ በመከላከያ ሰራዊቱና በህዝቡ መሃል ያሉ/የነበሩ በሳል የህዝብ ልጆችም፣ መለስን ማውረድ የግድ እንደሚል ተገንዝበው የራሳቸውን እርምጃ እንዲወስዱ ማድረግ የሚቻልበት ዘዴ ማቀናበርም ይቻል ነበር። ይሁን እንጂ፣ አወቅን ባዮች «ከባድመ መልስ ወደ መለስ» በሚል አደንቋሪ መፈክር ዙሪያ ተሰልፈው፣ እንጀራ በልተው ያልጠገቡ ምስኪን ዜጎቻችንና ሃብታችን ለማይረባ ነገር ሰውተን፣ ከባድመ መልስ ባድመን አስረክበን መለስንና ስብሓት ነጋን አትርፈናል። አእምሮ ላለው፣ በተለይም ለሚታገል ሰው፣ እጅግ የሚያበሳጭና የሚዘገንን ክስተት ነው።

አሁን የማቀርበው የመፍትሄ ሃሳብም እንደ ወትሮው በሰላማዊ መንገድ በብዕር፣ በቀለም፣ በማይክሮፎን ብቻ ነው። ስለሆነም በኤርትራውም ሆነ በኢትዮጵያው ወገን ማንንም ሊያሳስብ አይችልም። ይህንን ሃሳቤን በጠመንጃ ኃይል የማስፈጸም አቅሙም ፍላጎቱም ደግሞ የለኝም። ህዝብ የራሱን ጉዳይ በራሱ አውቆ እንዲወስን፣ የግሌን የመፍትሄ ሃሳብ ከተጨባጭ መረጃ በመነሳት ለህዝብ የማካፈሉ መብቴ ግን ማንም ኢዲሰጠኝ አልጠይቅም፤ ማንም እንዲነፍገኝም አልፈቅድም።

አገርና ህዝብ ከጥፋት ለማዳን ለሚደረግ ትግል የሁሉም ተሳትፎ ወሳኝ ቢሆንም፣ ከሁሉ በፊት ግን የተማረው ክፍል ሚና ቅድሚያ የሚሰጠው ነው። ይሁን እንጂ፣ በምሁሮቻችንና በፖለቲከኞቻችን ላይ ተስፋና እምነት ከማጣቴ የተነሳ፣ ካለው የጊዜ እጥረት አኳያ፣ ይህንን ሃሳቤን በህዝብ ዘንድ ፈጣን ግንዛቤ እንዲያገኝ ለማድረግ ሲባል፣ በጠባብ መድረክ ሊሰራበት የሚገባ ከቅርብ ቤተዘመድ የመነጨ ጠቃሚ የመረጃ ጭብጥ ሳይቀር በዚህ ዝግጅት ተካቶ ለሁሉም ይፋ እንዲሆን እንደተለመደው ከመንገዴ ውጭ ለመሄድ ተገድጃለሁ።

ዛሬ የነ መለስና የነ ስብሓት ነጋ ማንነት የሚጠራጠር ሰው ያለ አይመስለኝም። ኢትዮጵያና ህዝባችን በተከናነቡት ውርደት የማይስማማም አለ ብሎ መናገር አይቻልም። የጎደለው ነገር ቢኖር፣ ምን እናድርግ ብሎ የራሱን አማራጭ ሓሳብ የሚያቀርብ፣ ወይም ደግሞ ሌላው የሚያቀርበውን ሓሳብ በሰከነ መንፈስ አዳምጦ በመረዳት የቀረበው ሓሳብ እንዳለም ይሁን አስተካክሎ ለተግባራዊነቱ የሚረባረብ ሰው የሌለን መሆኑ ነው። የሰላማዊ ሰልፍ ጋጋታ፣ የስብሰባ ጫጫታ፣ የሬዲዮ ድንፋታና፣ የኢንተርኔት አሰልቺ ውትወታና ስድብ ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ከጥፋት ሊያድናቸው አይችልም። አገራችን ባሁኑ ጊዜ ያለችበት አስጊ ሆኔታ ደግሞ «መለስ አስፈላጊ ሰይጣን ነው» ብለን ለማመን ከምንገደድበት ደረጃ ላይ እንዳያደርሰን የሚያሰጋ ሲሆን፣ በከፍተኛ ፍጥነት እየተበላሹ በመምጣት ላይ ያሉ ሆኔታዎች ለመቆጣጠርም በቂ ጊዜ የለንም።

በተረፈችን ትንሽ ጊዜ ተጠቅመን፣ ከወቅቱ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች ተጨባጭና አስጊ የህልውና ሆኔታ በመነሳት፣ «የመፍትሄ ሃሳብ» ማቅረብ በእጅጉ ወሳኝ ነው። ከዚህ በመነሳት የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች አሁን ከፊታቸው ከተደቀነው አደጋ ተላቀው፣ ያለምንም ተጨማሪ ኪሳራ፣ ለዘለዓለም በሰላምና በብልጽግና ሊኖሩ ያስችላቸዋል ብየ በግሌ ያመንኩበትና ከብዙ ሁነኛ ዜጎች ጋር የመከርኩበት የመፍትሄ ሃሳብ፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ልጆች እንዲመክሩበት፣ በዚህ ዝግጅቴ አማካኝነት ቀርቧል።

ይህንን የመፍትሄ ሃሳብ ለማቅረብ አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት ለመገንዘብ ይረዳ ዘንድ፣ ለማስታወስ ያህል፣ በቅድሚያ አንኳር አንኳር በሆኑ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት ወቅታዊው ሆኔታ ምን እንደሚመስል ለማመላከት እወዳለሁ።

## የድንበር ውሳኔው ግኝት ሲገመገም

መለስ ዜናዊ በኤርትራ ጉዳይ ካለው ልዩ ተልእኮና አጀንዳ አንጻር፣ ካሁን በፊት ተካሄደ በተባለው ሬፈረንደም ከለገሰው አንፀባራቂ አገልግሎት ይልቅ፣ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ምንም ዓይነት ህጋዊ ተቀባይነት በሌላቸውና፣ ጣልያን ራሷ ውሉን ጥሳ ኢትዮጵያን በሙሉ ወራ የሰረዘቻቸውን የቅኝ ግዛት ስምምነቶች መሠረት ያደረገው የአልጀርሱ ስምምነት የወለደው የድንበር ውሳኔ፣ ለኤርትራ ይበልጥ ጠቃሚ አስተዋፅኦ አድርጓል ብሎ መናገር ይቻላል።

ሻዕቢያ፣ ትዕግስት በተመላበት ጥበብ፣ ዘ ሄግ ላይ በብቃት ተሟግቶ ተጨማሪ መሬት ብቻ ሳይሆን በራሱ ህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተኣማኒነትና ኩራት ተጎናፅፎ በሚገባ አትርፏል።

በአንፃሩ ደግሞ፣ መለስ ዜናዊ፣ እንደነ ስዩም መስፍን ያሉ አሽከሮች ተጠቅሞ፣ «ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት» በሚለው ቋሚ መርሆው ፀንቶ፣ እዚህ ግቡ የማይባሉ ተሟጋቾች አቁሞ ምንም ሳይሟገትና ሆን ብሎ በመሸነፍ ከሄግ ሲመለስ በኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን በብዙ ደጋፊዎቹና ካድሬዎቹ ሳይቀር ተተፍቷል። የመለስ መንግሥት ከሁሉም በላይ የጎዳውና፣ ካሁን ወዲያ በትግራይ ህዝብም ሆነ በሁሉም ኢትዮጵያዊያኖች ዘንድ ታማኝነት አሳጥቶ የሚያቅበዘብዘው ያለ አብይ ምክንያት፣ በተለይ ካንድ ዓመት በፊት አሸነፍኩ ብሎ በውሸት ቡራ ከረዩ ደጋፊዎቹን ማስፈንደቁ ነው። መለስ ከዚህ ከወረደበት መዓት ለመውጣት አሁንም መላምት ያጣል ብሎ መገመት ግን፣ ራስን ማታለል ብቻ ይሆናል። የመለስ መላምቶች ምን እንደሆኑ እመለስበታለሁ።

በድንበሩ ውሳኔ አሸናፊ የሆነው የኤርትራ መንግሥት፣ ምንም እንኳ ብይኑ ያጎናፀፈው ድል ከፍተኛ የፖለቲካ ጥቅምና በራሱ ህዝብ ተአማኒነት ያስገኘለት ቢሆንም፣ መለስና ስብሓት ነጋ ባሁኑ ጊዜ በህዝብ ቁጣ በተወጠሩበት ወቅት፣ ድንበሩ ተከልሎ ይሰጠዋል ማለት ግን የሚታሰብ አይደለም። እንዲያውም የድንበሩ ውሳኔ እንደዚህ ግልፅ ሆኖ መምጣቱ፣ የኤርትራ መንግሥት በነ መለስ/ስብሓት የተጠነጠነበት ከፍተኛ ሽብርና ትርምስ ባጭር ጊዜ ተግባራዊ እንዲሆን ፍጥነቱን በከፍተኛ ደረጃ ያስጨመረው መሆኑን ለመረዳት ችለናል።

በአንፃሩ፣ ምንም እንኳ መለስ ዜናዊ ኤርትራ ዓለምአቀፋዊ ድንበሯ በህግ ታውቆላት በመወሰኑ ካቶ ኢሳያስ በላይ የሚያስፈነድቀው ቢሆንም፣ ባጠቃላይ በኢትዮጵያ ህዝብ፣ በተለይ ደግሞ በትግራይ ህዝብና በደጋፊዎቹ ዘንድ ተተፍቶ፣ ካሁን በፊት ታይቶ በማይታወቅ ነውጥ እየተናጠ በመሆኑ፣ ነገር ዓለሙ ሁሉ መያዣ መጨበጫ ጠፍቶበታል። ስለሆነም ከዚህ አደጋ ራሱን ለማዳን ሲል ህወሓትን አፈራርሶ ከመበተን ባሻገር፣ የራሱ ህገመንግሥት መናድን ያካተተ ሌሎች ብዙ ክንዋኔዎችን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

ያለ ምንም ጥያቄ፣ ያቶ ኢሳያስና ያቶ መለስ መንግሥታት፣ በተለያየ መንገድና ምክንያት፣ ከፊታቸው ከፍተኛ አደጋ ተደቅኖባቸዋል። ስለሆነም ካሁን በኋላ የሁለቱም መንግሥታት ዋና አጀንዳ በተቻለ ፍጥነት አንዱ የሌላውን ተቃዋሚ በማጠናከር፣ ይህንን ሽፋን በመጠቀም፣ መለስ ባስመራ ያለውን መንግሥት፣ ሻዕቢያም ያዲስ አበባውን መንግሥት ከመለወጥ በቀር ሌላ መፍትሄ እንደሌላቸው የሚታውቅ ጉዳይ ህኗል። ስለዚህ፣ ሁለቱም መንግሥታት የየግላቸውን እቅድ ለማስፈፀም አጠቃላይ አቋማቸውና ዝግጅታቸው ምን እንደሚመስል ጠቅለል ባለ መልኩ እንመልከት።

## የኤርትራ መንግሥት በተመለከተ

የኤርትራ መንግሥት ካሁን በፊት ከራሱ ጋር ግኙኝነት ያላቸው የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ኃይሎች ተሰባስበው ህብረት እንዲፈጥሩ አንዳንድ ጥረቶች አድርጓል። ሆኖም፣ ይህንን ጠንካራ ጎኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ መከራው ብዙ ድክመቶች ነበሩት፤ አሁንም አሉት። ከኤርትራ መንግሥት ድክመቶች መካከል አንዱ ለህብረቱ መሳካት የሚፈጠረው መድረክ አስመራ ላይ ማድረግ ይችላል ብሎ ማሰቡ ነው።

በመሠረቱ፣ የኤርትራ መንግስት ተቀናቃኞች ይህ ቀረው የማይባል የማሌሊት አመራር ድጋፍና እንክብካቤ እየተደረገላቸው ያለ ምንም ችግር ባዲስ አበባ ከተማ በግልጽ ተሰብስበው ህብረት መመስረት ከቻሉ ዘንዳ፣ የማሌሊት ተቃዋሚዎች አስመራም ይሁን ምፅዋ ቢሰበሰቡ ሃጢአት አይደለም። ይሁን እንጂ፣ ይህንን ለማድረግ ያልተቻለው፣ የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ኃይሎች እርስ በርሳቸው በመናከስና በመካሰስ ላይ ተጠምደው ስለሚገኙ፣ ወደ አስመራ ደፍሮ ለመግባት እርስ በርሳቸው ስለሚፈራሩ ብቻ ነው።

ሌላው የሻዕቢያ ድክመት ደግሞ፣ በጣም ወሳኝ የሆነውን የጎንደር ህዝብ በትግሉ ላይ በሙሉ ልቡ እንዳይሳተፍ ኮሎኔል ታደሰ ሙሉነህ የተባለ በደርጉ ዘመን የኢትዮጵያ አየር ኃይል ፓይለት የነበረና፣ አሁን ደግሞ የኤርትራ አየር ኃይል አውሮፕላን አብራሪና አሰልጣኝ የሆነው ሰው «የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግምባር» (ኢህአግ) ሊቀመንበር ሆኖ ሳለ ምንም መስራት የማይቻልና ውጤቱም ዜሮ ብቻ ሳይሆን እጅግ አደገኛ መሆኑንም የሻዕቢያ ሹማምንቶች በቅጡ ያለመረዳታቸው ነው። ይህ ኮሎኔል ከግጭቱ በፊት ወደ አስመራ የተላከው በማሌሊት መሪዎች አማካኝነት ከመሆኑም በላይ፣ በተለይ May 10, 2003 ታትሞ በተሰራጨው Indian Ocean Newsletter የተባለ ጋዜጣ እንደዘገበውና ከሌሎች ምንጮች እንደምንሰማውም፣ ኮሎኔል ታደሰ ሙሉነህ የመቀሌው የዓይደር ትምህርት ቤት ህፃናት በናፓልም ያጋየ ነው የሚል ክስ እየቀረበበት ያለ ሰው ነው።[1] ከሁሉ የከፋ ነገር ቢኖር፣ በዚህ ኮሎኔል ሰበብ የጎንደርና የትግራይ ህዝብ እልክ ውስጥ ገብቶ የነ መለስ/ስብሓት መሳሪያ የሆነ እንደሆነ ነው።

ሌላ ሻዕቢያ ያላስተዋለው ጉዳይ ደግሞ፣ የተለያዩ አማሮች በድብቅ ወደ አስመራ መመላለሳቸውና በዚያ በኩል መደራጀታቸው ያደባባይ ምስጢር ሆኖ ሳለ፣ ይህንን ሃቅ ያማራው ብሄር ተወላጆች ሊደብቁት ስለሚከጅሉ፣ ይህ በራሱ በብዙ የትግራይ ተወላጆች ዘንድ ከፍተኛ ስጋትና ጥርጣሬ ያስከተለ መሆኑ ነው። ዛሬ ያማራ፣ የኦሮሞ፣ የሲዳማ፣ የኦጋዴን፣ የቤንሻንጉል፣ የጋምቤላ፣ ወዘተ. ህዝብ ልጆች ወደ አስመራ እንደሚመላለሱ በግልጽ የሚታወቅ ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ፣ በኢትዮጵያዊነቱ እምነት በታሪክ የራሱን ማንነት ያሳወቀን አብርሃም ያየህ «ለምን ወደ አስመራ ሄደ » በሚል ከማሌሊት አሽከሮች ጫጫታ ባልተለየ ሆኔታ የሚሰማው ያማሮች ጫጫታ ምክንያቱና ምንጩ፣ አብርሃም የትግራይ ህዝብ ልጅ ስለሆነ ብቻ ነው። ይህንን በተመለከተ አንድ አብነት ልጥቀስ።

የናሳው የጠፈር ምርምር እውቅ ሳይንቲስት ኢንጂነር ቅጣው እጅጉ «የኢትዮጵያ ብሄራዊ አንድነት ግምባር» የሚባል ድርጅት መስርተው የትጥቅ ትግል ማስጀምራቸው ገሃድ ሆኗል። በመሠረቱ፣ እንጂነር ቅጣው ካላቸው ታላቅ ሙያ አኳያ የተጎናፀፉትን ከፍተኛ ታዋቂነት ተጠቅመው ትክክለኛውና አማራጭ የሌለውን የትግል ስልት መምረጣቸው አስተዋይነታቸውን እንደሚያመለክት አጠያያቂ አይደለም። ከዚህም በላይ እኒህ እውቅ ኢትዮጵያዊ እጅግ ከፍተኛ የሆኑና ብዙ ጥቅም የሚያገኙባቸውን ስራዎቻቸውን እርግፍ አድርገው በመተው፣ አገራቸውንና ህዝባቸውን ከጥፋት ለመታደግ ሲሉ በትግል መሰማራታቸው፣ ለሌሎች ከዳር ቆመው ለሚተቹና እንደ ባእድ ሰው ያገራቸውንና የህዝባቸውን ጥፋት ተመልካች ለሆኑ ምሁራንና እውቅ ሰዎች ታላቅ አብነት በመሆናቸው ሊከበሩ፣ ሊመሰገኑና፣ ሊበራቱ ይገባል።

የኢንጂነር ቅጣው ትጋት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከያዝኩት ርእስ ጋር በተያያዘ፣ የኢንጀር ቅጣው ድርጅት ግን በትግራይ ተወላጆች ዘንድ ከፍተኛ ውይይት አስነስቷል። ለውይይቱ (ለውዝግቡ ማለት ይቻላል) መነሳት ሰበብ የሆነው፣ ኢንጂነር ቅጣው አውስትራሊያ በሚታተምና «ድንቅነሽ» በተባለ መፅሄት በቅርቡ የሰጡት ቃለመጠይቅ ነው።[2] ኢንጅነር ቅጣው በዚሁ ቃለመጠይቅ ስላነሷቸው ብዙ ቁምነገሮች ያለኝ አመለካከትና ልዩነት በተለየ መጣጥፍ በሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ። ላሁኑ ግን በተጠቀሰው ቃለመጠይቅ ላይ ለኢንጅነሩ ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከል ቁልፍ የሆነውና ለዚህ ከኤርትራ መንግሥት ጋር ግኑኝነት ላለው ነጥብ መነሻ የሆነውን አንድ ጥያቄና፣ ኢንጂነር ቅጣው ለጥያቄው በሰጡት መልስ ብቻ አተኩራለሁ። እጠቅሳለሁ፦

«ጥያቄ፤ ወያኔና ሻዕቢያ የከረረ ጠብ ውስጥ ከገቡ ጀምሮ አንዳቸው የሌላቸውን ተቃዋሚዎች እያሰባሰቡ ለመርዳትና ለማደራጀት ሲሞክሩ ቆይተዋል። በተለይም በኤርትራ በኩል አዳዲስ የወያኔ ተቃዋማዊዎችን የማዋለዱና የማደራጀቱ ስራ በስፋት ሲካሄድ ይታያል። የእናንተ ድርጅት ይህን በመሰለው ሂደት ውስጥ ከተፈጠሩት መሃል ይሆናል የሚል ጥርጣሬ ላላቸው ወገኖች ምን ዓይነት ምላሽ ይሰጧቸዋል ድርጅትዎስ ሻዕቢያን አስመልክቶ ያለው አቋም ምንድነው

ሳይንቲስት ቅጣው፤ በኛ በኩል – እኔም ሆንኩ ድርጅታችን – እስከ አሁን ከሻዕቢያ ጋር ያደረግነውም ግንኙነት ሆነ የተደረገልን እርዳታ የለም። ... በዚህ አጋጣሚ ለማስተላለፍ ወይም ለማስታውስ የምሻው ነጥብ ወያኔና ሻዕቢያ በፍቅርም ሆነ በጠብ የፈፀሟቸው ውሎችም ሆኑ ስምምነቶች፣ ወይም ያጫሯቸውም ሆኑ የሚያጭሯቸው ግጭቶች ሁለቱ ቡድኖች የጋራ ወይም የተናጠል የፖለቲካ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የፈጠሩት እንጂ ከሕዝቡ ጋር ምንም የሚያገናኘው ጉዳይ እንደሌለ ነው። ለምን ቢባል ሁለቱም ቡድኖች ሕገ–ወጥና በኃይል ሕዝቡ ጫንቃ ላይ የተፈናጠጡ በመሆናቸው የሕዝብ ውክልና የላቸውምና ነው። ሕዝብንና የፖለቲካ

ድርጅትን፣ የአገዛዝ ስርአትንና ሃገርን ለይተን ማየቱ ከብዙ ስህተቶች የሚጠብቀን ይመስለኛል።» የጥቅሱ መጨረሻ፤ ሰረዝ የኔ።

ኢንጅነር ቅጣው ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ የሰጡት መልስ ጠቃሚ መልእክት አለው። ይሁን እንጂ፣ «<u>እኔም ሆንኩ ድርጅታችን – እስከ አሁን ከሻዕቢያ ጋር ያደረግነውም ግንኙነት ሆነ የተደረገልን እርዳታ የለም።</u>» ያሉት የሚያስተዛዝብ ብቻ ሳይሆን ብዙ የትግራይ ተወላጆች በኢንጅነሩና በኤርትራ መንግሥት ላይ ጥርጣሬ እንዲያሳድሩ ምክንያት ሆኗል። እኔም ይህንኑ ችግር ለመቅረፍ ከኢንጂነር ቅጣው ጋር እንድንወያይበት በተደጋጋሚ ስልክ በመደወልና በኢሜይል አማካኝነት እንጂነር ቅጣውን ተማጥኘ ነበር። ሆኖም ምንም እንኳ፣ ኢንጂነር ቅጣው ከላይ በጠቀስኩት ቃለመጠይቅ ላይ «በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ካሉ የተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ምን ያህል ተቀራርቦ የመወያየትና የመደጋገፍ ጥረት አድርጋችኋል » በሚል ለቀረበላቸው ሌላ ጥያቄ ሲመልሱ፣ «አዎን አድርገናል። በአሁኑም ጊዜ ከልዩ ልዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ቀደም ብለን በጀመርነው መሠረት እየተወያየን ነው።» የሚል መልስ የሰጡ ቢሆንም፣ ከድርጅታችን ከትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህዴን) ጋር ግን ምንም ያደርጉት ውይይት እንደሌለና ለውውይት ተጋብዘውም በማናውቀው ምክንያት ፈቃደኛ ሆነው ያለመቅረባቸውን ለመገንዘብ ችለናል።

በመጀመሪያ ደረጃ ኢንጅነር ቅጣውም ሆኑ ድርጅታቸው ከኤርትራ መንግሥት ጋር በረጅም ጊዜ የዳበረ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ጠንቅቀን የምናውቅ መሆናችን ነው። እንዲያውም፣ ለምሳሌ ያህል፣ እኔ ወደ ኤርትራ ስመላለስ አንድም ቀን ፕሬዚዴንት ኢሳያስን በአካል አግኝቻው አላውቅም። አቶ ኢሳያስን አግኝቶ ማነጋገር ለኔ ከባድ ሆኖ ሳይሆን፣ እስካሁን ድረስ የአቶ ኢሳያስን የተጣበበ የስራ ጊዜ እንድሻማ የሚያስገድደኝ ሆኔታ ባለመፈጠሩ ነው። አሁን በቅርቡ አንዳንድ አስገዳጅ ሆኔታዎች ስላጋጠሙ ብቻ በግል አንድ ሰፊ ደብዳቤ ላቶ ኢሳያስ መጻፌ ግን ለወደፊቱም ቢሆን በታሪክ ሰነድነቱ ከኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ የምደብቀው ስላልሆነ እዚህም ብጠቅሰው እወዳለሁ። ኢንጅነር ቅጣው ግን ፕሬዚዳንት ኢሳያስን በአካል አግኝተው እንደሚያነጋግሩ በቂ መረጃ አለ። ኢንጅነር ቅጣው አስመራ ደርሸ አላውቅም የሚሉ ከሆነም የሚያስተዛዝብ ብቻ ሳይሆን፣ ከኛና ከትግራይ ህዝባችን ጀርባ የሚዶለት ነገር እንዳይኖር የሚያሰጋን ሆኖ ተገኝቷል።

እንግዴህ ይህንን የኢንጂነር ቅጣው ጉዳይ ከያዝነው ርእስ ጋር የሚያገናኘው የኤርትራ መንግሥት ከሚጠቀምባቸው ስልቶች አንፃርና፣ አንዳንድ የአማራ ብሄር ተወላጆች <u>በድብቅ</u> ከአስመራው መንግሥት ጋር የሚያደርጓቸው ግኑኝነት ራሱ የቻለ ሰበብ ያለው መሆኑን መጠቆም አስፈላጊ መሆኑን ለማመላከት ነው።

በደርግ ዘመን ማሌሊቶች ካባረሯቸው ከፍተኛ የቀድሞ የህወሓት ያመራር አባላት ጀምሮ ብዙ ሌሎች ሰዎችና ድርጅቶች ከደርግ መንግሥት ጋር በድብቅ ይገናኙ እንደነበሩ በትክክል አውቃለሁ። ሆኖም በድብቅ የሚደረግ ነገር ሁሌም ከግል አጀንዳና ጥቅማ ጥቅሞች ጋር የተያያዘ ስለሚሆን፣ የድብቅ ግኑኙነቶቹ ምንም የረባ ውጤት አላስገኙም ብቻ ሳይሆን፣ ተደብቀው ግንኙነት ባደረጉት ሰዎች ላይ የታሪክ ተጠያቂነትም እንደሚያስከትልባቸው ሳይታለም የተፈታ ሓቅ ነው። አሁንም በገሃድ ከኤርትራ መንግሥት ጋር ለመገናኘት ዳርዳር የሚሉ አንዳንድ ሰዎች የኤርትራ መንግሥት በአብርሃም ያየህ በኩል የገንዘብ ድጎማ እንዲያደርግላቸው ሲማጠኑ ቆይተዋል። አብርሃም ያየህ ግን ለራሱም ቢሆን ከኤርትራ መንግሥትም ይሁን ከሌላ ዘንድ የተደበቀ ቼክ ስለማይፈልግ፣ ለሌሎችም የተደበቀ ቼክ እየለመነ የሚያመጣበት ምንም ምክንያት የለውም።

ለአገራችንና ለህዝባችን መዳን ስንል የምንወስዳቸው እርምጃዎች ሁሉ፣ ተደብቀው ላይደበቁ፣ ከህዝባችን ዘንድ የምንደብቅበት ምንም ምክንያት ሊኖር አይችልም። ስለሆነም ከኤርትራ መንግሥት ጋር በስልትም ሆነ በስትራተጂያዊ ምክንያት የሚደረግ ማንኛውም ድብቅ ግኑኝነት ውጤቱ አስከፊና አፍራሽ እንደሆነና ለወያኔም ድንጋይ ማቀበል መሆኑን ሁሉም ወገኖች የተገነዘቡት አይመስልም። የዚህ ዓይነት አሰራር እያስከተለ ያለው አሉታዊ አስተዋፅኦ በቀላሉ የሚታለፍ አይደለም። እዚህ እንዲነሳ ያስፈለገውም ለዚህ ነው።

ዛሬ ባብዛኛው የትግራይ ተወላጆች ዘንድ የሚታየው አስፈሪ አመለካከት፣ «ሻዕቢያ በትግራይ ህዝብ ዘንድ በጎ አመለካከት የለውም። እንዲያውም የትግራይን ህዝብ ካላጠፋሁ ሰላም የለኝም የሚል አቋም አለው» የሚል አመለካከት ሆኖ ይገኛል። ይህ የሆነበት ያለምክንያት አይደለም።

የማሌሊትና የሻዕቢያ ግጭት በተከሰተ ማግስት በግልጽ እንደታዘብነው፣ ብዙ የኤርትራ ተወላጆች ግልብጥ ብለው፣ «እኛ ጠባችን ከትግሮቹ/ከዓጋሜዎቹ ጋር እንጂ ከአማራው ጋር አይደለም» በሚል በስፋት መንቀሳቀሳቸው ይታወቃል። በዚያን ጊዜ፣ ይህ ቅስቀሳ በኤርትራ መንግሥት አቋም የተወሰደበት ይሁን አይሁን ለይቶ ማመልከት አይቻልም። ከዚያ መንግሥት ጋር ባለን ግንኙነት መሠረት እንደተረዳነው ከሆነ፣ ቅስቀሳው በግለሰቦች/በቪድዮ-ነጋዴዎች ስሜት የተደረገ ነው ተብለናል። ይህንን መልእክት ያስተላለፍንላቸው የትግራይ ተወላጆች የሰጡት የመከራከርያ ሃሳብ፣ «ጉዳዩ ይህ ከሆነ፣ የኤርትራ መንግሥት የነጋዴዎቹን አፍራሽ አድራጎት ሊኮንነው በተገባ ነበር» የሚል ነው።

ሆኔታዎች እንዲህ እየተግተለተሉ ባሉበት ሆኔታ፣ ያማሮች በድብቅ ወደ ኤርትራ መመላለስ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አማሮቹ አጠገባቸው ካሉት የትግራይ ድርጅት ጋር እንኳ ለመስራት ያለመፈለጋቸው፣ አጠያያቂ ከመሆኑም በላይ፣ «አብርሃም ያየህ ለምን ወደ አስመራ ሄደ የሚለው ጫጫታ፣ በትግራይ ሰዎች ዘንድ ሻዕቢያ ተአማኒነት እንዳይኖረው በቂ ሰበብ ሆኗል። ከዚህ የተነሳ ይህ በራሱ አንድ ከፍተኛ የሻዕቢያ ችግር ሆኖ ይገኛል።

የኤርትራው መንግሥት ስልት ከወያኔ መሪዎች ስልት ጋር ሲነፃፀር የሚታየው ሌላው ጉድለት፣ እነ መለስ ከሱዳንና ከየመን ጋር በመመሳጠር በሚልዮኖች የሚቆጠር ብር በማፍሰስ የኤርትራ ተቃዋሚዎች አብረውና ተባብረው እንዲሰሩ እያደርጉ ሳለ፣ የኤርትራው መንግሥት ግን ነጋ ጠባ ወደ አስመራ እየዘለሉ በድብቅ የሚጎርፉትን ኢትዮጵያዊያኖች (በተለይ ድብቆቹ ያማራ ብሄር ተወላጆች ናቸው) በድርጅት ላይ ድርጅት እየከመሩ፣ ከነባሮቹና ከሰከኑት ታጋዮች ይልቅ እኛ እንበልጣለን በማለት እንዲያቅራሩ እንዲቀጥሉ በር መክፈቱ ነው። ይህንን ጉድለት ባስቸኳይ እልባት አግኝቶ፣ የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ኃይሎች ባስቸኳይ ግምባር ፈጥረው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ከወያኔ የተሻለ አማራጭ ሆነው ካልቀረቡ፣ የኢትዮጵያ ህዝብና የኤርትራ ህዝብ ለተጨማሪ እልቂት፣ ለአዲስ አደጋ የሚጋለጡ መሆናቸው አይቀሬ ነው።

የኤርትራ መንግሥት በኢትዮጵያ ህዝብ፣ በተለይም በአማራው ህዝብ፣ አሁን ደግሞ ከአማራው በበለጠ በትግራይ ህዝብ ዘንድ፣ ከዚያ ባሻገር ደግሞ ህልውናችን ከአማራውና ከትግራይ ህዝብ ጋር የተሳሳረ ነው በሚሉ አናሳ ብሄረሰቦች፣ በኢትዮጵያ አፋሮችና፣ በመሳሰሉት ህዝቦች ላይ በጥርጣሬ ዓይን የሚታይ ብቻ ሳይሆን እጅግ የተጠላ መንግሥት ነው። ይህንን ጥላቻ አንዳንዶቹ በተሳሳተ አመለካከት ከኤርትራው መንግስት አልፈው ወደ ሰላማዊው የኤርትራ ህዝብም ያወርዱታል።

የጥላቻው መጠን በብዙ መንገዶች የሚለካ ቢሆንም፣ በጣም የሚያስገርመው ግን፣ ካሁን በፊት ጠላቶቻችን የሆኑት የማሌሊት መሪዎች በአረሜናዊ መንገድ ኤርትራዊያን ወገኖቻችንን (ለዚያውም አብዛኞዎቹ ወገናዊነታቸው ለኢትዮጵያ የሆነ) ንብረታቸው እየተዘረፈ፣ ሰብእናቸው እየተገፈፈ ለዘመናት ካደራጁት ህይወታቸው በመፈናቀል ሲባረሩና ሲዋከቡ፣ ከጥቂቶቻችን መጯጯህ በቀር ሁሉም ዝምታ መምረጡ ነው። ከድርጅቶች መሃል፣ የወያኔ መሪዎች እኩይ ተግባር በሩቅና በቅርቡ የሚያስከትለውን ጣጣ በትክክል አውቆ፣ ቢያንስ ድርጊቱን የኮነነ (እኔ እስከማውቀው ድረስ) ነባሩና አዛውንቱ ድርጅት ኢህአፓ ብቻ ነው። ኢህአፓ፣ በረጅሙ በኢትዮጵያና በኤርትራ ህዝቦች ግኑኝነት ላይ ጠንቅ የሚያስከትለውን የማሌሊቶች እኩይ ተግባር በመኮነኑ ለኢትዮጵያ የሰጠው አገልግሎት በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ሆኖም፣ ለይስሙላ «የኤርትራ ህዝብ ህዝባችን ነው» እያሉ በሚመፃደቁት፣ እንደ ሓቁ ግን «በኤርትራ ምድር ሰዉ ብቻ ሳይሆን ሳር ቅጠሉ ሁሉ ነዶ ባሕሩ ብቻ ይቅርልን» የሚሉ የአጋንንት ልጆች፣ ውሸት ቢያልቅባቸው፣ «ኢህአፓ ባስመራ ጽሕፈት ቤት ከፍቷል» ብለው በማቅራራት በዚያ ሰሞን መድረኩን ሁሉ ሲያጣብቡ ተስተውለዋል።

ይህ በዚህ እንዳለ፣ እኛ ከማንም በላይ ከሻዕቢያ ጋር ይህ ቀረው የማይባል ጠብ የነበረን ዜጎች ብንሆንም፣ ለኤርትራ ህዝብ ያለንን ተቆርቋሪነት በዚያ በቀውጢው ጊዜ በተባበሩት መንግሥታት መድረክ ላይ በይፋ አቋማችንን የገለጽነው የቅርቡን ሳይሆን የሩቁን ያገራችን ጥቅሞች ከግምት በማስገባት ነው። በድብቅብቆሽ ሳይሆን በግልፅ ወደ ኤርትራ በመጓዝ በችግሩ ጊዜ በኤርትራ ህዝብ መሃል ተገኝተን «ጦርነት ፋይዳ የለውምና ሌላ መላምት እናፈላልግ» ብለን በግላጭ ለመውጣት የተገደድነውም በዚህ አቋማችን ምክንያት ከሻዕቢያ ጋር በተደርጉ ግኑኝነቶች አማካኝነት፣ ሻዕቢያ ኢትዮጵያና ኤርትራ በፌደሬሽን እንዲተሳሰሩ ፈልጎ ሃሳብ ማቅረቡንና፣ እነ አቶ መለስ ግን ይህንን እንደማይፈልጉ ያረጋጡላቸው መሆኑን ከራሱ ከኤርትራ መንግሥት ከፍተኛ የልኡካን ቡድን መርዶ ስለተነገረን ነው። እኔም በተለየ በዚያ እሳት መሃል ዘው ብየ ወደ ኤርትራ እንድገባ ያስገደደኝ ይህ ግንዛቤ ብቻ እንደነበር ካሁን በፊት የጻፍኩትን መመልከት ይቻላል።[3] ስለዚህ ከሻዕቢያ ጋር ምንም ዓይነት ግኑኝነት ያለማድረግ የማንም ሰው መብት ሆኖ፣

ግኑኝነት ከተደረገ ግን በድብቅ ሳይሆን ህዝባችን በሚያውቀው በይፋና በህብረት ቢሆን ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል በዚህ አጋጣሚ ለማስታወስ እንወዳለን።

ሌላ የሻዕቢያ ጣጣ ኦነግና የኦጋዴኒያው ድርጅት ኦብነግ የመሳሰሉ የብሄር ድርጅቶች ከኤርትራ ጋር መሥራታቸው፣ በተለይ በአማራውና በትግራይ ህዝቦች፣ ባጠቃላይ ደግሞ በሌሎች ኢትዮጵያዊያኖችም ዘንድ «ኢትዮጵያን ለመበታተን የተዶለተ ነው» በሚል ከፍተኛ የሆነ ስጋት መኖሩ ነው።

ብዙዎች እንደሚያስቡት ኦነግም ሆነ ኦብነግ በመሰረቱ ቄልጥ ብለው የመገንጠልን ዓላማ ለማራመድ የተነሱ ድርጅቶች አይደሉም። በርግጥ በነዚህ ድርጅቶች ፕሮግራም ውስጥ አሁን በስራ ላይ ያለውን የወያኔ ህገመንግሥት የሚፈቅደውንና ይህ ህገመንግሥት ሳይጻፍ ለኤርትራ የተቸረውን «የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል» የሚለው መርሆ ተካቷል። ይህ ደግሞ በኦነግና በኦብነግ ፕሮግራሞች ብቻ ሳይሆን፣ «በአንድነት ኃይሎች» ዘንድ ተቀባይነት ያለው «የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግምባር፣ አአዴግ/አርዱፍ» ፕሮግራም ቄምር ግልጽ ሆኖ የሰፈረ መርሆ ነው። ኦነግና ኦብነግም ሆኑ ሌሎች ኃይሎች ወያኔ በሚያስረዳድራት ኢትዮጵያ ህገመንግሥታዊ መብታቸው የሆነውን ተጠቅመው፣ ማሌሊት ለራሱ ሰጥቶ ለነሱ የከለከላቸውን መብት ለማረጋገጥ ይህንን መርሆ በፕሮግራማቸው ውስጥ ማካተታቸው ምንም ሓጢአት አይደለም። ዋናው ቁምነገር ግን እነዚህ ኃይሎች የሚታገሉላቸው ህዝቦች ምርጫቸው ምንድነው የሚለው ብቻ ይሆናል። ይህንን ደግሞ ከሚመለከታቸውና ከሌላው ህዝብ በላይ በተለየ ሆኔታ ተጨቁነዋል ከሚባሉት ህዝቦች በቀር ማንም ሊያውቅ አይችልም።

የማንም ህዝብ ምርጫ ማወቅ የሚቻለው፣ ባገራችን ፍፁም ነው የሚባል ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ ስርዓት ተመስርቶ የህዝባችን ፍላጎት ምን እንደሆነ ያለምንም ተፅእኖ ህዝቡ ራሱ ሲነግረን ብቻ ነው። እኛም በህዝቡ እስከተማመንና ህዝቡ የራሱን ጉዳይ በራሱ እንዳይወስን ለማድረግ እንደማይቻለን እስከተገነዘብን ድረስ፣ ብዙ የሚያስጨንቀን ጉዳይ ያለ አይመስለንም። ይህ ማለት ግን በራሱ በቂ ክንዋኔ አይደለም። ለዲሞክራሲና ለህዝባዊ ስርዓት መንገስ እየታገልን፣ አባቶቻችን በነሱ ዘመን በነበረው ስርዓትና እምነት ምክንያት በሌሎች ወገኖቻችንን ላይ የፈጸሟቸው ስህተቶችና በደሎች ምንም ሳንደናቆር በይፋ መኮነን ይኖርብናል። እኛ ደባብቀነውና ሸፋፍነው ልናልፈው የምንወደውን የህዝብ ቁስል፣ የዚያ የቆሰለው ህዝብ ልጆች በራሱ በህዝቡ ቋንቋ እየተጠቀሙ ዘመኑ ባፈራው የመገናኛ ቴክኖሎጂ አማካኝነት ነጋ ጠባ እየተሰራጨ ባለበት፣ በአንፃሩ ደግሞ ህዝቡ የሚያውቀውን ምስጢር እንደብቃለን የምንል ከሆነ፣ ህዝቡ እኛን አምኖ የገዛ ልጆቹን ተፍቶ ከኛ ጋር በሰላምና ባንድነት ተሳስሮ ይኖራል ብሎ መገመት ራስን ማታለል ይሆናል። ይህን በተመለከተ ካሁን በፊት «የኤርትራ ፋይል ሲከፈት» በሚል ርእስ እያጠናቀቅሁት ባለው የጽሑፍ ስራየ ላይ ራሱን የቻለ ምዕራፍ ተሰጥቶት ስለሚወጣ ለዚህ ዝግጅት መነሻ ወደሆነን ጉዳይ እንመለስ።

የኤርትራ መንግሥት ከተበታተነች ኢትዮጵያ ምንም ጥቅም እንደሌለው ራሱ በተለያዩ ጊዚያቶች ለኛ ሲገልጸው የቆየ ጉዳይ ነው። በኢትዮጵያ ያለው የብሄር/ብሄረሰቦች ችግር በዴሞክራሲያዊ መንገድ መፍታት እንደሚቻልና ተገንጥሎ መኖር እንኳንና ገና ለሚገነጠሉ ቀርቶ ለኤርትራ ህዝብም እንዳልጠቀመ ዛሬ የኤርትራ መንግሥት ባለስልጣናትን ጨምሮ ብዙ የኤርትራ ዜጎች የሚያወሱት ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያዊያኖች ከኤርትራው መንግሥት ጋር እንዳይነካኩ ጠላታቸውን የወያኔ አመራርን ስለሚፈሩና እርስ በርሳቸውም ስለሚፈራሩ የኢትዮጵያ ህልውናን አስመልክቶ ከአስመራ በኩል የሚመጣ አደጋ መኖር አለመኖሩን ለመገንዘብ፣ አደጋው ካለም በምን መንገድ ከዚህ አደጋ ራስን መከላከል ይቻላል ብለው ተግተው ሲሰሩ አይታዩም። እንዲያው በደፈናው ብቻ በጭለማ ሲደናበሩ፣ ምንም የተሻለ አማራጭ፣ ስልትና ዝግጅት ሳይኖራቸው፣ ያንን አጥብቀው የሚፈሩት የኢትዮጵያ የመበታተን አደጋ አፍንጫቸው ሊነካ ትንሽ ቀርቶታል።

ኢትዮጵያ የምትበታተነው ሻዕቢያ ስለፈለገው ወይም የብሄር ድርጅቶች የመገንጠል ፕሮግራም ስላላቸው አይደለም። እስካሁን ድረስ ካለን ግንዛቤ አኳያ፣ ባሁኑ ጊዜ ሻዕቢያ በድብቅ ኢትዮጵያን የመበተታተን ፍላጎት አለው ብለን ለማጠቃለል እጅግ ይከብደናል። ሆኖም ሻዕቢያ ቢፈልገውም እንኳ፣ ከነ መለስ ዜናዊ ጋር ተሻርኮ ካልሆነ በስተቀር ይህንን ብቻየን አደርጋለሁ ብሎ ቢነሳ ኢትዮጵያ ከመፍረሷ በፊት ሻዕቢያ ራሱ እንደሚፈርስ አጠያያቂ አይደለም። ማሌሊትና ሻዕቢያ ካሁን በኋላ ባንድ አልጋ ላይ ይተኛሉ ብሎ የሚያስብ ሰው ካለ ግን፣ በትግርኛ፣ «በእባብ የተነከሰ ሰው በልጥ ሲደነብር ይኖራል» እንደሚባለው፣ ከግጭቱ በፊት የታየውና በግጭቱ ሳቢያ የተንኮታኮተው የሻዕቢያና የማሌሊት ያልተባረከ ግኑኝነት ያስደነበረው ሰው ብቻ መሆን አለበት። ኢትዮጵያ በማያጠያይቅ መንገድ የምትበታተነው በሻዕቢያ ኃይል ሳይሆን፣ ወደ ከርሰ መቃብር በመውረድ ላይ ያለው ወያኔ፣ ሁሉም ነገር ሲያልቅበት፣ በየግምጃ

ቤቱ ያለውን ጠመንጃ ለሁሉም እኩል አከፋፍሎ የሸሸ ለት እንደሆነ ልብ ያለው ልብ ሊለው የሚገባ አሳሳቢና ወቅታዊ ጉዳይ ነው።

የኤርትራ መንግሥት ኢትዮጵያን የመበታተን ዓላማ ያለው ወይም የሌለው መሆኑን የመገለጫው ሰዓት ደርሷል። መለስና ስብሓት ባስመራ ላይ የራሳቸውን መንግሥት በመሰየም አሁን ዓይኑን አፍጦ ከመጣባቸው ህዝባዊ ቁጣ ለጊዜውም ቢሆን ለመግታት ወደ ኤርትራ መመረሹ አይቀሬ መሆኑን ሻዕቢያ በሚገባ አውቆ፣ የራሱ የሆነውን የኤርትራን ህዝብ ወደሌላ መከራ እንዳገባ ለማድረግ የሚፈልግ ከሆነ፣ ምንም ጊዜ ሳያጠፋ ከርሱ ጋር ግኑኝነት ያላቸውን የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ኃይሎች በቅርቡ በሚካሄደው የኢትዮጵያ «የተቃዋሚ ድርጅቶች ጉባኤ» መገኘታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል። ይህን በተመለከተ አሳማኝ መረጃዎችና ትንተናዎች በማከል ለኤርትራው መንግሥትና ለሚመለከታቸው የተቃዋሚ ኃይሎች መልእክታችን በጽሑፍ ያስተላለፍን መሆናችንን ለራሳችን ህዝብም ሆነ ለኤርትራ ህዝብ በዚህ አጋጣሚ ልናስታውቅ እንወዳለን።

ለማጠቃለል ያህል፣ የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ድርጅቶችና ደጋፊዎቻቸው በኤርትራው መንግሥት ላይ ካላቸው እምነት ይልቅ፣ የኤርትራ ተቃዋሚዎችና ደጋፊዎቻቸው በመለስ መንግሥት ላይ ያላቸው እምነት እጅግ ከፍተኛ መሆኑን የኤርትራው መንግሥት አምኖ በመቀበል ሚዛኑን ካላስተካከለ በቀር፣ ካለፈው ጊዜ በበለጠ የሁለቱም አገሮች ህዝቦች ከማያውቁት አዘቅት ውስጥ እንደሚዘፈቁ ሳይታለም የተፈታ መሆኑን ገልጸን እናልፋለን።

## የማሌሊት መንግሥት በተመለከተ

ዛሬ የነ መለስ ዜናዊና የነ ስብሓት ነጋ ህልውና በምን ዓይነት አስከፊ ሆኔታ ላይ እንዳለ ለማስረዳት ብዙ መታከት ያለብን አይመስለንም። ይህንን ለማድረግ ብንሞክርም እጅግ አሰልቺ ይሆናል። ምናልባት ትንሽ የምንለው ነገር ካለ፣ በኢትዮጵያው ወገንም ሆነ በኤርትራው ወገን፣ በተለይም ደግሞ በትግራዩ ወገን፣ ሁሉም እንደአቅሚቲ የነ መለስ ዜናዊ የማያወላዳ የደንቆሮ ጡጫ የቀመሰ ስለሆነ፣ ሁሉም ሰው በያለበት ቤት ዘግቶ ብስጭቱን እያኘከ በነ መለስ ዜናዊና በነ ስብሓት ነጋ ላይ በመዶለት ላይ ይገኛል፣ የሚል ነው።

በዓለም ከፍተኛ የፖለቲካና የውትድርና እውቅና ያገኙ አንድ የቻይና ጠቢብ የተናገሩትን ስናስታውስ የምናገኘው ትምህርት፣ እንዲህ የሚል ነው። እጠቅሳለሁ፦

> «ጠላትህ ሁሉም የማፈግፈጊያ በር/መስመር ተዘግቶበት ማምለጫ ያጣ ለት፣ ያለህን ኃይል በሙሉ ተጠቅመህ የተከበበውን ጠላትህ የሚያመልጥበትን ቀዳዳ ክፈትለት። ጠላትህ መውጪያ ቀዳዳ ካጣ ግን፣ ካንተ ባነሰ አቅም ቢሆንም እንኳ ጨክኖ በመታገል፣ ካንተ የበለጠ ኃይል አከማችቶ ሊወጣ ይችላል። ይህንን ለማድረግ ከቻለ፣ (ማለትም ጠላትህ ካንተ የበለጠ ኃይል ለመፍጠር ከቻለ)፣ የተፈጠርክበትን ቀን መርገም አለብህ። ጠላትህ ይህንን ለማድረግ ካልተቻለው ግን፣ ከሁሉ በፊት የሚወስደው እርምጃ አጥፍቶህ መጥፋትን ነው። ዛፎችን ያቃጥላል። ከብቶችን አርዶ ያቃጥላል። ድልድዮችን ይሰብራል፣ ህዝቡን እርስ በርሱ ያተራምሳል። ባጠቃላይ አንተ ባሸናፊነት ወጥተህ የምትጠቀምባቸውን ነገሮች በሙሉ አጥፍቶ ራሱንም ያጠፋል። ያንተ ድል ያለ ኪሳራ የሚረጋገጠው በጠላትህ ሽሽት መሆኑን ተረዳ።» የጥቅሱ መጨረሻ።

የማሌሊት ወራሪዎች ህልውና ከቁጥጥር ውጪ መሄዱ ለመረዳት ከተፈለገ፣ ከተጨባጭ መረጃዎችና ሰዎቹ በተጨባጭ ከሚያራምዷቸው ነገሮች በመነሳት ሲሆን ለበለጠ ግንዛቤና ጥንቃቄ እጅግ ጠቃሚ ነው። ስለሆነም ካገር ቤት ከህዝባችንና ከመከላከያው ሰራዊት አባላት የሚደርሱን የማያጠራጥሩ መረጃዎች በሙሉ የሚያመለክቱት ሰዎቹ ያበቃላቸው መሆኑን ነው። ይህ በራሱ ኢትዮጵያንና ህዝቧን ከጥፋት ያድናል ማለት ግን አይደለም። እንዲያውም፣ በተቃራኒው፣ መለስ ዜናዊ እኛን ለመቅጣት ሲል፣ ሰራዊቱን የሚበትንበትና ህዝባችን እርስ በርሱ አባልቶ ገለል የሚልበት ምቹ ሆኔታ መኖሩን በጥሞና ማስተዋል ያስፈልጋል። እዚህ ላይ አንድ ወሳኝ የሆነ ጉዳይ ለማንሳት እወዳለሁ።

የወያኔ/ማሌሊት ሰላዮችና ካድሬዎች ባሁኑ ወቅት በስፋት በመንቀሳቀስ ለትግራይ ተወላጆችና ለሌሎችም ውስጥ ውስጡን እያሰራጩት ያለው ወሬ «ወያኔ/ኢህአዴግ ስልጣን ከለቀቀ የትግራይ ህዝብ ይታረዳል፤ ኢትዮጵያም ትበታተናለች» የሚል እንደሆነ ያደባባይ ምስጢር ነው። ይህንን የሚሆንበት ምክንያት በሚል በወያኔ ሰላዮችና ካድሬዎች ከሚሰራጩ ማስፈራሪያዎች መካከል ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል፦

- ኢህአዴግ ቢወድቅ ሻዕቢያ በቅድሚያ በትግራይ ህዝብ ላይ ዘምቶ ይፈጀናል። ከዚያ በኋላ ደግሞ ኢትዮጵያን ይበትናል።

- ኦሮሞና አጋዴን ሌሎችም ህዝቦች ይገነጠላሉ ብቻ ሳይሆን በመጀመሪያ ትግሬን፣ ቀጥለው ደግሞ አማራውን ያርዱታል።

- ሶማሊያ አክራሪ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችን ወደ ኢትዮጵያ አሰርጋ በማስገባት በክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ህዝባችን ላይ ጀሃድ ያውጃል።

መልእክቱ በጣም ቀላል ነው። መልእክቱ የሚለው «በውድም በግድም እኛን ማቀፍ ይኖርባችኋል። ይህ ካልሆነ ግን አጥፍተናችሁ እንሄዳለን/እንሸሻለን» የሚል ነው። አእምሮው በትክክል ለሚያስብና ዓይኑን ከፍቶ ለሚያስተውል ሰው መልእክቱ አደገኛና ዘግናኝ ለመሆኑ ያለ ጥርጥር መናገር ይቻላል። ባለፉት አስራ ሁለት ዓመታት ረቂቅ በሆነ መንገድ ማሌሊት በኢትዮጵያ ምድር ያከናወነው ቢኖር፣ ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ደግሞ የትግራይ ህዝብ የዚህ ፍርሃትና ስጋት እስረኛ ሆኖ «ከወያኔ የባሰ እንዳይመጣ» በሚል ወያኔን ጫንቃው ላይ ተሸክሞ እንዲቀጥል የሚያደርግ ነው።

ይህንን ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ቅስቀሳ የሚካሄደው ስብሃት ነጋ በሚባለው የተንኮል ቋፍ ስር እየተመራ እንደሆነ በትክክል ይታወቃል። ስብሃት ነጋ ባገር ቤትና በውጭ አገሮች የሚኖሩና በስለላ ስራ እጅግ የተካኑ የዓድዋና የአክሱም ሰዎችን በወረንጦ ለቅሞ መልምሏል። በውጭ አገር የሚኖሩት እንደነ ብስራት አማረ ያሉትን አደገኛና በብዙ የኢትዮጵያ ህዝብ ሃብት የሚንቀሳቀሱትን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።[4] ይህ ጸሃፊ የስብሃት ነጋ የአክስት ልጅ እንደመሆኑ መጠን በማስተላለፍ ላይ ያለው መልእክት በበቂ መረጃ ብቻ ሳይሆን፣ ጸሃፊው ራሱም በስብሃት ወኪሎችና በቤተዘመድ አማካኝነት «ሰሞነኛው ድግስ» ቀርቦለት ለቀረበለት ጥሪ የሰጠው መልስ ስላለ ነው። ጥሪው ምን እንደሆነ ከታች እመለስበታለሁ።

ስብሓትና የስብሓት ምልምሎች ይህንን ወሬ አውርተው የሚያስወሩት ለህልውናቸው ሲሉ መሆኑን በሚገባ እንረዳለን። ይሁን እንጂ፣ እነሱ ለህልውናቸው ሲሉ ይህንኑ ማለታቸው መቀበል ባይቻልም፣ የነ ስብሓት ነጋ ዘመቻ ግን እንክን የለውም ማለት አይደለም። እነ ስብሓትና መለስ ዜናዊ እቅዳቸው ካልሰራ እንደገና በማናንሰራራበት ወይም ብዙ መስዋእትነት ሊያስከፍለን በሚችል መከራ ውስጥ እንድንዘፈቅ የሚያደርግ በቂ ዝግጅትና ብቃት እንዳላቸው ቅንጣት ታክል ጥርጣሬ ማድረግ እንደማያስፈልግ መረዳት የግድ ይላል።

እንደሚታወቀው፣ ባሁኑ ወቅት ማሌሊት ህዝብን ቀስቅሶ የሚያሳምንበት የራሱ ምላስ ተቆርጦ ተጥሏል። ስለሆነም ህዝብን የሚያስፈራራው በተለያየ ሽፋን የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች በስፋት በማሰማራትና ብዙ ገንዘብ በማፍሰስ ነው። ሰው ስለሸሸው፣ ዋናው የግኑኝነት መስመሩ በድርቅ ለተጎዱ እርዳታ እንሰብስብ የሚል አንዱ ፈሊጥ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የንግድ ፈቃድ መስጠት፣ የከተማ ቦታ ማደል፣ በትግራይ ደግሞ የሲቪክ ስብስቦች የሚመስሉ፣ ለምሳሌ የአጼ ዮሓንስ፣ የአግአዚ፣ የንግስተ ሳባ፣ ወዘተ. ትምህርት ቤቶች የቀድሞ ተማሪዎች ማህበራትን ማደራጀትን የመሳሰሉትን በመጠቀም ከሸሸው ህዝብ ጋር አዲስ የግኑኝነት መስመር በመዘርጋት አስጊ ናቸው የሚላቸውን ጉዳዮች ወደ ህዝብ ለማስረፅ ሲባክን ይታያል።

ባጭር አነጋገር፣ የማሌሊት አመራር ህልውናው ከባድ አደጋ ላይ የወደቀ መሆኑን በሚገባ ያረጋገጠ በመሆኑ፣ ባሁኑ ጊዜ ከመቼውም በበለጠ አደገኛና በታኝ ሆኖ ወጥቷል። ስለሆነም የማሌሊት አመራር ከዚህ የህልውና አደጋ ራሱን ለማዳን የቀረቺው አንዷት ምርጫ ብትኖር የፈለገውን ሰበብ ፈጥሮ ወደ ኤርትራ በመመረሽ የኤርትራውን መንግሥት ገርስሶ በምትኩ መለስ የሚያሽከረክረው አዲስ መንግሥት ማቆም ብቻ መሆኑ ግልጽ ሆኗል። ከዚህ የተነሳ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ዝግጅቶች ሁሉ በጥድፊያ በማከናወን ላይ ይገኛል።

## የመለስና የስብሓት ዝግጅቶች

የመለስና የስብሓት የወቅቱ ዋነኛ የፖለቲካ አጀንዳ «ሻዕቢያን ከስልጣን በማባረር በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ፌዴራላዊ ትስስር በመፍጠር የድንበሩ ጉዳይ በዚያ ትስስር ውስጥ ከስሞ ይቀራል» የሚል ሆኖ ይገኛል። ስለሆነም ይህንን ማድረግ የሚችለው በተለይ አሁን የድንበሩ ውሳኔ በኢትዮጵያ ኪሳራ በመጠናቀቁ ምክንያት፣ እየራቁት ያሉት ደጋፊዎቹንና ሌሎች የተበሳጩ ኢትዮጵያዊያንን በማለሳለስ ነው። ስነሆነም፣ የሻዕቢያና አደገኛነት በመተንተንና የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን በመለገስ የአጀንዳቸው ይዘት ከታማኝ ካድሬዎቻቸው በመጀመር

በተዋረድ ወደ ታች ወደ ህዝብ ለማስረፅ ብዙ ብር በማፍሰስ ጠንክረው በመስራት ላይ መሆናቸው እየተመለከትን ነው።

መለስና ስብሓት ነጋ ይህንን አስቸኳይ አጀንዳቸውን ለማስፈፀም ከሁሉ በፊት የወሰዱት ፈጣን እርምጃ፣ እነሱ የሚያንቀሳቅሷቸው የኤርትራ የተቃዋሚ ኃይሎች «ሃገራዊ ምሕዝነት ኤርትራ» (ሃምኤ) «Eritrean National Alliance» (ENA) በመባል የሚታወቀውን የህብረት ግምባር ፈጥረው በዚሁ ግምባር ጥላ ስር እንዲሰባሰቡ በማድረግ፣ ጦራቸውንም አንድ ወጥ አድርገው በሚገባ ማዘጋጀትን ነው።

በዚህ ክንዋኔ ጎልቶ የወጣ ጉዳይ ቢኖር፣ አዲስ አበባን መርገጡ ተሰምቶ የማይታወቀው አቶ ህሩይ ተድላ ባይሩ፣ ከመቅፅበት የግምባሩ መሪ ሆኖ መውጣቱ ነው። ለ«ሃምኤ/ ENA» መመስረት ከፍተኛውን ሚና የተጫወተው የ«ህዝባዊ ሓርነት ኤርትራ–ሰውራዊ ባይቶ» (ELF–RC) በተለምዶ «ጀብሃ» በመባል የሚታወቀው ነው። ሆኖም፣ የጀብሃ (ELF–RC) መሪ የሆነውና በቀላሉ ለነ መለስ አይምበረከክም የሚባልለት አቶ ስዩም ዑቅማሚካኤል፣ በመለስ ተግፍትሮ፣ «ሃምኤ/ENA»ን በመሰረተው ጉባኤ ላይ ለመገኘት በመጨረሻዋ ደቂቃ ብቻ ወደ አዲስ አበባ ብቅ ያለው አቶ ህሩይ ተድላ ባይሩ ከመቅፅበት የግምባሩ መሪ ሆኖ መሰየሙ የስብሓት ነጋ ረቂቅ የቤት ስራ ለመሆኑ በሚገባ ተረጋግጧል። በሌላ በኩል ደግሞ መለስ ዜናዊና ስብሓት ነጋ ሱዳንና የመን በማስተባበር የኤርትራን መንግሥት ተቃዋሚዎች በፋይናንስ፣ በትጥቅና በዲፕሎማሲው ዘርፎች ከፍተኛ ድጋፍ አግኝተው እንዲጠናከሩ አድርገዋል።

የአቶ ህሩይ ተድላ ባይሩ ለዚህ ስልጣን መብቃት ለወያኔ መሪዎች ማስፈለጉ ብዙ ጥልቅ ምክንያቶች አሉት። በዋናነት የሚታወቀው ግን፣ «በመጀመሪያ የትግራይና የኤርትራ ህዝብ በተለየ ሆኔታ ማስተሳሰር፣ ማለትም ካሁን በፊት የኤርትራ አባቶች ወጥነውት የነበረውን ‹የትግራይ ትግርኚ› ቅኝት መተግበር፣ ከዚያ በኋላ ደግሞ የትግራይ ትግርኚው ትስስር ከተቀረው የኢትዮጵያ ክፍል ጋር በፌደራሲዮን ማዋሃድ ያስፈልጋል» የሚለው የነ መለስ ዜናዊ/ስብሓት ነጋ እቅድ አቶ ህሩይ ተድላ ሳያወላውል ይቀበላል ተብሎ ስለታመነበት ነው።

በአንፃሩ ደግሞ በጣም ታዋቂ የሆነው የተጋድሎ ሓርነት ኤርትራ – አብዮታዊ ሸንጎ (ጀብሃ) መሪዎች የግምባሩን አመራር እንዳይቆጣጠሩ እነ ስብሓት ነጋ ያልፈለጉበት ምክንያት ግልጽ ነው። እንደሚታወቀው፣ አንጋፋው ጀብሃ (ELF)፣ በወያኔና በሻዕቢያ የተቀነባበረ ውጊያ ተመቶ ለስደትና ለመበታተን የበቃ ድርጅት ነው። ከዚያ በላይ ደግሞ አሁን የነ መለስ/ስብሓት አንገት አንቃ የያዘቺውን ባድመ የኤርትራ አካል ናት በሚል በትግሉ ዘመን ጀብሃ ከህወሓት ጋር መዋጋቱ የሚታወስ ነው። አሁንም ቢሆን በጀብሃ በኩል ባድመ የኤርትራ አይደለችም የሚል አቋም የለም። ስለዚህ፣ ለግምባሩ መመስረት ብዙ የጣሩትን የተጋድሎ ሓርነት ኤርትራ – አብዮታዊ ሸንጎ (ጀብሃ) መሪዎች ወደ ዳር ተገፍትረው አቶ ህሩይ ተድላ ያዲሱ ግምባር መሪ እንዲሆን የተመረጠበት ዋናው ምክንያት፣ «ጀብሃ ካሁን በፊት በህወሓት በመመታቱ ቂሙን አይረሳም» ከሚል ስጋት በተጨማሪ፣ «ሻዕቢያ ከተመታ በኋላም ቢሆን ጀብሃ የባድመ ይሰጠኝ ጥያቄ ማንሳቱ አይቀሬ ነው» ከሚል የመለስና የስብሓት ነጋ አስጨናቂ ስጋት የመነጨ ሆኖ ይገኛል።

እስካሁን ድረስ ከኤርትራ ተቃዋሚዎች በኩል የድንበር ውሳኔውን በመደገፍ አቋሙን በጋዜጣዊ መግለጫ ይፋ ያደረገው፣ ከአስመራ እስር ቤት አምልጦ ወደ ኢትዮጵያ የገባውና ከዚያም ወደ ውጭ አገር የቀጠለው አቶ ሰመረ ከሰተ የሚመራው «የዴሞክራሲ ለውጥ እንቅስቃሴ» (Movement for Democratic Change) የተባለው ድርጅት ብቻ ነው። ይህ ድርጅት፣ «የድንበሩ ውሳኔ ባስቸኳይ ተግባራዊ እንዲሆንና፣ ኢትዮጵያ ከባድመና ለኤርትራ ከተበየነላት ሌላው መሬት ባስቸኳይ ለቃ እንድትወጣ» የሚል መግለጫ አውጥቷል። ከዚህ የተነሳ ባዲስ አበባ የሚገኙ የድርጅቱ የማዕከላይ ኮሚቴ አባላት የሆኑት፣ አቶ ሓድሽ ኃይለ፣ አቶ ዮሓንስ አልማዝና፣ አቶ ጀማል ዓብደልመጂድ የተባሉ ሰዎች ለወያኔ እስርቤት ከተዳረጉ በኋላ ለጊዜው ከእስር ተለቀው በዓይነ ቁራኛ እንዲጠበቁ ተደርገዋል።

የድንበሩ ውሳኔ የሚቀበሉና ለተግባራዊነቱም የሚታገሉ መሆናቸውን እስካሁን ይፋ ያደረጉ የኤርትራው መንግሥት ተቃዋሚዎች እየታፈኑ ባሉበት ወቅት፣ ያቶ ተድላ ባይሩ ግምባር ግን እስካሁን ድረስ የድንበሩን ውሳኔ በተመለከተ አቋሙን አልገለጸም። ከማሌሊቶቹ ጋር ካልተጋጨ በቀር፣ ለወደፊቱም ቢሆን የድንበሩን ውሳኔ ደግፎ የሚያወጣው መግለጫ ይኖራል ተብሎ አይጠበቅም።

ሃምኤ/ENA ከተመሰረተ ወዲህ፣ በተለያየ መንገድ፣ ከኤርትራ መንግሥት ተቃዋሚዎች ጋር ግኑኝነት ካላቸው የግል ወዳጆቼ የሆኑ የኤርትራ ዜጎች በኩል ለኔ ለራሴ በግል ሲተላለፍልኝ የቆየው መልእክት ጠቅለል ባለ መልኩ፣ «ኢትዮጵያንና ኤርትራን በፌደራላዊ ትስስር ማቆራኘት ይቻላል። የድንበሩ ጉዳይም ተጨማሪ ጣጣ ከማምጣቱ በቀር ሌላ ምንም ቁምነገር ስለሌለው ከዚያ ለሚበልጥ የሁለቱም ህዝቦች ጠቃሚ ግኑኝነት መስራት ያስፈልጋል። ወዘተ.» የሚል ነው። የዚህ ዓይነቱ ግብዣ ከ«ሃምኤ/ENA ጎራ ደጋፊዎች ሲቀርብልኝ ከከረመ በኋላ፣ አሁን በቅርቡ ደግሞ ከራሱ ከማሌሊቱ ቀንደኛ መሃንዲስ ከስብሓት ነጋ ጎራ አንድ ሌላ ትኩስ ግብዣ በማያወላውል መንገድ ቀርቦልኛል።

ይህ ትኩስ ግብዣ፣ በቀጥታ ከስብሓት ነጋ ጎራ፣ ባሁኑ ሰዓት መምጣቱ ያለምክንያት አይደለም። ባለፈው ቅርብ ጊዜ «አስቸኳይ ማስታወሻ» በሚል አጭር መልእክቴ ላይ እንደገለጽኩት፣ ይህ አዲስ የግብዣ ጥሪ ቀደም ሲል «አስቸኳይ ማስጠንቀቂያ» በሚል ያቀረብኩት ጽሁፍ የገፋው/የወለደው እጅግ ከፍተኛ የመረጃ ጭብጥ ነው። ይህ የመረጃ ጭብጥ ከታች ከሚቀርበው የመፍትሄ ሓሳብ ጋር በቀጥታ የተያያዘ በመሆኑ፣ አጠር ባለ መልኩ መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል።

ባለፈው ወር «አስቸኳይ ማስጠንቀቂያ» በሚል ያቀረብኩት ጽሑፍ የተቋጨው ይህንን አሁን የያዝኩትና፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች ወደ ሌላ እልቂት እንዳይገቡ አንድ የመፍትሄ ሃሳብ ይዤ የምቀርብ መሆኑንና የኢትዮጵያ ህዝብም ይህንኑ የመፍትሄ ሃሳብ በጥሞና እንዲከታተል ጥሪ በማቅረብ እንደነበረ የሚታወስ ነው። ከዚሁም በተጨማሪ የሚቀርበው ሃሳብ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ቢያገኝ አስፈፃሚው ክፍል የተባበረ የተቃዋሚ ድርጅቶች ስብስብ ብቻ እንደሆነ በመጠቆም፣ አሁን ስራው በመፋጠን ላይ ላለው «የፖለቲካ ድርጅቶች ጉባኤ» ህዝቡ ድጋፉን እንዲቸር ጥሪ በማድረግ ነበር።

የዶክተር አክሊሉ ሃብቴን ቋንቋ ለጊዜው ልዋስና፣ እነዚህ ጥሪዎቼን በሚገባ «ያኘከው» ቢኖር፣ የማሌሊት የተንኮል ዋና መሃንዲስና የዚያች የምወዳት አክስቴ «የተረገመ ልጅ» የሆነው መሰሪው ስብሓት ነጋ ነው። እነ ስብሓት/መለስ ዜናዊ በመረጃ ሰራተኞቻቸውና በፖለቲካ ተንታኞቻቸው አማካኝነት ካላቸው የቅርብ ክትትልና ጥናት አኳያ፣ ካሁን በፊት ከጻፍኳቸው ጉዳዮች በመነሳትና፣ አሁን የማቀርበው የመፍትሄ ሃሳብ ይዘቱ ምን እንደሚሆን በትክክል የሚያውቁት ነው። ስለሆነም ይህንኑ የመፍትሄ ሓሳብ ይፋ ከማድረጌ በፊት፣ ለረጅም ጊዜ አግኝቸው የማላውቅ ልክ እንደኔ ለስብሓት ነጋ ያክስቱ ልጅ የሆነ፣ ለኔም በጣም የቅርብ የስጋ ዘመዴ የሆነ አንድ አዛውንት ሰው ባልጠበቅሁት ሰዓት ወደኔ እንዲመጣ መገደዱ የግድ ነበር።

ይህ ዘመዴ ምንም እንኳ ባለፉት ሰላሳ ዓመታት የተሳሳቱ የፖለቲካ መስመሮች እየተከተለ ሲወናበድ የቆየ ቢሆንም፣ በማንኛውም ድርጅት በውል ተደራጅቶ ያልተሳተፈ፣ ወያኔንም አዲስ አበባ እስኪደርስ ድረስ የተቃወመ፣ በኤርትራ ከኢትዮጵያ መለየትም በእጅጉ የሚበሽቅ ሰው ሲሆን፣ የኔን ክፉነትም የማይወድ፣ በብዙ ምክንያትም የማከብረውና የሚያከብረኝ የስጋ ዘመዴ ነው። ከዚህ ዘመዴ ጋር፣ ብዙ ውይይት ካካሄድን በኋላ፣ ስሙን በይፋ እንደማልገልጽ ቃል የገባሁለት ስለሆነ፣ ይህንኑ ቃሌን በመጠበቅ፣ ይዞት የመጣው ግብዣ ይዘት ግን፣ «አስጎምጂ» ስለሆነ ህዝብ እንዲያውቀው ማድረግ አስፈላጊ ነው። ምንም እንኳ ይህ ግብዣ በሌላ መንገድ፣ ማለትም በሌሎች ዘመዶቼና ባንዳንድ የኤርትራ የተቃዋሚው ጎራ ደጋፊዎች በኩል፣ የማውቀው ግብዣ ቢሆንም፣ እስካሁን ድረስ ያሉትን መረጃዎች በበለጠ በመመዘንና በማጽናት ግን ጠቃሚ አስተዋጽኦ ያለው ነው።

ከዚህ የቅርብ ዘመዴ ጋር ባደረግሁት ሰፊ ውይይት መሠረት፣ ሌላ ሌላውን ትቼ፣ የመረጃውን ፍሬነገር ብቻ ለህዝብ ይፋ የማድረግ ህዝባዊ ኃላፊነት ያለብኝ መሆኑን ግን ከስምምነት ላይ ደርሰናል። በተጨማሪ፣ በበኩሌ ይህንን ወንድሜን የላከው ስብሓት ነጋ ነው የሚል ግምት ያለኝ ሲሆን፣ ይህንኑ ግምቴም ለዘመዴ የሰነዘርኩለት ቢሆንም፣ እሱ ግን «በራሴ አነሳሽነት፣ ለአገራችን ችግር ዘላቂ መፍትሄ በማስገኘት ይጠቅማል ከሚል ነው» በሚል ሊያስረዳኝ ሞክሯል። ግራም ነፈሰ ቀኝ፣ የተከበረው ዘመዴ በስብሓትም ተላከ በራሱ አነሳሽነት መጣ የማያጨቃጭቅ ሆኖ፣ ቁምነገሩ ሰውየው ይዞት የመጣው ግብዣ ይዘቱ ምን እንደሆነና፣ እኔም ሆንኩ ሌሎች ዜጎች ግብዣውን እንዴት እንደምናስተናግደው ከመወያየቱ ላይ ነው።

ይህ የመረጃ ጭብጥ ለዚህ የመፍትሄ ሃሳብ መዘግየትና ከታቀደለት በላይ ሰፍቶ እንዲቀርብ አስገዳጅ ተፅእኖ የፈጠረ ነው። የነጻው ፕሬስ፣ ሁሌም ህዝብን ለማሳወቅ የማቀርባቸው አስተያየቶችንና ሃሳቦችን በማስተናገድ ረገድ የቸረው ሰፋፊ አምዶቹንና ትዕግሱቱን አደንቃለሁ። አሁንም ይህ ዝግጅቴና በውስጡ የታቀፉት መረጃዎቼም ወቅታቸውን ጠብቀው ከባለጉዳዩ ህዝባችን

ዘንድ እንዲደርሱልኝ ካለኝ ፅኑ ፍላጎት አንጻር፣ ነፃው ፕሬስ ይህ የጋራ የሆነን ሃገራዊ ጉዳይ በህዝብ ዘንድ ፈጣን ግንዛቤ ያገኝ ዘንድ፣ የተለመደውን አገልግሎቱንና ትዕግስቱን እንደማይነፍገኝ እምነቴ የፀና ነው። ይህንን ትውልድ ራሱን ከጥፋት ለማዳን እንዲከላከል ይቻል እንደሆነ የሚደረገው ትግል ወሳኝ ምዕራፍ ላይ በመድረሱ፣ ካሁን በኋላ ሊወስድ የሚገባው ማንኛውም እርምጃ በመደማመጥና በተባባረ መልክ ካልተከናወነ በቀር፣ «ውሃ ቢወቅጡት እንቦጭ ነው» እንደሚሉት ሆኖ መቅረት ነውና፣ የነፃው ፕሬስ ትዕግስትና ትብብር የምጠይቀውም ከዚህ አኳያ መሆኑን ከወዲሁ ለማስታወስ እወዳለሁ።

የዘመዴ ግብዣ ይዘት ከመጥቀሴ በፊት፣ ከዚህ መረጃ ጋር በተያያዘ፣ የዚህ ዘመዴ መጠነኛ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተክለሰውነት መግለጽ ለመረጃው ጭብጥ ግንዛቤ ጠቃሚ አስተዋፅኦ ይኖረዋል የሚል ግምት አለኝ። ምክንያቱም አንድ መረጃ ከይዘቱ ይበልጥ ሊተኮርበት የሚገባው የመረጃው ምንጭ ምንነትና የምንጩ ተአማኒነት ስለሆነ ነው።

የተከበረው ዘመዴ ካፄ ኃይለ ስላሴ መንግሥት ጋር በመጋፋት ካገሩ ወጥቶ አውሮጳ ከገባ ወደ አርባ ዓመቱ ተጠግቷል። በዓለም ፖለቲካም ሆነ በተለይ በኢትዮጵያና በኤርትራ ፖለቲካዊና ታሪካዊ ጉዳዮች ባለፉት ሰላሳ አምስት ዓመታት ብዙ ክትትል አድርጓል። በተለያዩ ጊዜያቶች ኢህአፓን፣ መኢሶንን (ከደርግ መፈጠር በፊት)፣ ደርግን (ከኢሰፓአኮ/ኢሰፓ መፈጠር በኋላ)፣ ወያኔን (ደርግ ከወደቀ በኋላ)፣ በተለያየ ጊዜና በተለያየ ምክንያት ሲደግፍና ሲቃወም የነበረ ሰው ነው። ካለፉት አስራ ሁለት ዓመታት ወዲህ ወደ አዲስ አበባና ወደ አስመራ ብዙ ተመላልሷል። ለሁሉም ቤተሰብ ማረፊያ በሚል በኢትዮጵያ አንድ መልካም ቤት ቀልሷል። ሰውየው እንደ ሰው ክፉ ሰው ባይሆንም፣ ክፋቱ እሱ የወደደውን ሁሉ ሌላው እንዲወድለት ወደ ማስገደድ ገደማ ያዘነበለ ፍላጎት የነበረውና ይህንን ባህርይ አሁን እየተወ ያለ ሰው ነው። የኔው ዘመድ የፖለቲካ ህይወት ባብዛኛው ከአቶ ህሩይ ተድላ ባይሩ የተሳሳረና የተሻረከ ነው። የዚህ ዘመዴ ወላጅ አባትና ያቶ ህሩይ አባት ደጃዝማች ተድላ ባይሩ በትግራይ በዓድዋ ከተማ በአስተማሪነት አብረው ከመስራታቸውም በላይ በፖለቲካ አመለካከታቸው የቅርብ ሸሪኮች ናቸው። የዘመዴ እናትና የአቶ ህሩይ እናትም እጅግ ከመዋደዳቸው በላይ እርስ በርስ ሲጠራሩ «አዳነይ» (ጓዲትየ) በሚል የፍቅር አጠራር ነው። ስለ ዘመዴ ተክለሰውነት ቀንጭቤ ይቺን ትንሽ ነገር ካስጨበጥኩ በኋላ ዘመዴ ያቀረበልኝ ግብዣ ከህዝብ ጋር ለመጋራት ያህል መረጃውን ላስከትል። የዘመዴ ግብዣ፣፣ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲጨመቅ፣ እንዲህ የሚል ይዘት ያለው ነው።

> «በነ አቶ ስብሓት ነጋና በነ አቶ ህሩይ ተድላ ባይሩ መካከል ሁሉንም ክፍል ከሚያጠግብ ስምምነትና መግባባት ላይ ተደርሷል። ‹ሁሉንም ክፍል› የሚባሉት የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች፣ አሜሪካና ሸሪኮቿ የምዕራብ መንግሥታት፣ ሱዳንና የመን፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ የአፍሪካ ህብረት፣ በቅድሚያ የሚጠቀሱ ናቸው። ‹የሚያጠግብ ስምምነትና መግባባት› የሚባለው ደግሞ፣ የድንበር ውሳኔው አሁን ኢትዮጵያዊያን የሆኑትን ብዙ ሰዎች ኤርትራዊ ዜግነት እንዲኖራቸው የሚያስገድድ፤ አሁን ኤርትራዊያን የሆኑትን ጥቂት ሰዎች ደግሞ የኢትዮጵያ ዜግነት እንዲኖራቸው በማስገደድ ከባድ ውዝግብ ስለሚፈጥር፣ የድንበር ማካለሉ ጉዳይ በሁለቱ አገሮች መንግሥታት ስምምነት ውድቅ ሆኖ፣ ሁለቱም አገሮች በአሁኑ ይዞታቸው እንዲረጉ ማድረግ ነው። አሁን በኤርትራ ያለው መንግሥት ግን በድንበሩ ውሳኔ ያለመለወጥ ፀንቶ ስለደረቀና ለወደፊቱም ስልሚደርቅ፣ የድንበር ውሳኔው ደግሞ በኢትዮጵያ በኩል ሰማይና መሬት ቢጣበቅ ተቀባይነት ስለሌለው፣ ከሁሉ በፊት ለኢትዮጵያ ጠንቅ መሆኑ የታመነበት አሁን በኤርትራ ያለው የሻዕቢያ መንግሥት ባጭር ጊዜ መገርሰስ አለበት።
>
> «የሻዕቢያ መንግሥት ከተገረሰሰ በኋላ፣ አዲሱ የኤርትራ አስተዳደር ስራውን የሚጀምረው፣ በቅድሚያ በትግራይ ህዝብና በኤርትራ ህዝብ መካከል የጠበቀ ክልላዊ የአስተዳደር ትስስር በመፍጠር፣ የመሬቱ የይገባኛል ጥያቄም በዚሁ ትስስር ከስሞ እንዲቀር ማድረግ ይሆናል። በቀጣዩ ደግሞ የትግራይና የኤርትራ ክልላዊ ትስስር ከተቀረው የኢትዮጵያ ክፍል ጋር በጠንካራ ፌደራላዊ መስተዳድር እንዲዋሃድ ይደረጋል።» የሚል ነው።

እንግዴህ፣ ይህ ግብዣ፣ በደረቁ ሲታይ፣ የሚያስጎመጃቸው ሰዎች ይታጣሉ ብሎ መገመት አይቻልም። ያም ሆነ ይህ፣ እኔን በተለየ መንገድ በከበሬታ ለመጋበዝ የተፈለገበት ራሱ የቻለ ምክንያት አለው።

እኔ፣ ከረጅም ዘመናት ጀምሮ፣ «የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች በጠንካራ ፌደራሲዮን ቢተሳሰሩ፣ በክፉ ዓይን ሳይተያዩና ለግጭት ሳይፈላለጉ፣ ለዘለዓለሙ በሰላምና በብልጽግና ደልቷቸው አብረው ሊኖሩ ይችላሉ። ከዚያ በመለስ የሚደረግ ማንኛውንም ነገር በሙሉ ግን፣ አብሮ ከመማቀቅና ብሎም ከመጠፋፋት በቀር ሌላ ፋይዳ የለውም»፣ የሚል ጽኑ አቋም ያለኝ ሰው ነኝ። ይህንን አቋሜም፣ ከማንም በላይ፣ የወያኔ መሪዎች፣ በትግራይና፣ በኤርትራ በኩል ያሉ የስጋ ዘመዶቼ ጠንቅቀው የሚያውቁት ነው። ስለሆነም፣ ወዳጄና የቅርብ ዘመዴ የሆነው የትግራይ ተወላጁ ዘመዴ ሊያስተላልፈው የፈለገው መልእክት፣ ባጭር አገላለጽ ለማቅረብ ከተፈለገ፣ «ለብዙ ዘመናት ስታልመውና ስትታገልለት የነበረው ሃገራዊ ቁምነገር ስለደረሰልህ፣ ፊትህን ወደዚሁ አዙረህ፣ ከተቻለ ሻዕቢያን በማስወገዱ ትግል ተባበር፣ ካልሆነም ለጊዜውም ቢሆን በገለልተኛነት አርፈህ ተቀመጥልን» የሚል ሆኖ ይገኛል።

«ትግራይ ትግሪኚ» የሚባለው ትስስር የሚጠናና የሚያወያይ ፍሬነገር ሆኖ፣ ግብዣውን እንደተባለው ተቀብሎ ሻዕቢያን ለማስወገድ በድግሱ ዝግጅት ላይ የመሳተፍ፣ ወይም ደግሞ ግብዣው ያጥግብ አያጥግብ በማያስጨንቅ በገለልተኝነት ድግሱን ሳያደናቅፉ የመቀመጥ ውሳኔ፣ የያንዳንዱ ተጋባዥ መብትና ግዴታን የሚመለከት ይሆናል። ሆኖም በግሌ ያለኝ አመለካከት፣ አቶ መለስ ዜናዊና አቶ ስብሓት ነጋ የሚያቀራጇቸው ትግራይና ኤርትራ፣ የሚያዋህዷቸው ትግራይ–ትግርኚና ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ለምንኖርበት አስፈሪና አወዛጋቢ ያፍሪካ ቀንድ ቀጣና ዘለቀታዊና አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት ያመጣል የሚል ብዥታ የለኝም። እነዚህ ሰዎች እንደሰው ተፈትነው ወድቀዋል። ፈተናውን እንዲያልፉ ደግሞ፣ ከነሱ በብዙ ጊዜ በእውቀትና በዕድሜ ተሞክሮ የሚበልጡ ወገኖቻቸው ብዙ ምክርና ተግሳፅ ቢለግሷቸው፣ በቀልዳቀልድና በአፀያፊ ሽሙጥ አጥላልተው በመጣል ሲወጠሩ ቆይተዋል። ይኸውና ዛሬ እንኳንስ የአገራቸውንና የህዝባቸውን ደህንነት ሊያረጋግጡ ቀርቶ፣ ራሳቸውንም ለማዳን ከማይችሉበት አዘቅት ውስጥ ሰምጠው፣ ሌላ ሰው እጃቸውን ጎትቶ ከዚህ አዘቅት ካላወጣቸው እነሱ ብቻቸው ራሳቸውን ማዳን እንደማይቻላቸው ገሀድ እያደረጉልን ይገኛሉ!

የጉዳዩ ፍሬ ነገር ይህ ሆኖ ሳለ፣ ተቀርቋሪው ዘመዴ ያቀረበልኝ መልካም ግብዣ/ድግስ ግን እኔ ብቻየን በልቼ አልጨርሰውም። ድግሱን የሚደግሰው ደግሞ፣ ሁሌም ከደገሰው ድግስ ስጋው ተበልቶ ያለቀ ደረቅ አጥንት ሲቀርብለት የኖረው ምስኪኑ ህዝባችን ብቻ ነው። ይህንን በቅንነት በመረዳት፣ ለውይይት ይረዳን ዘንድ፣ የግብዣው ዝግጅት ምን እንደሚመስል ለህዝብ ማቅረቡ ጠቃሚ መሆኑን ከተከበረው ዘመዴ ጋር በሃሳብ ከስምምነት ላይ ለመድረስ መቻላችን፣ ይህ በራሱ አንድ ሊደገፍ የሚገባው አብይ የባህላችን የእድገት ፍንጭ ነው። ለዚህ ስምምነት መደረስ ዋናው ምክንያትም፣ ሁለታችንም (እኔና ዘመዴ) ቢያንስ በኢትዮጵያና በኤርትራ ፌደራላዊ ትስስር አንድ ዓይነት እምነትና አቋም ያለን መሆኑ ነው።

ይህ ስትራቴጂያዊ አንድነታችን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ልዩነታችን የተመሰረተው ይህንን የጋራ ስትራተጂያችንን ለማስፈጸም በምንከተለው የተለያየ ስልት/ታክቲክ ብቻ ነው። የስልት/የታክቲክ ልዩነት ደግሞ አጭር ዕድሜ ኖሮት፣ ጊዚያዊ ጥቅም ወይም ጉዳት አስከትሎ በሃሳብ ከከሰመ በኋላ፣ በስልት/በታክቲክ የተለያዩትን እንደገና ካንድ ማዕከላዊ መድረክ ሊያገናኛቸው ስለሚችል፣ ከራስ የተለየ ስልት/ታክቲክ ይዞ የመጣን ሰው የጠላት ግብረ በላ አድርጎ መቁጠርና በዚያ መልክ ማስተናገድ ከኢትዮጵያዊያን የፖለቲካ ተሞክሮ ጨርሶ መወገድ ያለበት አጸያፊና ጎጂ የሆነ ልማድ ነው። የኔ የስልት ልዩነት የዚህ ጽሑፍ ማሳረጊያ የሆነው የራሴ የመፍትሄ ሃሳብ ነጥቦቼን ሳቀርብ ግልጽ የማደርገው ይሆናል።

## የማሌሊት ስርዓት ቀጣይ እርምጃ ምንድን ነው

መለስ ዜናዊ የተባለ ተናካሽ አውሬ፣ ባጠቃላይ በግጭቱ ሰበብ፣ በተለይ ደግሞ በድምበር ውሳኔው ጥይት ከፉኛ ተመቶ ከቆሰለ በኋላ በጣረሞት ተይዞ በመንፈራፈር ላይ ይገኛል። አውሬ ደግሞ የአውሬነቱን ባህርይ በበለጠ የሚገልጸው፣ ጥቃት በደረሰበት ሰዓት ነው። ስለዚህ መለስ ዜናዊ ከቁስሉ አገግሞ ይድናል ብሎ ማመን ቢያስቸግርም፣ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ተናዳፊና ተቅበዥባዥ አውሬ ሆኖ መገኘቱ ግን ያደባባይ ምስጢር ሆኖ ይገኛል። የመለስ በጣረሞት ተይዞ መገኘቱ ብቻ ግን በራሱ አደገኛ ክስተት ለመሆኑ በጥሞና ሊጤን ይገባዋል። መለስ በተከበበና በተወጠረ ቁጥር፣ የአውሬነት ባህርዩ አይሎ በመውጣት አጥፍቶን እንደሚጠፋ ወይም እንደሚሸሽ በተደጋጋሚ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

መለስ ዜናዊ በድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ መሠረት ከሻዕቢያ ጋር ድንበር ይካለላል ብሎ መጠበቅ ፈፅሞ የሚቻል አይደለም። መለስ ውሳኔውን ተግባራዊ የማያደርገው ጠልቶት ሳይሆን፣ ከሁሉ በላይ ሰራዊቱን፣ ደጋፊዎቹን፣ ካድሬዎቹንና የትግራይ ህዝብን፣ ባጠቃላይ ደግሞ

የኢትዮጵያን ህዝብ ብስጭትና ቁጣ በገሃድ ባይኑ እያየው ስለሆነ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ፣ መለስ ህዝቡን በመፍራት ለውሳኔው ያለመተግበር ሰበብ እየፈጠረ ውሳኔው እንደተንጠለጠለ ለረጅም ጊዜ መቀጠል ይቻለዋል ማለት ግን አይደለም። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ ከአራት ሺ ወታደሮች በላይ ያቀፈ የሰላም አስከባሪ ኃይል፣ ከአስራ ሁለት ሺ በላይ በሚሆኑ ልዩ ልዩ የሲቪል ባለሙያዎችና ሌሎች የጉልበት ሰራተኞች እየቀለበና በየቀኑ ብዙ ሚልዮን ዶላር እያፈሰሰ መለስን በማቆላመጥ ጊዜውን ለማጥፋት እንደማይፈቅድ ከማንም በላይ መለስ ራሱ በሚገባ የሚያውቀው ነው።

የኤርትራ መንግሥትም ውሳኔው ተግባራዊ ሆኖ ድንበሩ ይከለልልኝ በማለት የሚመለከታቸውን ሁሉ ከመወትወት ወደኋላ የሚል አይደለም። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም፣ በዚህ ጨዋታ በኢትዮጵያ የራሳቸው የስትራተጂ ጥቅምና ችግር ካላቸው ኃይሎች ዘንድ «በህግ ፊት ተቀባይነት ያለው ግልጽ ድጋፍ» አግኝቶ፣ ሻዕቢያ፣ «በዓለም የፍርድ መድረክ የተበየነልኝን መሬት በኃይል እወስዳለሁ» ቢል አሰገራሚ አይሆንም።

አስፈጻሚው አካል ደግሞ ውሳኔውን ካጭር ጊዜ በኋላ ተግባራዊ ለማድረግ የማካለሉን ስራ መጀመር አለብኝ ብሎ እየተሯሯጠ ስለሆነ፣ መለስም ውሳኔውን ላለመቀበል አሻፈረኝ ብሎ መቀጠል ስለማይቻለው፣ መለስ በቀረችው አጭር ጊዜ ይህንን ሆኔታ ለመለወጥ ይገደዳል። ይህም ማለት፣ መለስ ወደ ኤርትራ መመረሽ አለበት ማለት ነው። ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርበው ጥያቄ «መለስ ወደ ኤርትራ ለመመረሽ እንዴት ይቻለዋል » የሚል ብቻ ስለሚሆን ይህንኑ እንፈትሽ።

«መለስ ከሻዕቢያ ጋር የተጋጨው ሻዕቢያ ወራሪ ስለሆነ፣ መለስም ወረራውን ለመከላከል ሲል ነው ወደ ጦርነት የገባው» የሚለው የጠንቋዮች ግንዛቤ የችግሮቻችን ሁሉ ምንጭ ነው። ይህንን አስመልክቶ ብዙ የጻፍኩለት ስለሆነ፣ እዚያ ውስጥ ገብቶ ተጭማሪ ጊዜ አላጠፋም። ዋናው ቁምነገርና ደግነቱ ግን፣ መለስ በኤርትራ ጉዳይ ገና ከጥዋቱ ይዞት የተነሳለት አጀንዳ ምን እንደሆነና፣ ከግጭቱ በኋላም ቢሆን፣ ብዙዎች ካሁን በፊት እንደነገሩን፣ መለስ ይህንኑ አጀንዳውን ሰርዞ «የኢትዮጵያ ባንዴራ ባንዴራየ ናት» ያላለ መሆኑን፣ ህዝቡ፣ በተለይም የትግራይና ያማራ ተወላጆች፣ በማያጨቃጭቅ መንገድ በግልጽ ለመረዳት መቻላቸው ነው።

አንዳንዶቹ እንደሚሉት፣ የአልጀርሱ ስምምነት አሉታዊነት፣ የባድመ መንደር፣ ሌላው መሬትና የተወሰነ የህብረተሰባችን ክፍል ያለፍላጎቱ ወደ ኤርትራ ማስወሰዱ ብቻ አይደለም። የነዚህ ጉዳዮች አሳሳቢነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከዚህ በበለጠ ግን፣ የአልጀርሱ ስምምነት ውጤት የሆነው የሄጉ ይግባኝ የለሽ አሳሪ ውሳኔ፣ ኢትዮጵያና ህዝቧን ለታላቅ ውርደት ከመዳረጉም በላይ፣ ኢትዮጵያ በዓለም ህብረተሰብ ፊት እንደ ጀብደኛ ወራሪና የራሷ ያልሆነን ግዛት ለመቦጨቅ እንደተንፈራገጠች አመፀኛ አገር ሆና እንድትቆጠር ማድረጉ ጭምር ነው። ሻዕቢያንና ማሌሊትን ለማለያየት በእጅጉ የደከሙትና የተሰዉት ብርቅየ የኢትዮጵያ-ትግራይ ህዝብ ልጆችን ድካመ ቢስ አድርጎ አንገት ያስደፋውም፣ በዚህ የገበያ ግርግር፣ የተረጋገጠው አዋራጅ ውሳኔ ነው። ስለሆነም መለስ ባሁኑ ጊዜ በልቡ የሚሳለቅበት ምክንያት ቢኖረው፣ «ኤርትራን አትንኩ ብየ ብል፣ ራሳችሁ በለኮሳችሁት እሳት እናንተው ራሳችሁ ተቃጥላችሁ ማረር ትችላላችሁ። ችግራችሁ ሻዕቢያ ከሆነ ደግሞ ዛሬ ሻዕቢያ እናንተ በለኮሳችሁት ክብሪት ተገዶ ለኔም ጠላቴ ሆኗልና፣ እሱን አስወግጀ ሌላ በመተካት እንደገና ተጠናክሬ እወጣባችኋለሁ።» የሚል ብቻ መሆን አለበት።

መለስ ሻዕቢያን ለመጣል ከቻለ፣ ሁሌም የሚሳሳላት ኤርትራ፣ ዛሬ ከመቼውም በበለጠ ዓለም አቀፍ ድንበሯ በህግ ታውቆላት፣ የመለስ ዋና አጀንዳ የሆነውን ኢትዮጵያን የመበተን ዓላማ ልታሳካ በምትችልበት ሆኔታ ተኳኩላ፣ ተሽላልማ ተዘጋጅታለች ብሎ መናገር ይቻላል። አሁን የመለስ ራስ ምታት የሆነው፣ በግጭቱና በተለይ በዓይደር ጭፍጨፋ ምክንያት መለስ ሊታረቀው የማይቻለው ሻዕቢያ፣ ድንበሩ ይከለልልኝ እያለ የሚያስቸግረው መሆኑ ብቻ ነው። የድንበር መካለሉ ክንዋኔ በመሰረቱ መለስ እጅግ የሚፈልገው ቢሆንም፣ ባሁኑ ወቅት በራሱ በመለስና መለስ በሚሳሳላት ኤርትራ ህልውና ላይ ከፍተኛ አደጋ ስለሚያደርስ፣ አቶ መለስ ያለቺው ብቸኛ አማራጭ በኤርትራ ምድር መንግሥት ለውጦ ባቶ ኢሳያስ ቦታ ራሱ መለስ በሚያዘው ሌላ ሰው መተካት ብቻ ነው።

በዓለም የፍርድ ሸንጎ የተበየነውና በአልጀርሱ ስምምነት መሰረት ማንም ሊለውጠውና ሊያሻሽለው አይችልም የተባለለት የድንበር መካለል ጉዳይ ብዙ የሚያወዛግብ ስላልሆነ፣ መለስ ኢትዮጵያን ከበተነ በኋላ ተግባራዊ ለማድረግ ምንም የሚቸግረው አይደለም። በመለስ ልዩ ሙያ በሁሉም የተጠመደውና የተጠላው የትግራይ ህዝብም ከፈለገ ከኤርትራ ጋር ይቀላቀላል፤ አሻፈረኝ ካለ ደግሞ ከሚበተነው ክፍል ጋር የመበተን መብቱ የተጠበቀ ይሆናል። ይህ አባባል ተራ ሽሙጥ ሳይሆን አሁን ያለንበት መድረክና የማያወላውሉ መረጃዎች የሚያረጋግጡት ሃቅ ነው። ይህ ካልኩ

በኋላ፣ ጭብጣችን መለስ ወደ ኤርትራ በመመረሽ አስመራ ያለውን መንግሥት ለመለወጥ እንዴት ይቻለዋል የሚል ስለሆነ፣ ወደዚያው እናምራ።

## መለስ ሻዕቢያን ለመውጋት ምን ሰበብ ይጠቀማል

ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያና በኤርትራ ድንበር መካከል ለሚካሄድ ጦርነት ጀማሪና ቀስቃሽ መሆን ቀላል አይደለም የሚባልለት ብቻ ሳይሆን፣ በህግ የሚያስጠይቅ ወንጀል ጭምር ነው። ሻዕቢያ ቢበዛ «የተበየነልኝን መሬት አሰጡኝ» እያለ ዓለማችንን ከመማጠን ውጪ ከዚያ ባለፈ ግን በድንበሩ ውሳኔ ሰበብ ብቻ ራሱ ጦርነት የሚቀሰቅስበት ምክንያት ፈልገን ማግኘት አንችልም። እነ መለስ ግን፣ በውሳኔው ምክንያት የህልውናቸው ምሰሶ በከባድ ነውጥ ተናግቶ ስለተፈረካከሰ፣ የተፈረካከሰውና ሲጠጋገን የቆየው ስርዓታቸውን የሚደረማምስ ፈንጂም ሊፈነዳ የተሞላው ሰዓት ጊዜው ስለደረሰ፣ ፈንጂውን ለማምከን የተሞላውን ሰዓት ለመለወጥ የቀረቻቸው ዕድል በተለያየ ሰበብና ሽፋን ጦር ሰብቆ ሻዕቢያን ማስወገድና፣ በምትኩ ሌላ ለነሱ የሚስማማ ስርዓት መቆሙን ማረጋገጥ ብቻ ሆኖ ይገኛል። እነ መለስ ሻዕቢያን ለመገርሰስ ጦርነት የሚጭሩበትና በዓለም ህብረተሰብ ፊት አያስጠይቀንም ብለው ያመኑባቸው ሁለት ሰበቦች አሏቸው።

## ሰበብ ቁጥር አንድ

አንዱ ሰበብ፣ የሰላም አስከባሪ ኃይሉን ከዚያ አካባቢ በረቀቀ ዘዴ ገፍትሮ በማስወጣት፣ የኤትርራ ተቃዋሚዎች ግምባር የደጋው ክፍል ግብረ ኃይል በትግራይና በጎንደር ክፍላተ ሃገሮች በኩል ወደ ደቡብና ምዕራብ ኤርትራ፣ የቆላው ግብረ ኃይል ደግሞ በሱዳንና በአፋር በኩል ወደ ተለያዩ የኤርትራ ክፍሎች እንዲዘምቱ የሚደረግ መሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህ ማለት፣ እነ መለስ፣ ይህንን ሰበብ ተጠቅመው፣ «በኤርትራ መንግሥትና በተቃዋሚዎቹ መካከል ጦርነት እየተካሄደ ሳለ፣ ድንበር መካለል አንችልም» ለማለት ምቹ ሆኔታ ይፈጥርላቸዋል ማለት ነው።

እነ መለስ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጡበት የውግያ ግንባር በትግራይና በጎንደር በኩል ሲሆን፣ በትግራይ ግምባር ያለባቸው ችግር የሰላም አስከባሪው ኃይል በጣም አወዛጋቢ በሆነው በትግራይና በኤርትራ ድንበር ሰፍሮ መገኘቱ ነው። ስለዚህ በተቻለ ፍጥነት የሰላም አስከባሪውን ኃይል ከዚያ አካባቢ በረቀቀ ዘዴ ገፍትረው ለማስወጣት አቅደዋል። የሰላም አስከባሪውን ኃይል ገፍትሮ ለማስወጣት በነ መለስ/ስብሓት የተያዘው ዘዴ፣ በተለይ የሰላም አስከባሪው ኃይል ለሰፈረበት ቀጣና ቅርበት ላላቸው የትጥቅ ትግል ለሚያራምዱ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች እጅግ አደገኛና አሳሳቢ ነው። እቅዱ አደገኛና አሳሳቢ የሚያደርገው፣ እነ መለስ/ስብሓት የሰላም አስከባሪውን ኃይል ራሳቸው መትተው «ሻዕቢያ የላካቸው ሽብርተኞች የፈፀሙት የሽብር ተግባር ነው» በማለት ሰላም አስከባሪው ኃይል ለደህንነቱ ሲል ቦታውን ለቆ ወደመጣበት እንዲመለስ ስለሚያደርጉ ነው። ከዚህም የተነሳ የድንበሩ መካለል ጉዳይ ይደናቀፋል ማለት ነው።

የኤርትራ ተቃዋሚዎች ለወደፊቱ ሰፊ ቦታዎች ተቆጣጥረው ወታደራዊ አቋማቸውን ለማሳደግ ይችሉ እንደሆነ እንጂ፣ አሁን ባላቸው የሰው ኃይልና ወታደራዊ ዝግጅት ብቻቸውን ዘምተው ሻዕቢያን መቋቋም ይችላሉ ብሎ መጠበቅ ዘበት ነው። በተለይም ባሁኑ ወቅት የኤርትራ ተቃዋሚዎች በሁለት ምክንያቶች የኤርትራን ህዝብና ሰራዊቱን በራሳቸው ጎን ለማሰለፍ ችግር እንደሚኖርባቸው መረዳት ይቻላል።

አንዱ ምክንያት፣ በድንበሩ ውሳኔ ሳቢያ፣ ሻዕቢያ በህዝቡ፣ በተለይ በሰራዊቱ ዘንድ፣ አንፃራዊ ተኣማኒነት በመጎናፀፉ ነው። ከድንበሩ ውሳኔ በፊት፣ በብዙ ኤርትራዊያኖች ዘንድ የነበረው ጥርጣሬ፣ «ለመሆኑ ባድመ የኤርትራ መሬት ነው ሻዕቢያስ ወደ ጦርነት የገባው እውነት ኤርትራ ከኢትዮጵያ የምትጠይቀው ተጨማሪ መሬትና ሰው ኖሯት ነው » የሚል እንደነበር የሚታወቅ ነው። ከውሳኔው በኋላ ግን፣ ጥያቄው ተገቢ መልስ ስላገኘ፣ ጥርጣሬው በማያሻማ መንገድ ተወግዷል። ዛሬ በኤርትራ ህዝብ ዘንድ ሌሎች የዴሞክራሲና የኤኮኖሚ ጥያቄዎች የሉም ማለት ባይቻልም፣ በውሳኔው ሳቢያ ሻዕቢያ በኤርትራ ህዝብ ዘንድ አንፃራዊ ተአማኒነት መጎናፀፉን ለመረዳት አዳጋች አይደለም።

ሌላው ምክንያት ደግሞ፣ የኤርትራ ተቃዋሚዎች ግምባሩን ማለትም «ሃምኤ/ENA» ሲመሰርቱ ቅድሚያ አጀንዳቸው ያደረጉት፣ እንታገልለታለን የሚሉት የኤርትራ ህዝብ ጉዳይ ሳይሆን፣ በስልጣን ሽኩቻ መፋተጋቸው ነበር። ከዚህ የተነሳ የኤርትራው የተቃዋሚዎች ግምባር በርካታ ደጋፊዎቹን እንዳጣ በሚገባ እናውቃለን። ከዚህ በተጨማሪ፣ የኤርትራ ህዝብ ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ በማሌሊት ሰበብ በደረሰበት ከፍተኛ መፈናቀልና፣ ህዝቡ፣ «ወያኔ የታጋይ ሰማዕታት ልጆቻችንን መካነ–መቃብር ሳይቀር ያፈረሰብን እኩይ ነው»‘(5) ብሎ በመክሰስ ማሌሊትን አምርሮ ስለሚጠላ፣ ኃይል ካላስገደደው በቀር፣ በነ ስብሓት ነጋ አማካኝነት የሚመጣን ስርዓት በፈቃደኛነት የማይቀበል መሆኑ ነው።

ስለዚህ በኤርትራ ተቃዋሚዎች ጭምብል/ሽፋን ወደ ኤርትራ ለሚደረው ዘመቻ በዋናነት የሚሰለፈው፣ ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ጦር ሲሆን፣ በተለየ ግን፣ በነ ስብሓት ነጋ ወረንጦ የተለቀመ ትግርኛ ተናጋሪ የሆነ የህወሓት መደበኛና ተጠባባቂ ሰራዊት እንደሚሆን መረጃዎች በትክክል ይጠቁማሉ። በዚህ ትርምስ፣ ትናንት ለኤርትራ ነፃነት ሲባል የትግራይ ወጣቶች የትም ወድቀው በቀሩበት ሆኔታ፣ ዛሬ ደግሞ ለኤርትራ ዴሞክራሲያዊነት ሲባል ሁላችንም ትንሽ ትንሽ እንድንደማና እንድንሞት ተፈርዶብናል ማለት ነው!

## ሰበብ ቁጥር ሁለት

ሁለተኛው የነ መለስ/ስብሓት ሰበብ፣ ከቅርብ ጊዜ በፊት መለስ ዜናዊ የተውካዮች ምክር ቤት ሲከፍት ባቀረበው ዓመታዊ ሪፖርቱ ላይ በማያሻማ ቋንቋ ግልፅ አድርጎታል። በመሃል አዲስ አበባ፣ መስከረም አንድ ቀን (September 11) ተመረጦ የትግራይ ሆቴል በፈንጅ እንዲጋይ በተደረገና «አድራጎቱን የፈፀመው ሽብርተኛው ኦነግ ነው» ተብሎ በማሌሊቶቹ በተነገረን ማግስት፣ መለስ ለራሱ ፓርላማ ባቀረበው ሪፖርት እንገለጸው፣ «ሻዕቢያ ምንደኞችን እያስታጠቀ ወደተለያዩ ያገራችን ክፍሎች በመላክ ሰላማችን ለማወክ፣ እድገታችን ለማደናቀፍና፣ ብሎም አገራችንን ለመበተን የተለያዩ ሽብርተኞችን ወደተላዩ ያገራችን ክፍሎች በማስገባት ከፍተኛ አደጋ እየደቀነብን እንደሆነ ይታወቃል። ከሽብርተኞቹ መሃል በዋናነት ኦነግ ይጠቀሳል። ስለሆነም፣ ሌሎች ዴሞክራሲያዊያን አገሮችና መንግሥታት የተጠቀሙብትን ስልት በመጠቀም፣ እኛም ሽብርተኝነትን ከምንጩ ገብተን እናጠፋለን» የሚል ነው።

መለስ ዜናዊ ለምክር ቤቱ ያቀረበውን ሪፖርት መሠረት በማድረግ፣ የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ያማርኛው ክፍል ጋዜጠኛ የሆነቺው እህታችን ሄለን መሐመድ የመለስን ሪፖርት ስትዘግብ፣ እንዲህ ትላለች፤ እጠቅሳለሁ፦

> «...ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሃገሪቱ [ኢትዮጵያ] ከጎረቤቶቿ ጋር ያላት ግኑኝነት ሰላማዊና እየጎለበተ መሆኑን የጠቀመው ሪፖርቱ፣ የኤርትራን መንግሥት ግን በጠብ አጫሪነትና አሸባሪዎችን በማስታጠቅ ወንጅሏል። ‘ሻዕቢያ እያሰለጠነ የሚልካቸው ምንደኞች ሰላማችንን ለማወክ በተለያዩ አካባቢዎች ጥረት እንደሚያደርጉ ይታውቃል። ከዚህ አኳያም በቅድሚያ የሚጠቀሰው ኦነግ ነው› ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ምንም እንኳ መንግሥታቸው ከፍተኛ የሰራዊትና የመከላከያ በጀት ቅነሳ ቢያደርግም፣ በዚህ ዓመት የመደበኛ ሰራዊቱን የመከላከል ብቃትና ዝግጁነት የማሳደግ እቅድ እንዳለው አስረድተዋል።»

ጋዜጠኛዋ ይህን ካለች በኋላ፣ ዘገባዋን በመቀጠል፣ ከመለስ ሪፖርት ቀንጭባ፣ መለስ የተናገረውን በራሱ በመለስ ድምፅ ለአድማጮቿ ታሰማለች። እጠቅሳለሁ፦

> «ጀብደኞች ሰላማችንን ለመፈታተን የሚያደርጉትን ሙከራ በብቃት ለማክሸፍ መቻላችን የሚያረጋግጥ ሰፊ ሥራ እንሠራለን። ከዚህ ጎን ለጎን ሰፊ ተጠባባቂ ኃይል ለመፍጠር የሚያስችለን ጥናትና ቅድመ ዝግጅት ባለፈው ዓመት በተካሄደው ርብርብ በመጠናቀቁ ከያዝነው ዓመት ጀምሮ ይህንኑ ተጠባባቂ ኃይል የማሰልጠንና የመፍጠር ሥራ እንጀምራለን። እነዚህን ተግባሮች ለማከናወን ተፈላጊ ሆነው የተገኙ የህግ ለውጦችን ለማድረግ ይቻል ዘንድ ረቂቅ ህጎች ተዘጋጅተው ለምክር ቤቱ ይቀርባሉ።» የጥቅሱ መጨረሻ።

በዚሁ ሪፖርት መሠረት መለስ ለውጥ ያስፈልጋቸዋል ያላቸውን ህጎች ባፋጣኝ ለውጦ፣ ተጠባባቂው ኃይልም በስፋት አሰልጥኖ፣ በቅርቡ አስመርቋል። ይህም ማለት መለስ “ሽብርተኞችን ከምንጫቸው ለማድረቅ” ወደ ኤርትራ ለመመረሽ አስፈላጊውን ቅድመ ሆኔታ አጠናቆ አብቅቷል ማለት ነው።

ባጠቃላይ መረዳት የሚያስፈልገን ጉዳይ ቢኖር፣ መለስ ወዲ ዜናዊና አቦይ ስብሓት/ወልደሰይጣን ነጋ ከሰጠሙበት ማጥ ለመውጣት ያለቻቸው ምርጫ ወደ ኤርትራ መዝመት ብቻ ስለሆነ፣ ከላይ የተመለከቱት ሁለት ሰበቦች ሁለቱንም ባንድ ጊዜ በመጠቀም ወይም በቅደም ተከተል ተጠቅመው ወደ ኤርትራ እንደሚመርሹ የማያጠያይቅ ጉዳይ መሆኑ ነው።

እንግዲህ ሃቁ ይህ ከሆነ፣ ከዚህ ቀጥሎ መቅረብ የሚገባው ጥያቄ፣ መለስ ዜናዊና ስብሓት ነጋ ወደ ኤርትራ የሚያደርጉት ዘመቻ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የዓለም ህብረተ ሰብ፣ የወያኔ ጌቶች የሆኑት ምዕራባዊያን መንግሥታትና፣ ለጋሽ/አበዳሪ የረድኤት/የፋይናንስ ድርጅቶች እንዴት ይመለከቱታል የሚል መሆን ይኖርበታል።

ይህ ጥያቄ ካሁን በፊት በብዙ ተቆርቋሪ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ልጆች በኩል የቀረበልኝና አጥጋቢ መልስ የሰጠሁበት ነው። ሊጠየቅ የሚገባው ጥያቄም ነው። እኔ ራሴም ብሆን፣ ለዚህ ዝግጅት ጥንቅር ሲባል ካደረግሁት ጥናት አኳያ፣ የሰዎችን ግንዛቤ ለመለካት ያህል፣ ይህንኑ ጥያቄ ለተለያዩ ኢትዮጵያዊያንና ኤርትራዊያን ያቀረብኩት ጥያቄ ነው። ስለሆነም ይህን በተመለከተ ሊኖር የሚገባው ግንዛቤ በዚህ ዝግጅትም በመጠኑ ልንዳስሰው ይገባል።

## ጦርነት ቢነሳ የውጭ ኃይሎች ምን ይላሉ?

በበኩሌ «አሜሪካ ምን ይለናል ያውሮጳ ፓርላማ እንዲህ ሊላቸው ይችላል የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቢቆጣስ ቡሽና ቶኒ ብለየር ሰምተውታል ያፍሪካ አንድነት ቢሮ ካዲስ አበባ ተነቅሎ ወደ ሌላ አገር ሊሄድ ነው የሚባለው ትክክል ነው » ወዘተ. የመሳሰሉትን ጥያቄዎች አንስቻቸው አላውቅም! ቁምነገር ስለሌላቸው፣ ላነሳቸውም አልፈልግም። ከነዚህ ሁሉ ጋር ግን ምንም የግል ጠብ ይሁን ፍቅር የለኝም። ላገሬና ለህዝቤ ህልውና፣ ማለትም ለራሴም ህልውና፣ ስል ከማንም ጋር ለመታረቅም ይሁን ለመጣላት ግን ዝግጁ ነኝ! ሌሎች ኃይሎችም (ወያኔን ጨምሮ) ለህልውናቸውና ለጥቅማቸው ሲሉ ካዋጣቸው ማንኛውንም የመሰላቸው እርምጃ ቢወስዱ፣ ከሽብርተኝነት ውጭ እስከሆኑ ድረስ፣ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን በትህትና እቀበላለሁ።

በታሪካችን ሂደት በገሃድ የታየ ነገር ስለሆነ፣ በበኩሌ፣ «የኢትዮጵያን መበታተን ፍላጎት የማን የቤት ስራ ነው » ከሚል ባህረ ሃሳብ ውስጥ ገብቼ መዋኘት አልሻም። አንድ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ቢኖር ግን፣ ኢትዮያጵያና የኢትዮጵያ ህዝቦች፣ ዓለም አቀፋዊ ግዴታቸውን በህጋዊ መንገድ እየተወጡ፣ ማንነታቸውንና ጥቅማቸውን ያስከበራሉ እንጂ፣ እገሌ ገና ለገና ምን ይለኛል ብሎ ራስን መግደል የማያስፈልግ መሆኑን ነው። አሜሪካ ምን ይለናል ወይም አሜሪካ ይፋረድልናል ምናምን የሚሉ ካሉም፣ ራሳቸውን ለመግደል የወሰኑ ብቻ ይሆናሉ። እነ አቶ መለስ ባሁኑ ጊዜ ፀሃይ በባድመ በኩል እንዳትጠልቅባቸው የነብስ–ግቢ ነብስ–ውጪ ሩጫቸውን እንዲሮጡ አስገድዷቸው ያለውም ይህ ዓይነቱ ከንቱ ፈሊጥ ነው። ማሌሊቶች ታማኞቻቸው ሳይቀሩ እየፈረጠጡም ሆነ በተቀመጡበት የስልጣን ወንበር ላይ ሆነው የነ አቶ መለስ ጠላቶች «ህጋዊ» ቃል አቀባዮች እንዲሆኑ አድርጓቸው ያለውም ይህ አጉል ፈሊጥ የፈጠረው ሰበብ ነው። ለማንም ሰው ይጣምም አይጣም፣ የራስን አገርና ጥቅም ከአደጋ ለመከላከል ወይም ራስን ከአደጋ ለማስወገድ የማንም ፈቃድ የሚጠየቅበት ምንም ምክንያት የለም። ሊኖርም አይገባም። አበቃ!

አቶ መለስ እስካሁን ያደረሰው ጥፋትና ጥቃት «ፈረንጆች ይህን ይሉኛል፤ ያንን ያመጡብኛል» እያለ በመቀባጠር እንደነበር የሚታወቅ ነው። መለስና ግብረአበሮቹ አሁን ከደረሰባቸው አደጋ ለመዳን ወይም ህይወታቸውን ለተወሰነ ጊዜ ለማሰንበት ግን፣ ወሳኙ የኢትዮጵያ ህዝብ እንጂ፣ ፈረንጆች እንዳይደሉ ዛሬ በትክክል የተገነዘቡ ለመሆናቸው ብዙ ተጨባጭ ምልክቶች አሉ። ዛሬ መለስ ዜናዊን አሜሪካኖችን ቢበዛ በሽወዳ ያጭበረብራቸው እንደሆን እንጂ የጆርጅ ቡሽንና የሽሪኮቹ ቁጣ ፈርቶ እንደተለመደው በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ይፀዳዳል ብሎ መጠርጠር አይቻልም።

አቶ መለስ ከሌሎቹ የማሌሊትና የህወሓት ጀሌዎቹ የሚለይበትና እኛንም ያስቸገረን ነገር ቢኖር፣ ሰውየው ጭንቅላቱ እንደ ዘመኑ ኮምፒዩተር ነገሮችን ሰብስቦ በፍጥነት የመብላት ብቃት ያለው እኩይ ፍጥረት መሆኑ ነው። ጠላትም ቢሆን ማንም ሰው ጠንካራ ጎን ሊኖረው የግድ ነውና። ችግራችን ያንን ጠንካራ ጎን ለምን ሁሉንም ለሚጠቅም (ያባትም የናትም አገር ለሚጠቅም) ነገር አንጠቀምበትም ከሚለው ላይ የማንስማማ መሆናችን ነው።

የመለስ ሌላውና ወሳኙ ጥንካሬ፣ ሰውየው (መለስ) በሌሎች ሰዎች ደካማ ጎን በሚገባ መጠቀም መቻሉ ነው። በዚህ ረገድ የመለስን ችሎታ መለካት የሚቻለው፣ ባረቂ የጨረጨሱና

የበሰበሱ፣ ነገር ግን የሁሉም ተንኮሎች ብቸኛ ማህደር የሆኑት፣ «አቦይ ስብሓት» የተባሉትን አዛውንት፣ እስከ ዕለተ ሞታቸው ቀን ድረስ ከጎኑ ለማሰለፍ መቻሉ ነው። በኒህ ብኩን አዛውንት ላይ ሌሎች ሰዎች ያላቸው እውቀት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ «አቦይ ስብሓት»፣ የዛሬን አያርገውና፣ የቅርብ ወንድማችን የነበሩ ስለሆኑ፣ ባንድ ቤት አብረን በማደጋችን፣ በመሰሪነታቸው ብቃት በቅርብ የምናውቃቸው እጅግ አደገኛ የሆኑ አዛውንት መሆናቸውን ብንጠቁም አይከፋም። እውነት ለመናገር፣ የመለስ ጥንካሬ ምንጩ ከየት እንደሆነ ለማጥናት የሚሻ ሰው ካለ፣ በመጀመሪያ ስብሓት ነጋን በተመለከተ በቂ እውቀት ሊኖረው ይገባል።[6]

አቶ መለስ ወደ ኤርትራ መርሾ አስመራ ያለውን መንግሥት ለማስወገድ ሲንቀሳቀስ ማንም ምንም እንደማይል ራሱ መለስ ከማንኛችንም በላይ እንደገባው በተለያየ መንገድ ተገንዝበነዋል። በመጀመሪያ «ምን ይላሉ?» የሚባሉት ኃይሎች አሁን የተጠመዱት «ዓለም አቀፍ ሽብርተኝነት» የሚሉትን ጠላታቸው ተዋግተው በህልውናቸውና በኤኮኖሚያቸው ላይ ወርዶ ያለውን እልፍ አእላፍ መከራ መቅረፍ ብቻ ነው። ማንም ለዚህ ዘመቻ እስከተባበራቸውና እስከተነጠፈላቸው ድረስ አምባገነንም ሆነ ሽፍታ አቅፈውና ተንከባክበው ከይሉኝታ ውጪ ለመደገፍ ተገደዋል። ትናንት በአምባገነንነት ተፈርጀው በበርካታ የኤኮኖሚና የዲፕሎማሲ እቀባዎች ናላቸው ሊዞር ተቃርበው የነበሩት የፓኪስታኑ ጄኔራል ሙሻረፍ «ረጅም ዕድሜ ለሼክ ኦሳማ ቢንላዲን» ይበሉና፣ ዛሬ የልዕለ ኃያላኑ የጡት ልጅ ሆነው ሊሸከሙት ከሚችሉት በላይ ክብርና ሞገስ መጎናፀፋቸውን ያጤኑታል!

ባሁኑ ጊዜ የሽብርተኞች ምሽግ ናት፣ ወይም ለወደፊቱ ትሆናለች፣ ተብላ ባሜሪካና በሸሪኮቿ መዝገበ–ስራይ በቀይ ቀለም የተመዘገበችው ስርዓተ–አልባዋ ሶማሊያ እንደሆነች በሚገባ ይታወቃል። ኢትዮጵያ ተወደደም ተጠላ በታሪኳ፣ በህዝብ ብዛቷ፣ በቆዳ ስፋቷ፣ በሃይማኖቶች ጥንካሬዋ በመሳሰሉ ምክንያቶች የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ልዕለ–ሃገር መሆኗ የተረጋገጠ ነው። ከዚህ በላይ ደግሞ ከሶማሊያ ጋር ሰፊ ድንበር የምትጋራና በሶማሊያም የራሷ ችግር ያለባት አገር ናት። በነዚህና በሌሎች ብዙ ምክንያቶች፣ ዛሬ ኢትዮጵያ ለፀረ ሽበራው ዘመቻ መሳካት ሲባል ብቻ ወርቅየ አገር ናት ተብላ የፈረንጆች ፍቱን መፈትሄ–ስራይ ሆና ተገኝታለች። ስለሆነም፣ ልዕለ–ኃያላኑ ምዕራባዊያን መለስ ዜናዊን «ማሙየ እሽሩሩ» እያሉ ሲያቆላምጡት ማየታችን አስገራሚ አይደለም።

በዚህ ለምዕራባዊያን ኃያላን መንግሥታት ህልውና እጅግ ፈታኝ በሆነ ወቅት፣ በኢትዮጵያ ምድር ከመለስ መንግሥት የተሻለ ሌላ ግብረ–ሽበራን በመዋጋት ሊተባበራቸው የሚችል የተዘጋጀ ኃይል እንደሌለ፣ ባለጉዳዮቹ ኃያላን መንግሥታት፣ በተለይ ያሜሪካው ወንድሞቻችንና እህቶቻችን እነ አቶ ጆርጅ ቡሽና የስራ ጓደኞቻቸው፣ ከኛ ይበልጥ ልቅም አድርገው ያውቁታል።

ታሪካችን እንደሚያስረዳው፣ ያፍሪካ የነፃነት አጥቢያ ኮከብና ታላቅ አብነት የሆነችው ኢትዮጵያችን፣ የፈረንጆች ቅኝ ገዥነት ከአፍሪካ ምድር ጓዙን ጠቅልሎ እንዲወጣ ባሳየችው ፀረ–ኮሎኒያሊዝም «መጥፎ» ጠባይ ምክንያት፣ ለብተናዋ ይህ ቀረው የማይባል ሤራ ሲጠነጥኑባት የኖሩት አሁን በግሎባል–ሽብርተኝነት ቁም ስቅላቸውን በማየት ላይ ያሉ ኃይሎች መሆናቸው የታወቀ ነው። ዛሬ ደግሞ፣ ዓለም ባልታሰበ ሆኔታና በሚያስደንቅ ፍጥነት ስለተገለባበጠች፣ ምስኪኗ ኢትዮጵያችን ህልውናዋ ሳይናጋ በአንድነት ፀንታና ተረጋግታ እንድትኖር ከማንም ይልቅ የሚፈልጉት እነዚያ ለዘመናት ሲቦጫጭቋት የነበሩት ኃይሎች፣ በተለይ አሜሪካና እንግሊዝ፣ መሆናቸው ራሱ አንድ ያምላክ ተአምር ነው። በቀላል አባባል፣ ከጀኔራል ሙሻረፍ በበለጠ፣ ዘንድሮ ኦሳማ ቢን ላዲን የመጣው፣ ለመለስ ዜናዊና ለስብሓት ነጋ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል!

ከዚህ አዲስ ክስተት የተነሳ፣ ፈረንጆችን አስጨንቆ የሚያወዛውዛቸው ያለ አውሎ ነፋስ ቢኖር፣ «መለስ ዜናዊ ወሳኝ ደምበኛችን ከመሆኑም ሌላ፣ እሱ ሲወድቅ ኢትዮጵያ ትበታተናለች። ኢትዮጵያ ከተበተነች ደግሞ ያፍሪካው ቀንድ ቀጣና ይታመስና የሽብርተኞች መናኸርያ ይሆናል» የሚል ነው። ለዚህም ነው፣ መለስ ወዲ ዜናዊ በኢትዮጵያ አማራጭ የለም እየተባለ ለመሽሞንሞን ስለሚፈልግ፣ በቅርቡ የግምባር ምስረታ ይከውናል ተብሎ ተስፋ የተጣለበትና፣ በቅርቡ ይሰበሰባል የተባለውን «የፖለቲካ ድርጅቶች ጉባኤ (ፖድጉ)» እንዳይሳካ፣ በኒውዮርክ ከተማ፣ በወያኔው አምባሳደር ተብየው በአብዱልመጂድ የሚመራ ብዙ ብር የሰነቀ በታኝ ቡድን ለመሰየም የተገደደው።

ለጉባኤው (ፖድጉ) ብተና የማሌሊት መንግሥታዊ መዋቅር አልበቃ ብሎ፣ «በሰላም የሚታገሉ» የሚባልላቸው የውስጥ አርበኞችና፣ በታጁሮች የሚታገዙ የዳያስፖራ ሚድያዎች እና

የመሳሰሉት ቡድኖች የስራ ድርሻቸውን አውቀው ቦታ ቦታቸውን ይዘው በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ ጉባኤው ተሳክቶ አማራጭ እንዳይገኝ ለማድረግ ስብሓት ነጋ የፈለሰፈው ቆርኪ ደግሞ፣ «ኦነግ ኢትዮጵያዊ አይደለምና፣ ኦነግ በሚገኝበት ጉባኤ መገኘት አለብን ወይስ የለብንም » የሚል ውይይት በተለያዩ ተቃዋሚ በሚመስሉ መድረኮች ላይ ቀርቦ ውይይት እንዲደረግበት አዲስ የማሌሊት መርሃ ግብር ሆኖ ይገኛል።

ስለዚህ፣ መለስ ዜናዊና ስብሓት ነጋ ወደ ኤርትራ ለሚያደርጉት ዘመቻ፣ የዓለም ህብረተ ሰብ፣ የወያኔ ጌቶች የሆኑት ምዕራባዊያን መንግሥታትና፣ ለጋሽ/አበዳሪ የረድኤት/የፋይናንስ ድርጅቶች እንዴት ይመለከቱታል ለሚለው ጥያቄ ከላይ ባጭሩ በተሰነዘሩት ሆኔታዎች ዙሪያ አስፈላጊውን ግንዛቤ ለማግኘት ከባድ አይመስለንም። አሜሪካ ደህንነቷን ለመጠበቅና ጥቅሟን ለማስከበር ወደ ኢራቅ ስትመርሽ የለዘብተኛው «አፍሪካዊ» ወንድማችን የአቶ ኮፊ አናን ድርጅት ካላስፈለጋት፣ የወንድሞቻችን ጆርጅ ቡሽና ቶኒ ብለየር ኮንዶም የሆነው መለስ ዜናዊ የራሱንና የጌቶቹን ህላዌና ጥቅም ለማስከበር ሲል ወደ ኤርትራ ሲመርሽ፣ ሞቶ የተቀበረውን የኮፊ አናን ድርጅት ሊያግደው እንደማይችል ለባለ ኮምፒተሩ ጭንቅላት ለመለስ ዜናዊ የተደበቀ ምስጢር እንዳልሆነም በትክክል ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው እንላለን።

ሌላ ሊዘነጋ የማይገባው ጉዳይ ቢኖር፣ ያቶ ኢሳያስ መንግሥት በምዕራቡ ዓለም መንግሥታትና ፖለቲከኞች ዘንድ «ያልተቀደሰ መንግሥት» ተደርጎ የሚቆጠር መሆኑ ነው። አቶ ኢሳያስ እንደነ አቶ መለስ ዜናዊ በቀላሉ ለምዕራባዊያን መንግሥታት ያለማጎብደዳቸው፣ በብዙ ፓን አፍሪካኒስቶች ዘንድ የተደነቀ መሆኑን ብናውቅም፣ በፈረንጆቹ በኩል ግን እንደ «ጭራቅ» ያስቆጠራቸው መሆኑ በግልጽ የሚታወቅ ነው።

ምዕራባዊያኑ «ጌቶቻችን» በተቻለ ሁሉ አቶ ኢሳያስን ከአስመራ ለማባረርና፣ ያቶ ኢሳያስ መንበረ–መንግሥት ለፈረንጆቹም ሆነ ለኤርትራ ጎረቤቶች ታማኝ ወዳጅ በሆነ ሰው እንዲተካ ማድረግ የምዕራባዊያኑ የቤት ስራ እንደሆነ ለማወቅ ጠንቋይ መቀለብ አያስፈልገንም። ምክንያቱም፣ ያቶ ኢሳያስ መንግሥት ራሱ፣ «ሲ.አይ.ኤ. ሊገለብጠኝ ሲያሴርብኝ፣ እጅ ከፍንጅ ይዠ አስጣልኩት» ሲል ጋዜጣዊ መግለጫ በመስጠት በይፋ የነገረን ጉዳይ ስለሆነ ነው። ስለዚህ፣ የዓለማችን አዛዥና ናዛዥ የሆኑት ፈረንጆች ራሳቸው ሊፈነቅሉት የፈለጉትንና ይህንኑ ያከሸፈባቸውን ያቶ ኢሳያስ መንግሥት፣ አቶ መለስ ዜናዊና አቶ ስብሓት ነጋ ስራውን ተረክበው ቢያስፈጽሙ፣ አበጃችሁ ከሚባሉ በቀር፣ «ለምን ይህን ታደርጋላችሁ?» ብሎ የሚቆጣቸው ኃይል ሊኖር ይችላል ብሎ መደናበር አያስፈልግም።

## ጦርነት ቢነሳ የኢትዮጵያ ህዝብስ ምን ይላል

እንግዴህ፣ የሚቀረን ቁልፍ ጥያቄ ቢኖር፣ «የኢትዮጵያ ህዝብ ምን ይላል » ወይም «ካሁን በኋላ መለስ ለሚመራው ጦርነት የኢትዮጵያ ህዝብ ድጋፉን ይሰጣል ወይስ ይነፍጋል » የሚል ብቻ ይሆናል።

መቼም ሓቁን እንናገር ከተባለ፣ አዝማቹና ዘመቻው ማን ይሁን ምን በማያስጨንቅ፣ ወደ ኤርትራ ለሚደረግ ዘመቻ፣ በኢትዮጵያ ምድር ዘማች ይታጣል የሚል ጭቅጭቅ ያለ አይመስለንም። የአፄ ኃይለ ሥላሴንና የደርግን ህይወት የቆየውን ያህል ያቆየውም ሆነ፣ ደወሉ ሲደወል ስርዓቶቹ እንደ ጉም ተነው የጠፉት፣ ከኤርትራ በሚነፍሰው አውሎ ንፋስ ምክንያት እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም። ያቶ መለስ ኮምፒተራዊ ጭንቅላትም ይህንን በሚገባ ያውቀዋል። አሁን ያለው ሆኔታ ደግሞ ከመቼውም ይበልጥ የሚያዘምትና «አንድ ሰው እስኪቀር ድረስ እንዋጋለን» የሚያሰኝ እንደሆነ መረጃዎች በትክክል ያመላክታሉ። ይህን በተመለከተ አንዳንድ ነገሮች ጠቀም አድርገን እንለፍ።

መለስና ስብሓት በትክክል ያሰመሩበት ነገር ቢኖር፣ ሻዕቢያ፣ ባብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ፣ እንደ «ጭራቅ» የሚታይ ኃይል መሆኑን ነው። በተለይ ደግሞ፣ ሻዕቢያ «ከኢትዮጵያ እንገነጠላለን» ይላሉ የሚባልላቸውን የብሄር ድርጅቶች ከግጭቱ በኋላ ከመቅፅበት ቀልቦ ማስታጠቁንና ማደራጀቱን የሚያቅለሸልሻቸው ወገኖች ቁጥር ቀላል እንዳልሆነ ያልተደበቀ ሓቅ ነው። በዚህ ሰበብ ቢያንስ ከመላው የአማራ ክልል፣ ከመላዋ ትግራይ፣ ከኢትዮጵያ አፋሮች፣ «በደቡብ ኢትዮጵያ ባሉ የብዙሃን ብሄሮች የበላይነት ተውጠን እንቀራለን» ብለው የሚሰጉና «እጣ–ፋንታችን ከአማራውና ከትግሬው ህልውና ጋር የተሳሰረ ነው» ብለው ከሚያምኑ በደቡቡ ያገራችን ክፍል የሚኖሩ የተለያዩ የንኡሳን ብሄር/ብሄረሰቦች ህዝቦች፣ ወዘተ.፣ ሻዕቢያን ለመምታት ወደ አስመራ ዝመቱ ቢባሉ፣ በአስገዳጅ ሳይሆን በሙሉ ፈቃደኝነት ብረት እንደሚያነሱና ስንቅ እንደሚያሰንቁ አይጠረጠርም። ይህንን እውነታ በተለይ ኤርትራዊያን ወገኖቻችን በሚገባ የማይገነዘቡት ከሆነ እጅግ በጣም ተዘናግተዋል ብሎ መናገር ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪ፣ በነ አቶ ህሩይ ተድላ ባይሩ አስተናጋጅነት፣ በጣም ስትራቴጂክ የሆነውና ኢትዮጵያ በማሌሊቶች አማካኝነት ያጣችውን የባህር በር ባለቤትነት መልሳ የምታረጋግጥበት ሆኔታ ካለ፣ አሁንም ቢሆን «ከአስመራ መልስ ወደ መለስ» ብሎ መከተት ያስፈልጋል የሚሉ በርካታ ሰዎች ካሁኑ ጀምሮ ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል።

የተነሳንለት ዓላማ በኤርትራና በኢትዮጵያ ህዝብ ፊት ለተደቀነው አደጋ የመፍትሄ ሃሳብ ለማፈላለግ ስለሆነ፣ መድሃኒት የሚፈልግ ሰው ደግሞ በሽታውን መደበቅ ስለማያስፈልገው፣ እኛም ባሁኑ ወቅት ችግሮች በመደበቅ የመፍትሄ ሃሳብ ማቅረብ እንደማይቻለን፣ የሚመለከታቸው ሁሉ በውል ሊገነዘቡት ይገባል። ይህ ካልኩ ዘንዳ፣ እዚህ ላይ «የኢትዮጵያ ህዝብ ምን ይላል » ከሚለው ጥያቄ ጋር በተያያዘ፣ አንድ በውል ሊሰመርበት የሚገባ ሃቅ ማንሳት እፈልጋለሁ።

## የትግራይ ወፍ ወዴት እየበረረች ናት !

የማሌሊት መሪዎች በፈጸሙት ወንጀል ሰበብ፣ ከሁሉም በላይ ከመሃል የተቀረቀሩትና፣ ከታሪክ ተጠያቂነት ራሳቸውን ለማጽዳት በመፍጨርጨር ላይ ያሉ ዜጎች ቢኖሩ፣ የትግራይ ህዝብ ልጆች ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንብንም። ሁሉም እንደሚያስታውሰው፣ ማሌሊትና ሻዕቢያ እስከተጋጩባት የመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ፣ በማሌሊት ያፍዝ አደንዝዝ ሓሺሽ ያልተሳከሩ የትግራይ ምሁራንና ከተመኞች ነበሩ ብሎ ለመናገር በእጅጉ ይከብዳል። ዛሬ ደግሞ፣ በተቃራኒው፣ «ቋራሽ ወደ ኤርትራ ካልተዘመተ ሞተን እንገኛለን» ባዮቹ፣ ትናንት ኤርትራን አትንኩብን ብለው ቁም ስቅላችን ሲያሳዩን የነበሩት ሰዎች ሆነው ተገኝተዋል።

የትግራይን ህዝብ ከታሪክ ተጠያቂነት ለማዳን ስንል፣ የኤርትራን ጉዳይ በተመለከተ፣ ትናንት እኛ ስንናገረው የነበረውን ሁሉ ቀልበው የሚያስተጋቡና፣ «ጅብ ከሄደ በኋላ ውሻ ይጮሃል» እንደሚባለው፣ እነሱ በወረቀትና በቀለም የተስማሙበትን በዱላ ካላስመላሳችሁ በቀር፣ «ከሃዲዎች» ናችሁ የሚሉንም እነዚሁ ወገኖቻችን ሆነው ተገኝተዋል። አንፈርድባቸውም! ምን ያድርጉ? ምክንያቱም፣ አገርን አሳልፎ የሸጠ ማን እንደሆነ ሁሉም በህዝብ ፊት ቀርቦ የሚዳኝበት የፍርድ ቀን በተቃረበበት ባሁኑ ወቅት፣ ሰርጉንና መልሱን ደግሰው በቋፈራና በስክስታ በክብር የሸኟዋትን ኤርትራ የምትባል ሙሽሪት፣ በጠለፋ ቢሆንም መልሰው ወደ ዘመዶቿ ቤት ለማምጣት ሊያስፈልጋቸው የግድ ነውና! አስገራሚው ትያትር ግን፣ «ከብት ባልዋለበት ኩበት መልቀም» ይቻል ይመስል፣ በዳይ ተበዳይን እየከሰሰ ጮቤ እየረገጠ መቀጠሉ ነው!

ይህንን የማነሳው ሽሙጥ ለመናገር ወድጀን አይደለም። በዚህ ሂደት፣ ዛሬ፣ ባስቸኳይ አንድ መፍትሄ ካልተገኘ በቀር፣ ሁሉም የትግራይ ምሁራንና፣ እነዚህ ምሁራን በረቀቀና ፈጣን በሆነ ዘዴ የሚቀሰቅሱት የትግራይ ህዝብ፣ «ወደ ኤርትራ ዘምቼ፣ አባቶቼ እነ አጼ ዮሐንስና እነ ራስ አሉላ አባ ነጋ የተዋደቁለትን የምፅዋ ባሕር የጨው ጠበል ጨልፌ ካልጠጣሁ ሞቼ እገኛለሁ» ብሎ የተነሳሳ መሆኑን ስለምመለከት ነው። ይህንን በራሱ፣ ኢትዮጵያ በነመለስ ተንኮል ያጣቿውን ስርትራቴጂያዊ ጥቅሞቿን በዘለቄታው ለማረጋገጥ ትቻል አትቻል ለውይይት የሚተው ሆኖ፣ በዚህ ግለት በሚቀሰቀሰው ግጭትና ጦርነት የሚደርሰው ጥፋት ግን፣ አንዱ ሌላውን በማጥፋት ወይም አብሮ በመጥፋት ከፍተኛ አሰተዋፅኦ እንዳለው ለማንም የተሰወረ አይደለም።

ማንም ይወቅለት አይወቅለት በማያስጨንቀን፣ የትግራይ ህዝብ በነ መለስ ዜናዊ የኤርትራ ጉዳይ አያያዝ ላይ ያለው ተቃውሞ፣ ገና ወያኔ አዲስ አበባ ሳይደርስና፣ ሻዕቢያ ምፅዋን እንደተቆጣጠረ፣ በመቀሌ ከተማ ባደባባይ ወጥቶ አቋሙን ግልጽ በማድረግ ያስመሰከረ ህዝብ ነው። ይቅርታ ይደረግልኝና፣ በወቅቱ አዲስ አበባ ሆኘ ሆኔታውን በመከታተል ስለነበርኩ፣ ያኔ ያገኘሁት መረጃ ባጭሩ ላካፍል።

ሻዕቢያ ምፅዋን በተቆጣጠረ ማግስት የሻዕቢያ የኪነት ቡድን ወደ መቀሌ መላኩ ይታወሳል። በወቅቱ በመቀሌ ከተማ የማሌሊት ተወካዮች የነበሩት፣ ደመኛችን ሓሰን ሺፋና የድሮ ጓዳችን አብርሃ ካሕሳይ (ማንጁስ) ነበሩ። የሻዕቢያ ኪነት ደቀመዝሙሮች ለመቀበልና ትርኢቶቻቸውን ለመመልከት የመቀሌ ህዝብ በወያኔ ታዞ በመምጣት የመቀሌን ስታዲዮም አፍ ጢሙ እስኪሞላ ድረስ ጢቅ ብሎ ሞልቷል። ትርኢቱ ሊጀመር ጥቂት ጊዜ እንደቀረው፣ ከዚህ መጣ የማይባል ብዙ ህዝብ ያካተተ ሰላማዊ ሰልፈኛ ወደ ስታዲየሙ እየተመመ ይገባና የሻዕቢያ ኪነት ትርዒቱን እንዳያሳይ ይቃወማል።

በዚህ ድንገት ደራሽ ሰላማዊ ሰልፈኛ የተደናገጡት ሓሰን ሺፋና ኣብርሃ ካሕሳይ፣ እንደዛሬ የወያኔ ጡንቻ ገና ያልደለደለ ስለነበርና በወቅቱ ዴሞክራሲ አመጣን እያሉ ሲመጻደቁ ስለነበር፣ ሓሰን ሺፋ ብዙ ያልተናገረ ሲሆን፣ ኣብርሃ ካሕሳይ ግን «የኤርትራ ህዝብ ወገናችን

መሆኑ መታወቅ አለበት፤ ሆኖም ግን አሁን በጠየቃችሁት መሠረት፣ የኪነት ቡድኑ ትርኢቱን እንዳያሳይ ወስነናል» በሚል ንግግር ኪነቱም ህዝቡም ወደየመጡበት ይመለሳሉ። የኪነቱን ቡድን መርተው የሄዱት የሻዕቢያ ባለስልጣናትና የኪነቱ ቡድን አባላትም በድንጋጤ ተውጠው ወደ ማረፊያዎቻቸው ይመለሳሉ።

ከስታድየሙ መልስ ወዲያውኑ ሓሰን ሺፋና ኣብርሃ ማንጁስ አጠቃላይ የመቀሌ ህዝብ፣ የህወሓት ሰራዊትና አባላቱ በዚያው ዕለት ሌሊትኑ ስብሰባ ጠርተው ህዝቡን ሲያነጋግሩ ያድራሉ። ኤርትራዊያኑን ባስደነቀ ሆኔታ፣ በነጋታው ጥዋት ወደ ሃያ ሺ የሚገመት ህዝብ ሰላማዊ ሰልፍ ወጥቶ «የሻዕቢያ ኪነት ትርኢቱን እንዲያቀርብልን እንፈልጋለን አለ» ተብሎ የኪነት ቡድኑ ዝግጅቱን በመቀሌ አሳይቶ፣ ከዚያም ወደ ሌሎች ከተሞች አመራ። የኪነት ቡድኑ በመቀጠል ወደ ተምቤን፣ ዓድዋና አክሱም ሄዶ በወያኔ ጥበብ ምን ዓይነት አቀባበል እንደተደረገለት ሌላ ጊዜ ብንመለስበት ይሻላል።

ይህንን ከያዝነው ጉዳይ ጋር በተያያዘ እዚህ ልጠቅሰው የፈለግሁት፣ የኤርትራን ጉዳይ በተመለከተ፣ በትግራይ ህዝብ ዘንድ ያለው ስሜትና ብሶት፣ ኢትዮጵያዊያንም ሆኑ ኤርትራዊያን በትክክል እንዲገነዘቡት ለማድረግ ወሳኝ አብነት በመሆኑ ነው። እውነት ለመናገር ከሆነ ሌላው ሁሉ ተለያይቶ ሊኖር ይችል ይሆናል። የትግራይ ህዝብና የኤርትራ ህዝብ፣ የትግራይ ህዝብና የጎንደር ህዝብ አለያይቼ አኖራለሁ የሚሉ ካሉ ግን፣ ውጤቱ እጅግ አውዳሚና አጥፊ መሆኑ ይህ ትውልድ ልብ ሊለው የሚገባ ወሳኝ ጉዳይ ነው።

ባጠቃላይ ሲገመገም፣ እነ መለስ ይህንን ህዝብ ጠንቅቀው ስለሚያውቁት፣ ለከባድ አደጋ የዳረጋቸውን የህዝብ ቁጣ ለማርገብ ሲሉ፣ ወደ አስመራ ሲዘምቱ በፈቃደኛነትም ሆነ በገፈፋ የሰው ኃይል ያጣሉ ብሎ መጠርጠር ራስን እንደማታለል የሚያስቆጥር መሆኑን ጠቁመን ወደሌላው ጉዳይ እናመራለን።

## ለጦርነቱ ገንዘብ ከየት ይመጣል

አንድ ያልተነሳ ጥያቄ ቢኖር፣ «ወደ ኤርትራ የሚደረገው ዘመቻ መጠነ ሰፊ ወጪ ስለሚጠይቅ፣ አሁን የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ በዳሸቀበት፣ በረሃብና በኤይድስ ሚሊዮኖች በሚረግፉበት ወቅት፣ ገንዘቡ ከየት ይመጣል » የሚል መሆን አለበት። መልካም ጥያቄ ስለሆነ ትንሽ ልንዳስሰው ይገባል።

በመሰረቱ የደኸየው ህዝባችን እንጂ የማሌሊት መንግሥት አይደለም። የህልውና ጉዳይ እስከሆነ ድረስ፣ እነ መለስ ለረጅም ዘመናት ያከማቹት ሃብት ለዛሬ ካልሆናቸው ለመቼውም ሊሆናቸው አይችልም። ከትግሉ ዘመን ጀምሮ፣ በኋላም መንግሥት ተሁኖ የተከማቸው ሃብት ትተውት ወደ መቃብር ሊወርዱ ማሌሊቶች ተስማምተው ወስነዋል ተብሎ ካልተነገረን በቀር!

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዘንድሮ ድርቅ የመጣው፣ የነ መለስ ህልውና እንዳይደርቅ ነው ብሎ መናገር ይቻላል። እውነት ለመናገር ያህል፣ «ዕድሜ» ለድርቅና በዚሁ ሰበብ ለሚመጣው መጠነ ሰፊ እርዳታ፣ የነ መለስ ደጋፊዎችና የፈረደበት ሰራዊት ቢያንስ ዛሬ ከመቼውም የበለጠ መልካም አቅርቦት የሚያገኝበት ሆኔታ ተፈጥሯል። ትናንት ማሌሊትን አዋልዶ እነ መለስን ለመንበረ ዙፋን ያበቃው የትግራይን ህዝብ ያደረቀውና የፈጀው ድርቅ ያስገኘው ሃብት እንደነበረ በቦታው የነበሩ ሁሉ ያውቁታል። አንዲት ፍሬ ነገር ላክል።

ማሌሊቶች «ከትግራይ ተራሮች ስር ተወሽቀን፣ የዓለም ኢምፐሪያሊዝም (ሶሺዮ ኢምፐርያሊዝም ጭምር) እናወድማለን» የሚሉትን ቅዠት ወርውረው የጣሉት፣ ያሁኑ «ጌታችን» የጆርጅ ቡሽ አባት የሆኑትና፣ የፊልም ተዋናዩ የአቶ ሮናልድ ሪገን ምክትል ፕሬዚዳንት የነበሩት ትልቅየው አቶ ቡሽ ከዋሺንግተን ከንፈው በሱዳን መሬት የከሰላ ከተማን በተሳለሙ ጊዜ ነበር። የአቶ ቡሽ ጉብኝት ሌላም ሌላም ተልእኮ የነበረው ቢሆንም፣ ዋናው ጉዳይ ግን፣ በኢትዮጵያዊያን የአሜሪካ ባለሚሎች የአክሱም ተወላጁ አቶ ገብረስላሴ (የአይ. ኤል. ኦ. I. L. O. ሰራተኛ በሽፋን)፣ እና በነ አቶ ዓብዱል አባቦራ (የዓለም ቤተክርስቲያናት ካውንስል ሰራተኛ በሽፋን) አማካሪነት፣ እነ አቶ መለስ ዜናዊ የማሌሊት ስንክሳራቸውን በውሃ አጥበው የነጻ ገበያ መዘምራን ለመሆን በመስማማታቸው፣ በድርቅ ሽፋን እርዳታ እንዲጎርፍላቸው አቶ ቡሽ በሩን ማስከፈት ስለነበረባቸው ብቻ ነው። «ዓብዱል» ብሎ የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ ማድረግ ያስፈለገው፣ ለስራው ታማኝ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ቢጠፉ አይደል!

ትልቅየው ቡሽ ያን ሁሉ ደክመው እስከ ከሰላ/ሱዳን ድረስ ተጉዘው፣ በቸርነታቸው፣ የትግራይ ህፃናትን እያቀፉ ሲስሙና ሲያጫውቱ በዓለም ቴሌቪዥን መስኮቶች መታየታቸው፣

ለማሌሊቶች እንደ ሮኬት መምጠቅ፣ ከተለያዩ ምንጮች ህሉቀ–መሳፍርት ብር በማስገኘት ዋነኛ ቀስቃሽ ምክንያት ነበር። የወንድማችን የአየርላንዱ ታዋቂ ከያኒ፣ ያቶ ቦብ ጌልዶፍ፣ «ባንድ ኤይድ» (Band Aid)፣ አሁን ያቶ መለስ ታማኝ ሰራተኛ የሆኑትን ዶክተር አሰፋ አብርሃን በትግራይ ቋሚ ወኪል አድርጎ በመሾም ያፈሰሰው መጠነ ሰፊ እርዳታ፣ የትልቅየው ያቶ ቡሽ ተልእኮ ያሳካው ትንግርተኛ የስራ ውጤት ነበር። ዶክተር አስፋ አብርሃ «የኢትርዮጵያ አሰብ–አፋር ነፃ–አውጪ ንቅናቄ (ኢአአነን)»[፯](7) አርበኛ የሆኑት የወንድማችን ያቶ በላይ አባይ ካሳ የእህት ልጅ) ናቸው።[፰](8)

አሁንም አቶ ቦብ ጌልዶፍ ፊታቸውን ወደ ኢትዮጵያ ስላዞሩ፣ «እሰየው» ብለናል!! ከእንግዲህ ላቶ መለስ የኤርትራው ዘመቻ በቂ ስንቅና ትጥቅ መሸመቻ ዶላር ሊጎርፍልን አይደል! ስምንቱ የዓለማችን ባለጸጋ አገሮች ከመሰብሰባቸው ትንሽ ቀደም ብሎ የ«ማርሻል ፕላን ለአፍሪካ» ተጣባቂ የሆኑት እውቁ የሮክ ሙዚቃ አቀንቃኝ የደጉ ያቶ ቦብ ጌልዶፍ ኢትዮጵያን ለአምስት ቀናት መጎብኘት ያቶ መለስ ጦርነት ሰርግና ምላሽ እንደነበረ ጠቅሰን ብናልፍ በቂ ነው!

በሰብአዊ እርዳታ ሽፋን ከሚጎርፈው ብር በተጨማሪ፣ ዛሬ እነ መለስ ከለጋሽና ከአበዳሪ የገንዘብ ተቋሞች የሚያገኙት ከፍተኛ ገንዘብ፣ እንኳንስ በጦርነት ሰበብ ኤኮኖሚው የዳሸቀው ሻዕቢያና፣ በተለያየ ምክንያት የተጎሳቆለቺውን ሚጢጢ ኤርትራን ቀርቶ፣ ሌላውን የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና አገሮች ለማሽብር በቂ ኃይል ነው። ይህንን ስንል፣ እነ ስብሓት ነጋ በተለያየ ቄምብል ከዘረጉት የፋይናንስና የንግድ ኢምፓየራቸው ውስጥ የተከማቸው ከፍተኛ ንዋየ–ማሌሊት ከግምጃ ቤት ሳይነካ እንደተጠበቀ ማለታችን ነው።

## የመፍትሄው ሓሳብ ጭብጥ

እንግዲህ፣ በጣም በተመጠነ አቀራረብ፣ ከዚህ በላይ ከቀረቡት የመንደርደሪያ ነጥቦች ሁለት አበይት ጭብጦች መቅሰም ይቻላል።

- **አንዱ ጭብጥ፤**

የመለስ/ስብሓት መንግሥት በምንም ምክንያት ከሻዕቢያ ጋር የድንበር መካለል እንደማያከናውንና፣ በአንፃሩ ይህ መንግሥት በቅርቡ ወደ ኤርትራ የሚገሰግስ መሆኑ ነው። ሰበቡ ከዚያ የሰፋና የጠለቀ መሆኑን ብናውቅም፣ «የድንበር ጥያቄ ያስከተለው ነው» የተባለለት የትናንቱ ግጭት ዛሬ ቦታ ስለሌለው፣ አሁን እነ መለስ ወደ ኤርትራ የሚመርሹት በኤርትራ ያለውን መንግሥት አስወግደው ራሳቸው በሚናኙት ሌላ ስርዓት ለመተካት ነው። በዚህ ሂደት አሁን ከኤርትራ ባሻገር እየተሽሎከለኩ የሚዋጉዋቸውና የሚያተራምሷቸው ተቃዋሚዎቻቸውንም ያመክናሉ ማለት ነው።

- **ሁለተኛው ጭብጥ፤**

ባንድ በኩል፣ የኤርትራው መንግሥት ካሁን በፊት ለአንዳንዶቻችን እንደገለጸውና[፱](9) ባለፈው ጊዜ «አስቸኳይ ማስጠንቀቂያ» በሚል ርእስ እኔ ባቀረብኩት ጥሪ አዘል መጣጥፍ ላይ እንዳቀረብኩት፣ ማለትም፣ አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ከአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያ ጋዜጠኛ ከእህታችን ከአዳነች ፍስሃየ ጋር ባደረገው ቃለመጠይቅ «መንግሥታት ፈለጉት አልፈለጉት በኤርትራና በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል ለወደፊት ትውልዶች የሚቀጥል የመዋሃድ ዝምድና መኖር አለበት። በፍላጎትና በምኞት ላይ ብቻ ሳንወሰን በተጨባጭ ወደ መዋሃድ ወደሚያመሩን እቅዶች መግባት አለብን።» በሚል ግልጽ እንዳደረገው፤

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ከወያኔ መንግሥት ድጋፍ የሚሰጣቸው የኤርትራው መንግሥት ተቃዋሚዎች የውህደቱን ሃሳብ እንደሚስማሙበት መረጃዎች ግልጽ እንደሚያደርጉልን ከሆነ፤

ዛሬ፣ ቢያንስ በመርሆ ደረጃ፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች በፌደራሲዮን እንዲተሳሰሩ የሚያስችል ሆኔታ የበሰለ መሆኑ ገሃድ ሆኖ ይታያል። በኛ በኩል፣ ይህ ክስተት፣ የሚጠበቅ፣ የሚደገፍና ሊሰራበት የሚገባ ክስተት ነው ብለን እናምናለን።

በኤርትራ መንግሥት በኩል ያለው አቋም ምንጩን በዚህ ጽሑፍ የግርጌ ማስታወሻ የጠቀስኩትና ካሁን በፊት በግልፅ የፃፍኩት ስለሆነ እዚህ መድገሙ አያሻም።

በአቶ ህሩይ ተድላ ባይሩ በሚመራው ግምባር በኩል ያለው አቋም ደግሞ፣ ባንድ በኩል፣ የግምባሩ ደጋፊና ያቶ ህሩይ ተድላ የቅርብ ሰው የሆነና እኔም በሰውነቱ የማከብረው፣ ለጊዜው

ስሙን መጥቀስ የማያስፈልገኝ፣ ታዋቂ ኤርትራዊ ለኔ በግል ግልጽ አድርጎልኛል። ከዚህ በበለጠ ደግሞ ያቶ ህሩይ ተድላ ቤተሰብ ከኔ ቤተሰብ ጋር የቀረበ ወዳጅነት ያለው ቤተሰብ ስለሆነ፣ የኔ የፌደራላዊ መፍትሄ አቋምም በሁሉም ዘንድ የታወቀ ስለሆነ፣ በጣም የቅርብ ዘመዴ የሆነው የትግራይ ሰው በሽምግልና መልክ ቀርቦ፣ «ያንን የምትፈልገው የፌደሬሽን መፍትሄ ማምጣት የሚቻለው ሻዕቢያን በማስወገድ እነ አቶ ህሩይን በማስተናገድ ስለሆነ፣ በዚህ መስመር እንድትሰለፍ ጥሪ ቀርቦልሃል፣ ወዘተ.» በሚል በጓሮ በኩል የማውቀውን በፊት በር መጥቶ አስረግጦልኛል።

እነዚህን ከላይ በተቻለ ጨምቄ ያቀረብኳቸው ጭብጦች በራሴና በሌሎች ዜጎች ጥረት በተገኙ ወሳኝ መረጃዎች የተመሰረቱ ናቸው። ይሁን እንጂ፣ ጉዳያችን የግል ጉዳይ ሳይሆን የህዝብ ጉዳይ ስለሆነ፣ እነዚህን ጭብጦች ህዝብ እንዲወያይባቸው ለኢትዮጵያዊያንና ለኤርትራዊያን ወገኖቻችን በታላቅ ትህትና ስናቀርብ ከፍተኛ ደስታ ይሰማናል።

የተለያዩ ሰዎች፣ በተለያየ ግንዛቤ፣ የተለያየ የመፍትሄ ሓሳብ ሊኖራቸው ይችላል። ስለሆነም፣ «የኛ ሃሳብ ካልተቀበላችሁ» ብለን ከማንም ሌላ ሰው ጋር ምንም ዓይነት ጦርነት የምናካሄድበት ምክንያት አይኖረንም። በደርጉም ዘመን የምናውቀውንና የገባንን ነገር በሰላማዊ መንገድ በማይክሮፎን፣ በብዕርና በወረቀት አማካኝነት ኡኡታችንን ከማስደመጥ በቀር፣ ዱላ አንስተን ሃሳባችንን በግድ ተቀበሉ የሚል አልወጣንም። አሁንም፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ወገኖች ስለሆንን ግን፣ መረጃዎቻችንን ለህዝብ ከማቀበል ባሻገር፣ በዜግነታችንና በተቆርቋሪነታችን ምክንያት የራሳችን የሆነ የግል የመፍትሄ ሓሳብ የማቅረብ መብቱና ግዴታው ስላለን፣ ይህንኑ ከዚህ ቀጥለን እናቀርባለን።

## የመፍትሔ ሓሳብ

ከሁሉ ነገር የከበደ ሸክም ቢኖር፣ በከባድ ምክንያት የተቃቃሩ ሁለት ወንድማማች/እህትማማች ሰዎች ለማቀራረብና ለማስማማት ተብሎ የሚደረግ ጥረት ነው። ሁለት ባዕዳን ሲጣሉ ብቻ ሳይሆን ሲገዳደሉ እንኳ፣ በመልካሙ ባህላችን መሠረት፣ የተቃረኑት ወገኖች በጋብቻ እንዲተሳሰሩ በማድረግ ጥላቻቸው ተወግዶ በደም ተሳስረውና ታርቀው በፍቅር እንዲኖሩ ሲደርግ ብዙ ጊዜ በህይወታችን የመሰከርነው ሃቅ ነው።

ዛሬ በህይወት ያለን በርካታ የትግራይ ሰዎች አብዛኛዎቻችን የተለያዩ ግጭቶች በወለዷቸው ምክንያቶች በተከሰቱ ጋብቻዎች ሳቢያ የተገኘን ሰዎች ነን። በሌላው ህብረተሰባችንም ተመሳሳይ ሆኔታ እንደሚኖር ይገመታል። በሁለት ወንድማማቾች ወይም በሁለት እህትማማቾች መካከል የሚነሳን ግጭት ከባድ የሚያደርገው ግን፣ ከዝምድናቸው የተነሳ ሁለቱን ወገኖች በጋብቻ አስተሳስሮ ለማስታረቅ ያለመቻሉ ነው።

ከኤርትራዊያን ወገኖቻችን ጋር ገጥሞን ያለው ከባድ ችግርም፣ ሁለት በድምና በስጋ አንድ በሆኑ ዘመዳሞች መሃል የተከሰተ ከባድ ግጭት ስለሆነ ብቻ ነው። አንዳንድ የራሳቸውን ታሪክ ከማወቃቸው በፊት የፈረንጅ ታሪክ ያጠኑ የኤርትራና የትግራይ ሰዎች (በኤርትራው ወገን ትንሽ ያይላል) እርስ በርስ በመጠላለፍ አንዱ ሌላውን ሲያንቋሽሽ እየተመለከትኩ እገረማለሁ። የትግራይና የኤርትራ ምሁራን፣ ኦጋዴንና ኦሮሞ ዘመዶቻችሁ ናቸው ብለው ከነሱ ጋር ባንድነት ተጣብቃችሁ መኖር አለባችሁ ብለው ወስነውብናል። በተቃራኒው ደግሞ የኤርትራ ህዝብ ለኛ ባዕድ ነው ይሉናል። እውነት ለመናገር፣ ከዚህ የከፋ የምፅአት ቀን ምን ጊዜም የሚመጣብን አይመስለንም። ትግራይ የኢትዮጵያ ማህፀን ናት ብለን ከተስማማን አይቀር፣ ለኛ የሚጨንቀን ያለው፣ በዚህ ቀመር ኤርትራዊው ሰው ከኢትዮጵያዊው ሰው ጋር በማነፃፀር ለይተን ለማወቅ የተቸገርን መሆኑ ነው።

ከዚህ የተነሳ፣ ሁለት በደምና በስጋ አንድ የሆኑትን ህዝቦች፣ ሁለቱንም የሚጎዳ አደጋ እንዳይደርስ ለማድረግ የሚቀርብ ገላጋይ የመፍትሄ ሃሳብ ለመሰንዘር፣ በጣም ሚዛናዊ መሆን እንደሚገባው የታወቀ ነው። በማንኛውም ግልግል ደግሞ አንዱ ሁሉንም ነገር ጠቅልሎ መውሰድ፣ ሌላው ደግሞ ሁሉንም ነገር ጠቅልሎ ማጣት አይኖርበትም። ይህ ሊሆን የሚችለው «ግልግል አያስፈልግምና በጡንቻ ይዋጣልን» ተብሎ፣ የተጋጩት ወገኖች ችግራቸውን በኃይል እንዲፈቱ የተተዉ እንደሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ ሁለት የተጋጩን ወገኖች በግልግል ሰላም እንዲያወርዱ ከፈለጉ፣ ከሁሉም በፊት፣ ሰጥተው ለመቀበል ቅን ሆነው መቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

ይህ የመፍትሄ ሃሳብ ካንድ መረጃ በመሰብሰብና በመመዘን ሆኔታዎችን በቅርብ ከሚከታተል ሰው የተሰነዘረ ሃሳብ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች

እርስ በርስ ከመጠላላትና፣ አወቅሁሽ ናቅሁሽ ከመባባል ተላቀው ተባብረውና ተረዳድተው ባንድነት እንዲበለጽጉ ህልም ካለው ግለሰብ ዜጋ በኩል የሚቀርብ የመፍትሄ ሓሳብ ነው። ይሁን እንጂ፣ በተላለየ ፕሮፓጋንዳ ተተብትበው፣ ለዘመናት ደም ሲፋሰሱ የነበሩና አሁንም ከዚያ አዙሪት ያልተገላገሉ ሁለት ወንድማማቾችና እህትማማቾችን የሚያስማማ የመፍትሄ ሃሳብ ማቅረብ ማለት አንጎል የሚያዞርና እጅግ ከባድ ስራ መሆኑን ለመገመት አያዳግትም።

ስለዚህ፣ ተቆርቋሪ ኢትዮጵያዊያንና ኤርትራዊያን ዜጎች ይህንን የኔን የመፍትሄ ሃሳብ ያንድ ግለሰብ ሃሳብ እንደመሆኑ መጠን፣ በጎደለው እያስተካከሉና፣ አዲስ ሃሳብም በመጨመር እንዲያሻሽሉትና እንዲያዳብሩት በታላቅ አክብሮት እጋብዛለሁ። ምናልባት ይህንን የመፍትሄ ሓሳብ «የደንቆሮ ሃሳብ ነው» የሚባል ከሆነ፣ ሃሳቡን እንዳለ ወይም በከፊል ከመወርወር በቀር፣ ጠብና ጉጥጫ ምንም እንደማያስፈልገንና፣ በዚች ባንዲት ሰብአዊ ሃሳብ ተለያይተን በሌሎች በሚያስማሙን በርካታ ጉዳዮች እየሰራን ተከባብረን በሰላም መኖር እንደሚቻል ከወዲሁ ለማስታወስ እወዳለሁ።

የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ችግር ምንጩ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተ.መ.ድ.) ተሳትፎ የተበየነውን የኢትዮጵያና የኤርትራ ፌደራላዊ አስተዳደር፣ እንበለ ተ.መ.ድ. ተሳትፎ፣ በንጉሠ ነገሥቱ ፍላጎት ብቻ፣ መፍረሱ እንደሆነ ካሁን በፊት በዝርዝር የጻፍኩለት ነው።[10] በኢትዮጵያው ወገን፣ ተወደደም ተጠላ፣ «ፌደረሽኑ በኤርትራ ህዝብ በጎ ፈቃድና ስምምነት ነው የፈረሰው» እየተባለ የሚነዛው ጫጫታ፣ ተራ ፍሬከርስኪ ከመሆን ያለፈ ሌላ፣ በህዝቦች መካከል በቀጣይነት መተማመን እንዲፈጠር በማድረግ ረገድ ምንም ፋይዳና በጎ አስተዋጽኦ የለውም። ባጭሩ ለመግለጽ ያህል፣ <u>«ፌደረሽኑ በኤርትራ ህዝብ ፈቃድና ፍላጎት መሠረት የፈረሰው፣ ልክ ሬፈረንደሙ በኤርትራ ህዝብ ፈቃድና ፍላጎት መሠረት በፀደቀበት ሆኔታ ነው»</u> ብሎ መደምደም ይበቃል።

ስለዚህ፣ ኢትዮጵያ ኤርትራን እንደ ትግራይ ወይም እንደ ጎንደር ሌላ አንዷት የኢትዮጵያ «ጠቅላይ ግዛት» ናት ስትል ጊዜዋን በከንቱ ማባከን የለባትም። ዛሬ እንኳንና ፀሓይ የሞቀው የኤርትራ ጉዳይ ቀርቶ፣ ለኦሮሞ፣ ለትግራይ፣ ለአማራም ሆነ ለሌላው ክፍል፣ ከፌደራላዊ አስተዳደር በቀር ሌላ አማራጭ የለም። ስለራሴ «ክልል» ለመናገር ከተፈቀደልኝ፣ እኔ እስከማውቀው ድረስ፣ ካሁን ወዲያ በትግራይ መሬት ባማርኛ ወይም በሌላ ቋንቋ ችሎት የሚቀመጥ ፍርድ ቤት፣ ክስ የሚመሰርት ፖሊስ ጣቢያ፣ ፊደል የሚያስቀጥር ተማሪ ቤት እንደ በፊቱ ይኖራል ብሎ መገመት ወይም መጠበቅ ራስን ማታለል ብቻ ይሆናል። የኤርትራ ህዝብ የራሱን ቋንቋዎች ወርውሮ አማርኛ ካልተናገረ ብለን የተጓዝንበት መንገድ ያስከፈለን ዋጋ ተመኑ እጅግ ከፍተኛ መሆኑ የትናንትናው ትውስታችን ነው። ዛሬ ደግሞ ሆኔታው ከዚህ የባሰ ስለሆነ፣ ኃይልን ተጠቅሞ ኤርትራን የራሴ ጠቅላይ ግዛት አደርጋለሁ የሚል ካለ ጤነኛ አዕምሮ የሌለው ሰው ብቻ መሆን አለበት።

ያሁኑ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ቀሳፊ ግጭት ምንጭ ደግሞ፣ የኤርትራን ነፃነት አስገኘ የተባለለት የትናንቱ የኤርትራ ሬፌረንደም አፈጻጸም ህጋዊነትና ተቀባይነት የሌለው መሆኑ ነው። ይህንንም በተመለከተ ካሁን በፊት በዝርዝር የጻፍኩትን መመልከት ይጠቅማል።(10)

ማንም ንፁህ አዕምሮ ያለው ሰው (ኤርትራዊያኖች ጭምር) እንደሚረዱት፣ ግማሽ ኤርትራዊ የሆነውና ለኤርትራ ነፃነት ሸንጡን ገትሮ የታገለው መለስ ዜናዊ ባዲስ አበባ ቤተመንግሥት ባይኮፈስ ኖሮ፣ ሻዕቢያ በጊዜያዊ የኃይል ሚዛን ምክንያት ኤርትራን ለተወሰነ ጊዜ ሊቆጣጠር ይችል እንደሆን እንጂ፣ የኤርትራን ባንዴራ በተባበሩት መንግሥታት ጓሮ ለማውለብለብ ይችል ነበር ብሎ ማመን ቀርቶ ማለም አይቻልም። በጣም የሚያሳዝነውና ሁሌም አደጋ የሚያስከትለው ደግሞ፣ መለስ ዜናዊ በወቅቱ ህገመንግሥታዊ ያልነበረውን መብት ለሻዕቢያ የቸረው፣ በተጭበረበረ መንገድ ቢሆንም እንኳ፣ ገና ፓርላማ ኖሮ የህዝብ ውክልና ሳይሰጠው በመሆኑ ነው። ስለሆነም፣ ከዚህ በፊት እንደፃፍኩት፣ ካሁን በፊት የተካሄደው ሬፈረንደም ህጋዊ ባለመሆኑ፣ ለኤርትራ ህዝቦችም ሆነ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ዘላቂነት ያለው ሰላምና ብልፅግና ያመጣል ብሎ ማሰብ አይቻልም።

የሬፈረንደሙ አፈፃፀም የኢትዮጵያ ህዝብ ተሳትፎ ያልነበረው፣ ከሻዕቢያ በቀር ሌሎች የኤርትራ የፖለቲካ ኃይሎች ያልተሳተፉበት ስለሆነ፣ ምንም እንኳ የኤርትራ ህዝብ ትግል ምንነትና ይዘት ከመቼውም ይበልጥ ባሁኑ ወቅት በኢትዮጵያዊኖች ዘንድ በቂ ግንዛቤ ያስገኘ ቢሆንም፣ አሁንም ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም ዓይነት ትስስር ሳይኖራት በሰላም ትቀጥላለች ብሎ ማሰብ ግን በጣም አሳሳቢ ነው። ሌላ ሌላውን እንተውና፣ መለስ በኢትዮጵያ ቤተመንግሥት በማይኖርባት የመጀመሪያዋ ደቂቃ፣ ኢትዮጵያዊያኖች በተለያየ ሰበብና ሽፋን ወደ ኤርትራ

መዝመታቸው አይቀሬ ነው። ክፋቱ ግን፣ የመለስ ፍላጎት ከሌሎች ኢትዮጵያዊያኖች ፍላጎት ጋር ፈፅሞ የተለየ ቢሆንም፣ መለስ በቤተመንግሥታችን እያለም ቢሆን ወደ ኤርትራ የሚደረገው ዘመቻ ተቀነባብሮ የተዘጋጀ መሆኑን ከላይ የቀረበው ዝርዝር በሚገባ የሚያስገነዝበን መሆኑ ነው። ስለዚህም ነው፣ በዚህም ተባለ በዚያ፣ አንድ መፍትሄ ካልተገኘ በቀር፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች ወደዱም ጠሉ እየደሙ መቀጠላቸው የማይታጠፍ ሓቅ ነው የምንለው!

አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት፣ እኛ «መለስ ዜናዊ የሚሰራው ለኤርትራ ብቻ ነው» ስንል፣ በኤርትራዊ ደሙ እንዳልሆነ ሁሉም እንዲገነዘበው ያስፈልጋል። ዘርአይ ደረስ፣ ሞገስ አሰገዶም፣ አውዓሎምና አብርሃ ዶበጭ ጀግኖች ኢትዮጵያዊያኖች ናቸው የምንለውም በትውልዳቸው አማሮች ወይም ጉራሮች ስለሆኑ አይደለም። ዛሬ እንደምንታዘበው፣ መለስ እንዳይወድቅባቸው በመርበትበት ላይ ያሉት የትግራይ ኢትዮጵያዊያኖች ሳይሆኑ ኤርትራዊያኖች መሆናቸውም በቂ ምስክር ነው። መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ቤተመንግሥት በማይኖርበት ወቅት፣ ያለ ምንም ጥርጥር፣ ለኤርትራ ህዝብ አዲስ የሬፈረንደም ግብዣ እንደሚቀርብለት የታወቀ ጉዳይ ነው። ለዚያውም ባዲስ አበባ ጤነኛ መንግሥት ቢቆም ነው። ይህ የማይሆነው፣ ኢትዮጵያ የምታባል ፍጥረት በተተለመላት ማሌሊታዊ መርሃ–ግብር መሠረት ተሸራርፋ ከቀበና ወንዝ የተወረወረች እንደሆነ ብቻ ነው።

ሓቁ ይህ እስከሆነ ድረስ፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች አስከፌ መከራ ማስወገድ የሚቻለው፣ ሁለቱም ህዝቦች ፅንፍ አቋማቸውን ወርውረው፣ በኃይልና በመናናቅ ሳይሆን በፍቅር፣ በመከባበር፣ በመተሳሰብና በንፁህ ህሊናቸው ከመካከለኛ መገናኛ መሬት (middle ground) ላይ ሲገናኙና ሲመካከሩ ብቻ ነው።

የኔና ከኔ ጋር የሚመክሩ በርካታ ኢትዮጵያዊያኖችና ኤርትራዊያኖች የመፍትሄ ሓሳብና ማዕከላዊው መንገድ፣ ማንም እየተነሳ ሊንደው የማይችልና፣ አንዱ በሌላው የውስጥ ጉዳዮች ገብቶ በማያምስበት ህግና ደንብ መሠረት የተጠናከረና በዓለም ህብረተ ሰብ ዘንድ ዋስትና ያለው፣ ለሁሉም አስተማማኝ የሚሆንና ለተቀሩት የኢትዮጵያ ህዝቦችም አብነት ያለው **ፌደራላዊ ትስስር** ብቻ ነው።

ይህ ፌደራላዊ ትስስር በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍላተ ሃገሮች ከሚኖር ፌዴራላዊ ትስስር በእጅጉ የላቀ እንደሚሆን ለመገመት አያዳግትም። በኢትዮጵያና በኤርትራ ቤተሰባዊና ተፈጥሮአዊ ትስስር ያለ ጉልህ ጉድለት ምንድን ነው ተብሎ ቢጠየቅ፣ «መተማመን የሚባል ነገር ተሟጦ ደርቋል» ብሎ መመለስ ይቻላል። አሁን አርጅተን በሞት አፋፍ ላይ ያለን የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ልጆች ሰርተነው ልናልፍ የሚገባ ታላቅ ታሪካዊ ስራ ቢኖር፣ በህዝቦቻችን መካከል ሰፍኖ ያለውን ያለመተማመንና ያለመከባበር አስወግደን ማለፍን ነው።

እግረመንገዳችን ትንሽ ሃሳብ ጣል ለማድረግ ከተፈለገ፣ ይህንን የመተማመን በር ለመክፈት ያህል፣ ኢትዮጵያና ኤርትራ በፌደራሲዮን ሲተሳሰሩ፣ ኤርትራ የራሷ ገንዘብ፣ የራሷ ፓስፖርት፣ የራሷ ባንዴራ እንደያዘች መተሳሰር ትችላለች የሚል እምነት አለን። በተጨማሪም በፌደራሉ መንግሥት ያገር መከላከያ የእዝ ሰንሰለት ስር ሆኖ፣ ኤርትራ የራሷ የመከላከያ ኃይል እንዲኖራት ማድረግ የሚቻልም ሊሆን ይችላል። እነዚህ ሁሉ ግን፣ የጠፋውን መተማመን ለማስወገድ ሲባል የሚወሰዱ የቅድሚያ እርምጃዎች እንጂ፣ ህዝቦች ፓስፖርት ሳያስፈልጋቸው፣ ድንበር ሳያግዳቸው፣ ማንም «ማን ነህ » ሳይላቸው ሲገበያዩ፣ ለቅሶ ሲደራረሱ፣ ሰርግ ሲገባበዙ ባጭር ሂደት ራሱ በተፈጥሮ ከስሞ የሚጠፋ ጉዳይ ነው።

የዚህ ትስስር አፈፃፀም ሰፊና ጥልቅ ከመሆኑ ባሻገር፣ በቂ ጊዜና ውይይት የሚጠይቅ መሆኑ አይካድም። ዋናው ቁምነገር ግን፣ ጉዳዩ እልባትና ውሳኔ ማግኘት ያለበት የህዝብ ህጋዊ ውክልና በሌላቸው ድርጅቶች ወይም መንግሥታት መካከል በሚደረግ ስምምነት አማካኝነት ሳይሆን፣ በህዝብ ፍላጎትና ፈቃድ ብቻ መሆን አለበት። በሁለቱም ወገን ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችና የተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት በዚህ መርሆ ከተግባቡ፣ መርሆውን ለማስፈፀም የዓለም ህብረተሰብ፣ በኃይላቸውና በሃብታቸው ምክንያት የዓለሙን ህብረተሰብን እንደፈቀዱ የማድረግ «መብት» ያላቸውና፣ በዚህ እኛ በምንኖርበት ቀጣና ሰላም ሲነግስ የራሳቸው ጥቅም ለማስተናገድ ምቹ ሆኔታ የሚፈጠርላቸው የምዕራባዊያን መንግሥታት ጭምር ለመርሆው ግብ መምታት ያልተቆጠበ ድጋፍና ተፅእኖ እንደሚያደርጉልን ሳይታለም የተፈታ ሃቅ ነው።

ይህንን መርሆ ለማስፈፀም በሚኖረው ሂደት፣ በኢትዮጵያም ሆነ በኤርትራ ያሉ ህዝቦች ማንም ሊቀለብሰው የማይቻለው የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ስልጣን የመወሰን መብታቸው በተጠናከረ መንገድ እውን የሚሆንበት መልካም አጋጣሚ ይኖራል ማለት ነው። ይህንን መርሆ ተቀባይነት ለማግኘትም ሆነ ውድቅ ለማድረግ ግን ብቸኛው አማራጭ መንገድ፣ ከህዝቦች ጀርባ

በሚደረግ የገበጣ ጨዋታ ሳይሆን፣ ህዝብ ማንንም ሳይፈራ ስለራሱ ራሱ ሲወስን ብቻ ነው። ከዚህ ውጪ የሚኖር አፈፃፀም አዎንታዊ ውጤት አይኖረውም ብቻ ሳይሆን፣ ሰዓቱን ጠብቆ በሚፈነዳ ፈንጂ ላይ ተቀምጦ አብሮ ለመፈንዳት እንደመጠባበቅ የሚያስቆጥር ቁምር ነው።

በማሌሊትና ሻዕቢያ ግጭት ምክንያት ሁለቱም ወንድማማች ህዝቦች እልፍ አእላፍ መስዋዕትነት ለመክፈል የተገደድነው፣ የወያኔና የሻዕቢያ ግኑኝነት በህዝብ ፈቃድ ያልተመሰረተና ሁለቱም ኃይሎች  ከህዝቦቻቸው ጀርባ ሆነው ያድቦለቦሉት ባዶ ግኑኝነት ስለነበር ብቻ ነው። እንዲያውም ግኑኝነቱ የህዝቦች እምነትና ተሳትፎ ነበረው ሊባልለት ቀርቶ፣ የሁለት ኃይሎችም ሳይሆን፣ የሁለት መሪዎች ግኑኝነት ብቻ ነበር ብሎ በግልጽ መናገር ይቻላል። ግኑኝነቱ በድቡሽት ላይ እንደገነባ ቤት ስልነበረ፣ ማንም ደካማ ከመሬት ብድግ ብሎ ተነስቶ፣ በቀላል ግፊትና ወጪ፣ ሊደረማምሰው ስለቻለ፣ አክሳሪው ውጤት ራሱ በቂ ምስክር ነው።

ይህ ያልተቀደሰ ግኑኝነት ህዝቦቻንን ከማድማቱ ባሻገር፣ ግጭቱ የሁለቱን አመራር ቁምር አበጣብጧል። የሻዕቢያና የወያኔ ክፍፍል በባህርዩ ተመሳሳይነት ያለው ነው። የህዝባቸው ቁጣ ያስደነገጣቸው የህወሓት መሪዎች እነ ተወልደ ወልደማርያም፣ ገብሩ አስራት ወዘተ. አቶ መለስን ገና ሰዓቱ ሳይደወል ሸሽተውታል። በሻዕቢያው በኩል ባመራሩ የነበሩት እነ ጴጥሮስ ሰለሞን፣ ሸሪፎ፣ ወዘተ. ካቶ ኢሳያስ ካምፕ ፈጥነው ያፈነገጡትም እንደዚሁ በህዝባቸው ፊት ከተጠያቂነት ለማምለጥ ሲሉ ነው። ልዩነቱ፣ አሁን እንደምንመለከተው፣ የህወሓቶቹ «ኮብላዮች» ከድንበር ውሳኔው በኋላ ህዝባዊ ተአማኒነት ማትረፋቸው ሲሆን፣ በአንፃሩ ደግሞ የሻዕቢያዎቹ «ኮብላዮች» በውሳኔው ውጤት ምንም ያላተረፉ ምናልባትም የከሰሩ መሆናቸው ነው።

ይህንን አላስፈላጊ ብጥብጥ አንድ የሚያረጋግጥልን ነገር ቢኖር፣ የህዝብ ውክልና የሌላቸውና የህዝባቸውን ጉዳይ ከህዝባቸው ጀርባ ተደብቀው እንደፈለጉ የሚወስኑ ስርዓቶች፣ አንድ ችግር በተፈጠረ ቁጥር እርስ በርሳቸው ከመበላላትና ከመጠፋፋት ሊያመልጡ የማይችሉ መሆኑን ነው። በቦታው ተገኝተን እንደመሰከርነው፣ ፕሬዚዴንት መንግሥቱ በመጨረሻ ሰዓት እንደተወጠሩ፣ ከሁሉ በፊት የከዷቸው በተለያየ የኃላፊነት እርከን ተመድበው ይሰሩ የነበሩ የፓርቲያቸው፣ የመንግሥታቸውና፣ የደህንነቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ነበሩ።

አቶ መለስ ሳይመረጥና በተጭበረበረ ምርጫ ተመርጫለሁ በሚል፣ አቶ ኢሳያስ ደግሞ ምንም ምርጫ ሳይኖር ያጠናቀቋቸው ስራዎች ሁሉ ህዝባዊነትና ዘላቂነት አላቸው ብሎ መጠበቅ አደገኛ ነው። የኤርትራ ጉዳይ «በሰላማዊ መንገድና በዴሞክራሲያዊ አግባብ» ተጠናቋል በተባልን ማግስት፣ ያተረፍነው ሰላምና ዴሞክራሲ ሳይሆን ጦርነትና እልቂት፣ መፈናቀልና መጠላላት፣ ውድቀትና በረሃብ መገረፍ ሊሆን የቻለውም በዚህ ምክንያት ነው። ጦርነቱ የጠቀመው ክፍል ቢኖር፣ ሁለቱም ህዝባዊ ውክልና የሌላቸው ስርዓቶች የስልጣን ዘመናቸው እንዲራዘም ያስቻላቸው መሆኑ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ ሁለቱም ስርዓቶች፣ በተለያየ ደረጃ ቢሆንም ቅሉ፣ ዛሬ በህዝባቸው ዘንድ ያላቸው ተአማኒነት እየተሟጠጠ ለመሆኑ በግልጽ መመልከት ይቻላል።

እውነት ለመናገር ያህል፣ መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ያለው ተኣማኒነት፣ በፈለገው መንገድ ሊጠገን በማይችል ሆኔታ፣ ፈጽሞ የተሟጠጠ ነው። በአንጻራዊ መልኩ፣ ምንም እንኳ አሳሳቢ ተቃዋሚ የለውም ለማለት ባይቻልም፣ አቶ ኢሳያስ፣ በሚገባ ከሰራበትና የህዝቡን ብሶት በትክክል ለማዳመጥ ከቻለ፣ ተቃዋሚዎችን ካስተናገደ፣ የነጻውን ፕሬስ ከፈቀደ፣ እስረኞችን ከለቀቀና ከኢትዮጵያ ህዝብ ልጆች ጋር በሽወዳ ሳይሆን በጥሞና መመካከር ከቻለ፣ ከመለስ ዜናዊ ይልቅ በላቀ ሆኔታ አቶ ኢሳያስ ከራሱ ህዝቡ ጋር ካለው ግንኙነት አኳያ መልካም ዕድል አለው ብሎ መናገር ይቻላል።

በኤርትራ ህዝብ የውስጥ ጉዳይ ገብተን የመፈትፈት መብቱም ግዴታውም ባይኖረንም፣ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ህዝቦች ሰላምና ብልጽግና ካለን ህልምና፣ ከኤርትራ መንግሥትም ጋር ካለን ግኑኝነት አኳያ፣ ካሁን በፊት በተለያየ መንገድ እንደሞከርነው ሁሉ፣ አሁንም በቅንነትና በወገናዊነት የምንለግሰው ምክር አለን።

የኤርትራ መንግሥት ከራሱ አመራር ያፈነገጡበት የቀድሞ የራሱ ባለስልጣኖችና የግል ፕሬሱ ጋዜጠኞች በማረፊያ ቤት እንዲቆዩ ያደረገበት ምክንያት በጥሞና ተከታትለነዋል። ሚዛናዊ አስተያየት ለመስጠት ያህል፣ በማረፊያ ቤት የሚገኙት ኤርትራዊያን የዴሞክራሲ መብት እንዲረጋገጥ ሲሉ ብቻ ጥያቄ አቅርበው ከሆነ፣ ይህ እርምጃ በራሱ የኤርትራ ህዝብ ጠላቶች ያደርጋቸዋል ብሎ ለመናገር አይቻልም። የኤርትራ ህዝብ ለረጅም ዘመናት ከከፈለው መስዋዕትነት አኳያ፣ ዴሞክራሲ ቢያንሰው እንጂ አይበዛበትምና። ያፈነገጡት ባለስልጣኖችም ሆኑ የግል ፕሬሱ ጋዜጠኞች ከፍተኛ ስህተት እርምጃውን የወሰዱበት ወቅት አጉል ወቅት መሆኑ ነው። ትንሽ እናብራራው።

ያፈነገጡት ባለስልጣኖችም ሆኑ ጋዜጠኞቹ አቶ ኢሳያስን የሚያውቁት፣ መለስ ዜናዊ ከባድመ ባሻገር በጣም ዘልቆ፣ ከግጭቱ መከሰት ጋር ምንም ግኑኝነት የሌላቸውን ባረንቱንና ተሰነይን ከወረረ በኋላ አይመስለንም። እስከ ግጭቱ ድረስ አቶ ኢሳያስ በሳሕል ተራራዎች ከነበረው ማንነት በተለየ አስመራ ስለገባ ብቻ ያሳየው ያሰራር ለውጥም ይሁን ተክለሰውነት አለ ብሎ መናገርም አይቻልም። «ከማሌሊት ጋር የተፈጠረው ግጭት ባቶ ኢሳያስ አምባገነንነትና ጠብ ጫሪነት የተከሰተ ስለሆነ አቶ ኢሳያስ አስመራ ሲደርስ የሳሕል ማንነቱን ለውጧል» የሚባል ከሆነም፣ ግጭቱ የተከሰተበት ምክንያት ጠንቅቀን ስለምናውቅ፣ አባባሉን ልንቀበለው አንችልም። ያም ሆነ ይህ፣ በማረፊያ ቤት ያሉት ሰዎች ራሳቸውን በፍርድ ሸንጎ ለመከላከል ሳይችሉ ላልተወሰነ ጊዜ ታፍነው፣ ከቤተሰቦቻቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር እንዳይገናኙ ተከልክለው፣ ወዘተ. ይቀጥሉ የሚል እምነት ጤነኛ እምነት አይሆንም።

በርግጥ ይህንን በተመለከተ የኤርትራ መንግሥት ያለበትን ችግር እንረዳለን። እንደሚታወቀው፣ የኤርትራ መንግሥት ሰዎቹን የሚከሰው በአገር ክህደት እንደሆነና «በጦርነቱ መሃል አንዳንዶቹ ከመለስ ዜናዊ መንግሥት ጋር ግንኙነት በመፈጠር የኤርትራን ፕሬዚደንት ለማስወገድ ሞክረዋል» የሚል ነው። ለዚህም የኤርትራ መንግሥት ማስረጃ አለኝ ባይ ነው። ይህ ክስ ካገር ክህደትና ህዝብን ከማበጣበጥ በላይ፣ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ነው የሚሉም አሉ።

እንግዲህ የኤርትራ መንግሥት ችግር አለው የምንለው፣ ማስረጃ ካለ ሰዎቹን ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ እንዲያገኙ ማድረግ ያለመቻሉ ነው። ሰዎቹ የተከሰሱት ባገር ክህደትና በመንግሥት ግልበጣ (ያውም ሲ.አይ.ኤ.'ን ጨምሮ ከውጭ ኃይሎች ጋር በመመሳጠር፣) ከሆነ ደግሞ፣ የፍርድ ቤቱ ሂደት በሰዎቹ ህይወት ላይ የሚያስከትለው አበሳ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። አቶ ኢሳያስ፣ ፈረንጆቹን ለመብላት እንደ አቶ መለስ ዜናዊ «ዴሞክራት» ይሁኑ ከተባለም፣ የራሳቸው ዳኛ ሰይመው ተከሳሾቹን ባደባባይ አስፈርደው ባደባባይ ለመስቀል የሚቸግር አይመስለንም።

ከቅርብ ክትትል እንደምንረዳው የኤርትራ መንግሥት በሰዎቹ ተግባር እጅግ ያዘነ ቢሆንም፣ ሰዎቹን ከዚች ዓለም ለማጥፋት ግን የሚፈልግ አይመስለንም። ይህ በጎ ገፅታ ያለውና እጅግ የተቀደሰ ሃሳብ ነው። የድንበሩ ጉዳይ ሲጠናቀቅና መረጋጋት ሲፈጠር፣ የሰዎቹም ጉዳይ ሰብአዊነት ባልጎደለው መንገድ እልባት እንዲያገኝ በመንግሥት በኩል የታሰበ ይመስለናል።

አሁን የድንበር ውሳኔው ጠቀመም አልጠቀመ፣ ድንበሩ ተከለለም አልተከለለ፣ ግልፅ ሆኖ መጥቷል። ህዝቡም ብዙ ነገር አውቋል። የሰዎቹ በማረፊያ ቤት መቆየት ደግሞ በራሱ መረጋጋትን አያመጣም። መንግሥት ደግሞ ከግለ ሰብ የበለጠ ሆደ ሰፊና ይቅር ባይ መሆን ስለሚገባው፣ ሰዎቹን ፍርድ ቤት አቅርቦ ማስፈረድ አደገኛነቱ ቢገባንም፣ እንዲሁ መቀጠልም አሉታዊ አስተዋፅኦ ከሚኖረው በቀር ሌላ ምንም ፋይዳ የለውም። ኤርትራ ደግሞ በዓለማችን ውስጥ ልዩ ደሴት ሆና የተከሰሱትን ሰዎች ፍርድ ቤት ሳታቀርብ አሻፈረኝ ብትል፣ ለጠላቶቿ ድንጋይ ከማቀበል በቀር ሌላ ጠቀሜታ የለውም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆች የተቃቃሩትን የኤርትራ ህዝብ ልጆች አስታርቆ፣ ለኤርትራና ለኢትዮጵያ ህዝቦች ሁለገብ ሰላም በመስራት፣ ለኤርትራ ህዝብ ያለውን ወገናዊነት ከማስመስከር የበለጠ ሌላ ስራ የላቸውም። ማንም ፈረንጅ ደግሞ ባፍሪካውያን የውስጥ ጉዳይ ገብቶ ችግር ከመፍጠር በቀር፣ ለአፍሪካውያን ሰላምና ብልጽግና ያስባል ብለን ስለማናምን፣ የኤርትራ መንግሥት መልካም ፈቃዱ ሆኖ፣ እኛ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቹ ለሰላም ሲባል የሽምግልና ሚና እንድንጫወት እንዲተባበረን በምንሳሳለት የኤርትራ ህዝብና በራሳችን ስም በአክብሮት እናስታውሳለን።

ይህንን የሰላም መልእክታችን ለኤርትራ መንግሥት ካስተላለፍን በኋላ፣ ሌሎች ይህ የመፍትሄ ሃሳብ ለሚመለከታቸው ኤርትራዊያንና ኢትዮጵያዊያንም የተለየ መልእክት ለማቅረብ እንወዳለን።

## ከማሌሊት ጋር ዝምድና ላላቸው
## የኤርትራ ተቃዋሚ ኃይሎች የምናስተላልፈው መልእክት

የማሌሊትና የኤርትራ ግጭት በተከሰተ ማግስት፣ በቅድሚያ የተለያዩ የኤርትራ ተቃዋሚዎች ወደ አዲስ አበባ ዘልቀዋል። ከዚያ ለጥቆ ደግሞ የተለያዩ የኢትዮጵያ የተቃዋሚ

ድርጅቶች ወደ አስመራ ዘልቀዋል። በመሠረቱ፣ ይህ እርምጃ፣ በፖለቲካ ስራ ሲታይ ባህርያዊና የተለመደ ስለሆነ፣ ምንም እንከን የለውም። እንከን የሚኖረው ተቃዋሚዎች በስልት ምክንያት የሚያስተናግዳቸውን መንግሥት መሳሪያና አሽከር የሆኑ እንደሆነ ነው።

ዛሬ ወደ ኤርትራ የምንመላለሰው ኢትዮጵያዊያን፣ ገና ለገና የኤርትራ መንግሥት ይረዳናል ስንል የዚያ መንግሥት አሽከሮችና ጉዳይ አስፈጻሚዎች እንሁን ብንል፣ በመጀመሪያ የምንጋጨው ከኤርትራ ህዝብ ልጆች ጋር ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም፣ ተወደደም ተጠላ፣ ያስመራው መንግሥት ብዙ ጠላቶች እንዳሉት ስለምናውቅ ነው። በተመሳሳዩ ወደ ማሌሊት ኢትዮጵያ የሚመላለሱት ኤርትራዊያን የመለስና የስብሓት ነጋ አሽከሮችና ጉዳይ ፈጻሚዎች ለመሆን ከፈቀዱ፣ ዋጋውን የሚያስከፍላቸው እርር ኩምትር ያለው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሚሆን ማስታወሱ ተገቢና ግዴታችንም ነው።

አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ወደ ኤርትራ ሲገሰግሱ፣ «የጠላቴ ጠላት፣ ወዳጄ ነው» ከሚል ጊዜያዊ ስልት በመነሳት እንደሆነ የሚካድ አይደለም። አንዳንዶቻችን ግን፣ ከዚች ካፍንጫችን ስር ርቃ የማትሄድ ጊዜያዊ ታክቲክ ተነስተን ሳይሆን፣ ከዚህ ስልት በጣም የራቀ ግብ ላለው ስትራቴጂያዊ ዓላማ መሆኑን የሚመለከታቸው ሁሉ እንዲረዱልን እንፈልጋለን። ለስልታዊ ጥቅማጥቅሞች ስንልም፣ ጠቃሚ ጊዜያችንን ማባከን አንፈልግም። በኤርትራ ተቃዋሚዎች ዘንድም ተመሳሳይ አቋም እንዲኖር ምኞታችን የፀና ነው።

በኛ በኩል፣ ለኤርትራና ለኢትዮጵያ ህዝቦች ስትራቴጂያዊ ጥቅም ስንል፣ የወያኔ መሪዎችን ያዋለደው ሻዕቢያን፣ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ እንደ ጭራቅ እስከሚታይ ድረስ እንደተዋጋነው ሁሉም የሚያውቀው ነው። ውጤቱም በገሃድ የታየ ስለሆነ ሌላ ማብራሪያ የሚያስፈልገው አይመስለንም። በአንጻሩ ግን፣ ምንም እንኳ ብዙዎቹ የኤርትራ ተቃዋሚዎች ቀደም ሲል በማሌሊት መሪዎች ብዙ በደል የደረሰባቸው ቢሆንም፣ ወያኔን በመዋጋት ያሳዩት የተግባር እንቅስቃሴ ግን የለም። በተግባር ያየነው ካለ፣ እኛ ለራሳችን መሽሎኪያ በቀደድነው ቀዳዳ ሾልከው፣ የኤርትራ ተቃዋሚዎች ቀድመውን ወደ አዲስ አበባ ሲመርሹ ብቻ ነው።

የኢትዮጵያና የኤርትራ ዘመነኛ ፖለቲከኞች (ተቃዋሚዎችም ጭምር)፣ ራሳቸውን ለመጥቀም ሲሉ፣ እነሱ የማይሞቱትን ሞት ደግሰው ትግላችንን ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ እንዲያመራ በማድረግ፣ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ምስኪን የህዝብ ልጆች ላልረባ ነገር የትም ወድቀው ቀርተዋል። ለጠቃሚ ልማት ይውል የነበረው፣ መጠኑ ከፍተኛ የሆነ የህዝቦቻችን ገንዘብና ንብረትም ባዶ ሜዳ ላይ ፈሶ ቀርቷል። ውጤቱም ፀፀትና ለቅሶ ብቻ ሆኖ ይገኛል። የዚህ ሁሉ መንስኤው፣ በየጊዜው ያመራሩን ስልጣን በኃይል የተቆጣጠሩ ኃይሎች ህዝብን ሳያማክሩ፣ በህዝብ ስም፣ የወሰዷቸው ስትራቴጂያዊ ህልውናችንን የሚጎዱ የተሳሳቱ የታክቲክ እርምጃዎች ናቸው። ሁላችንም ከዚህ ክፉ ልምድ ትምህርት ቀስመን ስህተቶቹን እንደገና እንዳንደግማቸው ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅብናል።

ለኤርትራ ተቃዋሚዎች ወገኖቻችን በአክብሮት የምናስተላልፍላቸው መልእክት ቢኖር፣ መለስ ዜናዊና ስብሓት ነጋ ከነግብረበላዎቻቸው ጋር ለኛ የፖለቲካ ተቀናቃኞቻችንና ተራ ጠላቶቻችን ብቻ ሳይሆኑ፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ለማጥፋት የተነሱ የሰይጣን መልእክተኞች ናቸው። ጠላቶቻችን ብቻ ቢሆኑ ኖሮ፣ የሃይማኖታችን ህግ እንደሚያዘው፣ «ጠላትህን ጭምር ውደድ» ስለሚለን፣ ይቅር ለመድኃኔዓለም ብለን ልንታረቃቸው ምንኛ በወደድን! ሆኖም፣ ሃይማኖታችን፣ «ሰይጣን ስለሚያጠፉህ ቀድመህ አስወግደው» በማለት ስለሚያዘን፣ ማሌሊቶቹም እርኩስ መንፈስን ተገን በማድረግ፣ እኛም ቅዱስ መንፈስን ተገን አድርገን ከመጠፋፋት በቀር ሌላ ምርጫ የለንም ብለን ተያይዘነዋል። ቅዱስ መንፈስና እርኩስ መንፈስ ተጋጥመው ማንኛቸው እንደሚያሸንፉ ደግሞ ከወገኖቻችን ሁሉ የተሰወረ አይደለም።

የማሌሊት መሪዎችን ሰይጣናዊነት ለኤርትራ ተቃዋሚዎች ማስረዳት የሚያስፈልገን አይመስለንም። የማሌሊት መሪዎች፣ በኢትዮጵያ የህዝብ ውክልና ሳይኖራቸው ከተፈጥሮ/ከባዮሎጂያዊ ወገናችን ከኤርትራ ህዝብ ጋር ያለያዩንና ያናከሱን ሰይጣኖች ናቸው። እኛን አምነው፣ ኢትዮጵያ አገራችን ናት ብለው ባገራቸው መሬት በሰላማዊ ኑሮ የተሰማሩትን፣ ነገር ግን ከሌሎች ኤርትራዊያን ፖለቲከኞች ጋር የራሳቸው ፖለቲካዊ አመለካከትና ልዩነት የነበራቸውን፣ እንደነ እህታችን ሳራ መኮንን፣ ወንድማችን ተስፋንክኤል ጆርጆና ሌሎችም ብዙ ኤርትራዊ–ኢትዮጵያዊያኖች ወገኖቻችችን፣ አንገታቸውን በካራ አርደው የገደሉ ሰይጣኖች የማሌሊት መሪዎች ናቸው።

በርካታ ያስተዳደር በደሎች ቢኖሩም፣ ከሌሎች ህዝቦች፣ በተለይ ከጭቁን ህዝቦች፣ ጋር ለዘመናት ተከባብሮ ይኖር የነበረውን የትግራይ ህዝብ ከሁሉም ኢትዮጵያዊ ጋር፣ የተቀረው ህዝብ

ደግሞ እርስ በርሱ እንዲባላ ያደረጉ የሰይጣን ቡችላዎች የማሌሊት መሪዎች እንደሆኑም ለኤርትራ ተቃዋሚ ወገኖቻችን መንገር የለብንም። አጼ ኃይለስላሴ፣ ኮሎኔል መንግሥቱ፣ አቶ ኢሳያስ ዴሞክራቶች ላይሆኑ ይችላሉ። ሆኖም ግን በዘርና በቋንቋ አተራምሰው እርስ በርሳችን አላተራመሱንም። ስለሆነም እየመከርንም እያለቀስንም የምንታገላቸው ሰዎች እንጂ እንደነ መለስ ዜናዊና ስብሓት ነጋ አጋንንት ናቸው ብለን አስበን አናውቅም። ሰው ሲሳሳት ለማረም ይቻል ይሆናል፤ ጋኔን ግን የአፈጣጠሩ ባህርይ ተሳስቶ ለማሳሳት ስለሆነ፣ ጋኔንን ማረም ስለማይቻል መፍትሄው ጋኔንን ታግሎ ጨርሶ ማስወገድ ነው።

የማሌሊት መሪዎች፣ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ህገ መንግሥታዊ መብት ሆኖ ሳይፀድቅ ለኤርትራ የፈቀዱ፣ ህገ መንግሥታዊ መብት ሆኖ ከተደነገገ በኋላ ደግሞ ከትግራይ በመለስ ላለው ሁሉ ከልክለው፣ በትግራይም ከነሱ በቀር ሌላ የትግራይ ሰው እንዳይንቀሳቀስ ያደረጉ አጋንንት ናቸው። የማሌሊት መሪዎች አገራችንን በቋንቋ ሸንሽነው፣ ምንም እንኳ አባቶቻችን ያደረሱት በደል ያለ ቢሆንም፣ ለዘመናት አብሮ በመከባበር የኖረውን ህዝባችን እርስ በርሱ እንዲናከስና እገረመንገዱም የትግራይን ህዝብ እንዲነክስ ሆኔታዎችን ሆን ብለው ያመቻቹ ርኩሰ–መናፍስት ናቸው። ባዲስ አበባ በመሃል አራዳ፣ በአዋሳ ከተማ፣ በኦሮሚያ፣ በኦጋዴንያ፣ በሃዲያ፣ ወዘተ. በጠራራ ፀሃይ ወገኖቻችንን ያረዱ አጋንንት የማሌሊት መሪዎች ናቸው። ለአብነት ያህል እነዚህን ጠቃቀስን እንጂ፣ የማሌሊት መሪዎች ሰይጣናዊ ተግባር ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም።

እንግዲህ የኤርትራ ተቃዋሚዎች በህዝባችን መሃል፣ ባገራችን ሃብት በኢትዮጵያ ምድር የምታደርጉት ያለው እንቅስቃሴ በሰይጣን የተደገፈ እንቅስቃሴ እንደሆነ ልናስታውሳችሁ እንወዳለን። ስለዚህ ግኑኝነቶች እንደተለመደው በታክቲካዊ ጥቅማጥቅሞች የተተበተቡ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ መደረግ ያለበት መሆኑን ለራሳችሁም ሆነ ለራሳችን ህልውና ስንል ልናስጠነቅቃችሁ እንወዳለን።

እኛን ከኤርትራ ተቃዋሚዎች የተለየ የሚያደርገን፣ እኛ ኤርትራን በቋንቋና በሃይማኖት ከሚያበጣብጥና የኤርትራን ህልውና ከሚፈታተን ኤርትራዊ ኃይል ጋር ምንም ዓይነት ሽርክና የሌለን መሆናችን ነው። በኤርትራ የውስጥ ጉዳይ ገብተን ለመዘባረቅ ሳይሆን፣ ለራሳችን ህልውናና ስትራቴጂያዊ ጥቅም ስንል፣ ኤርትራ ፍፁም ህዝባዊትና ዴሞክራሲያዊት አገር እንድትሆንልን እንፀልያለን። ዓላማው መጥፎም ይሁን በጎ በማያስጨንቅ፣ የኤርትራ ህዝብ በደሙና በንብረቱ ብዙ መስዋእትነት የከፈለ ህዝብ እንደመሆኑ መጠን፣ ለኤርትራ ህዝብ ዴሞክራሲ ቢያንሰው እንጂ አይበዛበትም ብለን ለኤርትራ መንግሥት በግልፅ ከማስታወስም አንቦዝንም። ስለሆነም የኤርትራ ተቃዋሚዎች ለመብታቸው ሲሉ የሚያደርጉት ተጋድሎ የምንደግፈው እንጂ የምንቃወመው እንዳልሆነ በሚገባ እንዲታወቅልን እንፈልጋለን።

የኛ ዋና ስጋት የኤርትራ ተቃዋሚዎች ከማሌሊት መሪዎች ጋር ተሻርከው የሚያስገኙት ትርፍ በኢትዮጵያ ህዝብ ኪሳራ እንዳይሆን ነው። የገቢዎችና የወጪዎች የሂሳብ መዝገብ በሚገባ ተይዞ፣ ትርፉ ሁለቱም ህዝቦች እኩል የሚከፋፈሉት መሆን ይኖርበታል። ሽሪኮች መልካም ትርፍ እንዲያገኙ ከፈለጉ ደግሞ በዝቅተኛ ወጪ ከፍተኛ ገቢ ለማግኘት ተደማምጠው መስራት ይጠበቅባቸዋል። ስለዚህ ታክቲኩ ሲንተከተክ ባንዱ ወገን አትራፊነት በሌላው ወገን ደግሞ ኪሳራና ውድቀት እንዳይጠናቀቅ፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች ጉዳይ ለማስፈፀም፣ በስልትም ሆነ በስትራቴጂያዊ ምክንያቶች፣ የምንወስዳቸው እርምጃዎች የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች እኩል የሚያተርፉበት መሆኑን አስቀድመን መገንዘብ ይኖርብናል እንላለን።

የኢትዮጵያ ህዝብና የኤርትራ ህዝቦች ከፊታቸው የተደቀነው አደጋ እጅግ ከፍተኛ ለመሆኑ የሚያነጋር አይደለም። ይህንን አደጋ ለማስወገድ ደግሞ፣ በጦር ሜዳ ከሚደረግ መጠፋፋት ይልቅ፣ በጠረጴዛ ዙሪያ በሚደረግ ቅን ውይይት ብቻ ቢሆን አላስፈላጊ ዋጋ እንደማያስከፍል ለመረዳት አያስቸግርም። የኤርትራ ተቃዋሚዎች፣ ከነ መለስ ዜናዊና ስብሓት ነጋ ጋር ሆነው፣ በኢትዮጵያና በኤርትራ ህዝብ መካከል ጠቃሚ ትስስር እንዲኖር መፈለጋቸው በመርሆ ደረጃ የሚደገፍና የሚደነቅም ነው። ይሁን እንጂ፣ ከማሌሊት ጋር የሚሰሩት የኤርትራ መንግሥት ተቃዋሚዎች እንዲያውቁልን የምንፈልጋቸው ሁለት ጉዳዮች አሉ።

ከሁሉ በፊት መታወቅ ያለበት የመለስ ዜናዊን መንግሥት ከሻዕቢያ ጉያ ለማውጣት ህዝባችን ከፍተኛ ዋጋ የከፈለ መሆኑን ነው። የዚህ ትግል ውጤት ህዝባችንና ሁሉም የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ሳይጠቀሙበት፣ የኤርትራ ተቃዋሚዎች ግን በኢትዮጵያ ምድር እንዲንፈላሰሱ መልካም አጋጣሚ አስገኝቶላቸዋል። ባሁኑ ጊዜ፣ ኢትዮጵያ ለኤርትራ ተቃዋሚዎች የምታፈሰው የህዝባችን ሃብት እጅግ ከፍተኛ እንደሆነም በመረጃ የሚታወቅ ጉዳይ ነው። ይህ በዚህ እንዳለ፣ የኤርትራ ተቃዋሚዎች ለተነፈጋቸው የዴሞክራሲ መብት በመታገላቸው ምንም የማያስጨንቀን

ሆኖ፣ መለስ ዜናዊና ግብረበላዎቹ የሚቆጣጠሩት ሌላ ስርዓት ባስመራ እንዳይመሰረት ግን አጥብቀን የምንከላከለውና የምንታገለው ለመሆኑ ከወዲሁ እንዲታወቅልን እንፈልጋለን።

ኤርትራ ለማሌሊት መሪዎች ደጀን መሆን ማለት፣ በኢትዮጵያ ለምናካሄደው የህልውና ትግል እጅግ አደገኛ መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ በሚገባ ይረዳል። ስለዚህ፣ ማሌሊቶችን ከሻዕቢያ ዋሻ ለማስወጣት የተደረገው ትንቅንቅ፣ እንደገና ከኤርትራ ተቃዋሚዎች ጋር በሚደረግ ግብግብ ተተክቶ ሌላ ችግርና መከራ እንዳይፈጠር የሚያስጨንቀን ብቻ ሳይሆን፣ አደጋ እንዳይደርስም አበክረን ስንማጠን መቆየታችንን የሚመለከታቸው ክፍሎች በቅንነት እንዲረዱልን እንወዳለን።

ሌላው ነጥባችን፣ በጉዳዩ ላይ ካለን ክትትልና የህይወት ተሞክሮ፣ ከታሪካችን አኳያም፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች፣ ከገቡበት ማጥ ሰጥመው እንዳይቀሩ፣ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የቀራቸው ብቸኛ ዕድል ቢኖር፣ ኢትዮጵያዊያንና ኤርትራዊያን አባቶች በዓለም ፊት ተስማምተው ያቆሙት፣ ነገር ግን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት፣ በራሳቸው ምክንያት፣ ያለ ኤርትራ ህዝብ ፍላጎትና ፈቃድ፣ ያፈረሱት ፌደራላዊ ትስስር፣ በበለጠ መንገድ ተጠናክሮና አብቦ፣ ማንም ሌላ ሰው ወይም ኃይል በኤርትራዊያን የውስጥ ጉዳይ ምንም ዓይነት ጣልቃ እንዳይገባ በህግ ተደንግጎ በዓለም ፊት ባዲስ መልክ እንዲታወቅ ማድረግ ብቻ መሆኑን ነው።

በዚህ መርሆ በኤርትራ ተቃዋሚዎች በኩል ያለውን ቅን አመለካከት በመረጃዎች በመደገፍ የምናውቀውን እናውቃለን። ይህንን ቅን አመለካከት የመላው የኤርትራ ተቃዋሚዎች አመለካከት ይሁን፣ ወይም በጓሮ በኩል ከነ መለስ ዜናዊና ከነ ስብሓት ነጋ ጋር በሚደረግ መመሳጠር የሚሸከረከር ይሁን አይሁን በማያስጨንቀን፣ በመሠረተ ሃሳቡ ላይ ግን  ምንም ዓይነት ልዩነት የለንም። ይህንኑ ሃሳብ በቅን ለሚያቀርቡልን ወገኖቻችን በቅንነት  እንደገለጽንላቸው ሁሉ፣ ለናንተም ደግመን በቅንነት ልንገልጽላችሁ የምንወደው ቢኖር ልዩነታችን በመርሆው ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በአፈጻጸም ላይ የተመሠረተ የታክቲክ ልዩነት መሆኑን ነው።

ማንም ሊመጻደቅበትና ሊያሰናክለው በማይቻለው፣ የኤርትራ ህዝብ ፍላጎት የሚወሰነው በራሱ በኤርትራ ህዝብና በኤርትራ ህዝብ ፍላጎት ብቻ እንደሆነ በትክክል እንገነዘባለን። የኢትዮጵያ ህዝብ የሚኖረው ተሳትፎ፣ በታሪክ፣ በፖለቲኮ-ኤኮኖሚ፣ በጂኦ-ፖለቲካና፣ በህግ ተመርኩዞ፣ የኤርትራ ህዝብ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ተፋቅሮና ተሳስሮ ሲኖር የሚያገኘውን ጥቅምና፣ ይህንን በማይሆንበት ግን የኤርትራ ህዝብ የሚደርስበትን ጉዳት በፉከራና በሽለላ ሳይሆን በጥንቃቄ፣ በትዕግስትና በቅንነት ማስረዳትና ምርጫው የተሳሳተ እንዳይሆን ማሳሰብ ብቻ ነው። ይህ ሁሉ ከተደረገ በኋላ  የኤርትራ ህዝብ ፍላጎት በጠመንጃ ኃይል በተገኘ ነፃነት ብቻ ይረጋገጣል የሚባል ከሆነ፣ በበኩላችን ይህንኑ በፀጋ ለመቀበል የሚገደን አይደለም።

ከማሌሊት መሪዎች ጋር ያለን ልዩነትም፣ በፕሮግራማቸው ከሰፈረው የኤርትራ ጥያቄ አፈራረጅ በተጨማሪ፣ ለኤርትራ ነፃነት መረጋገጥ ተካሄደ በተባለው ሬፈረንደም አፈጻጸም ያለን አሳማኝ ልዩነት ብቻ ነው። ግልጽ ለመሆን ያህል፣ የኤርትራ ሬፈረንደም የምንቃወመው ውጤቱን ሳይሆን፣ አፈጻጸሙ በምንም አግባብ ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ አይደለም የሚል መሆኑ ነው።

ያለፉት መከራዎቻችን ተመልሰው እንዳይመጡ የምንሰጋ ዜጎች ያለን የመፍትሄ አቋም በሁለት ምርጫዎች ላይ የተመሰረተ ነው። ሁለቱም ምርጫዎች ግን፣ የኤርትራ ህዝቦች፣ ከማንም ግለሰብ ወይም ኃይል ተፅእኖ ነፃ ሆነው፣ በዴሞክራሲያዊ አግባብ፣ በኢትዮጵያ ህዝቦችና በኤርትራ ህዝቦች የሚመረጡ ገለልተኛ ታዛቢዎች በሚገኙበት፣ የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው እንዲወስኑ ሙሉ ባለስልጣን መሆናቸውን በማርጋገጥ ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

አንዱ ምርጫ፣ በሁሉም የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች ተሳታፊነት እንደገና አዲስ ሬፈረንደም እንዲካሄድ በማድረግ የኤርትራ ህዝብ የተለያዩ ምርጫዎች ተሰጥተውት የወደደውን ምርጫ ሁሉም እንዲቀበል ማድረግ ነው።

ሁለተኛው ምርጫ ደግሞ፣ እንደገና ሬፌረንደም ማካሄድ አድካሚ ነው የሚባል ከሆነ፣ ሁሉንም በሚያረካ ሆኔታ፣ የኤርትራና የኢትዮጵያ ህዝቦች ጠንካራ ፌደራላዊ ትስስር እንዲኖራቸው በፈቃደኝነት እንዲስማሙ ማድረግ ነው።

እዚህ ላይ ትኩረት ሰጥተን ልንገነዘበው የሚገባን ቁምነገር አለ። ይኸውም እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ሁለት አማራጮች፣ ከሁሉም በላይ የሚጠይቁት ነገር ቢኖር፣ ዴሞክራሲን ነው። ከሁለቱ ምርጫዎች አንዱን መርጦ በተግባር ለመተርጎም ከተፈለገ ደግሞ፣ የማንም ሌላ ሰው ወይም ኃይል የጫካ  «ተሞክሮ» ወይም «እኔ አውቅልህአለሁ» ሳይሆን፣ ህዝቦች በህዝብነታቸው ማንም ሊነፍጋቸው በማይቻለው ዴሞክራሲያዊ መብታቸው ተጠቅመው የሚተረጉሙት ብቻ

መሆኑን የሚመለከታቸው ክፍሎች በሙሉ ጠንቅቀው ሊገነዘቡት ይገባል። በዚህ ዴሞክራሲያዊ ሂደት የኤርትራ ተቃዋሚዎችም ይስተናገዳሉ ማለት ነው።

አንዳንድ ኤርትራዊያን የሚነግሩን ካለ፣ «ሻዕቢያ በኃይል ኤርትራን ከተቆጣጠረ ዘንድ፣ የተካሄደው ሬፈረንደም ባይካሄድም ኖሮ ነፃነታችንን የሚነፍገን አልነበረም» የሚል ሊሆን ይችላል። ለዚህ መልሱ በጣም ቀላል ነው።

በመጀመሪያ፣ ጉዳዩ ይህ ከሆነ ታዲያ ለምን ሬፈረንደም አስፈለገ ብለን እንጠይቃለን። ከዚያ በበለጠ ደግሞ፣ በወቅቱ በኢትዮጵያ መንበረ መንግሥት መለስ ዜናዊ የተባለ፣ በትውልዱ ሳይሆን በተግባሩና በዓላማው ኤርትራዊ የሆነ የሰይጣን መልእከተኛና አሽከር ባይኖር ኖሮ፣ የተባበሩት መንግሥታትም ሆነ ሌሎች ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ኃይሎች ለኤርትራ እውቅና ለመስጠት ምንም ዓይነት መብት የላቸውም እንላለን። የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆች ወኔ ጭራሽ ተሰልቦ ጀግንነት ርቋችኋል የምንባል ከሆነም፣ ምናልባት፣ ግፋ ቢል፣ የኤርትራ ዕድል ከሰሜን ሶማሊያ ዕድል ምንም ያልተለየ ይሆን እንደነበር የሚያጠያይቅ አይሆንም። የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያቀርበው ያለው ክርክርም ይህ ነው።

ይህንን ለኤርትራዊያን ወገኖቻችን የምናስተላልፈው ልዩ መልእክት ለመቋጨት ያህል፣ እንደገና ደግመን ደጋግመን የምናሰምርበት ቁምነገር፣ ሌላ ሌላውን መስዋዕትነት ወደ ጎን ትተን፣ ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝቦች፣ በተለይ ደግሞ ተጠቂው የትግራይን ህዝብ ያስደነገጠውና ቀፎው እንደተነካ ንብ ያስቆጣው ነገር ካለ የመቀሌው የዓይደር ጭፍጨፋ መሆኑን በሚገባ ሊሰመርበት ይገባል። በሁሉም ዘንድ እንዲታወቅ የምንፈልገውም፣ ይህንን የዓይደር ሰማዕታት ደም ለሐገር ህልውና እንደተከፈለ መስዋዕትነት ተድርጎ እንዲቆጠርና ደሙ እንዲደርቅ ከተፈለገ፣ ደሙ የሚደርቀው የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦችን አንድ ላይ በሚጠምር ነጭ የሰላም ጨርቅ ብቻ ያሆናል። ይህንን ጥምረት ለማረጋገጥ ግን ሌላ ጦርነት፣ ሌላ ዘመቻ በማወጅ ተጨማሪ ዋጋ በመክፈል ሳይሆን፣ በሰከነ አዕምሮ በሚደረግ ውይይትና ምክክር ሊጠናቀቅ መሆን ይገባዋል።

ከነ ስብሓት ነጋና ከነ መለስ ዜናዊ ያለን ልዩነትም ይህ ነው። በነ መለስና በነ አቶ ህሩይ መካከል በሚደረግ መግባባት ወደ አስመራ መርሸን የምናረጋግጠው ፌደረሽን ዋጋው እንዲሁ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። አስራ አምስት ሚልዮን ህዝባችን በረሃብ እያለቀ፣ ሌሎች ሚልዮኖች በቀሳፊው የኤይድስ በሽታ እያለቁና ብዙ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ቀውሶች በኢትዮጵያ፣ በተመሳሳዩ፣ ምናልባትም በከፋ መልኩ፣ የኤርትራ ህዝብም ባሰቃቂ ሆኔታ በሚገኙበት ወቅት፣ ሌላ ታክቲክ፣ ሌላ ፍጥጫ መፍጠር በሁለቱም ህዝቦች ህልውና ላይ እንደመፍረድ የሚያስቆጥር ነው። ይህ እንዳይሆን የፈለገውን መስዋዕተነት ለመክፈል ዝግጁ ሆኖ ሃላፊነቱን መውሰድ የኛ የሁለቱም ህዝቦች ታጋይ ልጆች ግዴታና መብት መሆኑን በሚገባ መረዳት ይኖርብናል።

በኛ በኩል ይህንን ጉዳይ፣ ያለ ምንም ተጨማሪ ዋጋ ክፍያ፣ «ካሁን በፊት እነ አቶ መለስ ዜናዊን ለፌደራላዊ ውህደት ጠይቀን እምቢ አሉን» ከሚለው የሻዕቢያ መንግሥት ጋር የረባ ውይይት በማካሄድ ያለ ተጨማሪ መስዋዕትነት በሰላማዊ መንገድ ለማስፈጸም ሁሉንም የኢትዮጵያ ልጆች ግምባር ፈጥረው እንዲንቀሳቀሱ ጥሪያችንን በማስተላለፍ ላይ እንገኛለን። ውጤቱም ያማረና የሰመረ እንዲሆን፣ ሁሌም ብርታቱን የሰጠን አምላካችን እንዲረዳን፣ ራሳችን በመፀለይና፣ ፀሎታቸው ከኛ በላይ የሚደመጥ ያምላክ ወዳጆች የሆኑ ወገኖቻችንና የህዝቦቻችን ወዳጆች በየመስጊዱና በየቤተመቅደሱ እንዲፀልዩልን እያደርግን ነው። እኛ ሃሳብ ከማቅረብ ውጪ ሌላ ሚና የለንም። ይህ ሃሳባችን የሚጠቅም ከሆነና አምላክም ሚልዮን ክፋታችንና ሓጢአታችንን ይቅር ብሎ ፊቱን ወደኛ የሚያዞር ከሆነ ግን፣ እኛ ብናልፍም ልጆቻችን የዚህ ሃሳብ ተጠቃሚ እንደሚሆኑም ከአምላክ ጋር እምነታችን የፀና ነው። እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን!

ይህንን የመፍትሄ ሃሳብ ስናጠናቅቅ የነ አቶ መለስ/ስብሓት የፌደረሽን ዕቅድ ይዘው ለሚመጡ ቤተዘመዶቻችንና፣ ለኤርትራ ተቃዋሚዎች የምናስተላፈው መልእክት ቢኖር፣ የኛ ስልት ፌደረሽን ለማምጣት፣ የኤርትራን መንግሥት መገርሰስ አስፈላጊ አይደለም የሚል መሆኑ ነው። ስለዚህ ለዚህ ሲባል የሰው ህይወትና ንብረት ከሚጠፋ ይልቅ፣ ያለምንም ኪሳራ ጉዳዩ ሁለቱም ህዝቦች እንዲመክሩበት ዕድል በመስጠት በዚያ ሂደት በሁለቱም አገሮች ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለ ምንም ማወላወል እንዲረጋገጡ በማደርግ ሁሉም የሚስተናገድበት ሆኔታ ለመፍጠር ተደማምጠን መስራት ይኖርብናል በማለት እንሰናበታለን።

## ለኢትዮጵያ የተቃዋሚ ኃይሎች የምናስተላልው መልዕክት

ያለ ምንም ማጋነን፣ የኢትዮጵያ ህዝብ የመጨረሻ ዕጣ ፋንታ በተቃዋሚ ኃይሎች እጅ ይገኛል። ዛሬ ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ለመታደግ የሚሹ ኃይሎች ሁሉ ከመቼውም በላይ ሊገነዘቡት የሚገባቸው ሐቅ ቢኖር፣ ላንዴት ጊዜ ብቻ ህብረት ፈጥረው አገራቸውንና ህዝባቸውን ራሳቸውንም ከምፅአት ከማዳን ሌላ አማራጭ የሌላቸው መሆኑን ነው።

ከሁን በፊት የተለያዩ የተቃዋሚ ኃይሎች ህብረት ለመፍጠር ያደረጉት ጥረት የተሳካ ውጤት ባያስገኝም፣ ብዙ ትምህርትና ተሞክሮ በማስገኘት ረገድ የተጫወተው ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ከሁሉ በላይ፣ ከማሌሊት በተጨማሪ፣ እነማን ለስልጣን እንደሚራወጡ፣ እነማን ለምን እንደሚሰሩ፣ እነማን በተቃዋሚ ቼንብል ስውር ተልእኮ እንደሚያከናውኑ፣ እነማን አዲስ አበባ ሲመለሱ የህዝብ ፍርድ በመፍራት በውጭ አገር እየተሽሎከለኩ ተቃዋሚ እየመሰሉ በማጭበርበር በህዝብ ስም ገንዘብ እየመነተፉ እንደሚጠቀሙና፣ ባጠቃላይ በተቃዋሚነት ሽፋን እነማን በታኞችና አገር አጥፊዎች እንደሆኑ በሚገባ ለይተን ለማወቅ የቻልነው ለህብረት ግምባር ምስረታ በተደረጉ ጥረቶች አማካኝነት ብቻ ነው ማለት ይቻላል።

ባሁኑ ጊዜ፣ «የኢትዮጵያን የትግል መድረክ እኛ ካልተቆጣጠርነው፣ ኢትዮጵያ አፈር ትብላ» የሚሉት ትናንትናም ወደ ገደል የመሩንና ተያይዘን ገደል እንዳንገባ ከመንገዳችን ውጪ በመጓዝ በየመድረኩ የመከርናቸው፣ የለመናቸው፣ ያወያየናቸው ሰዎች ስለሆኑ ለኛ አዲስ ሰዎች አይደሉም። ሆኖም አገር የሚድነው ትናንት የተሰሩትን ስህተቶች በቪድዮ እየቀረፁ እየደጋገሙ በመመልከት ሳይሆን፣ ላገር ህልውና ሲባል፣ ያለፈው እንዳለፈ ለታሪክ ተትቶ ባዲስ መንፈስ፣ ባዲስ መላምት አብረን ከመስራት ሌላ አማራጭ የለም በሚል ሁሉን ወደኋላ ትተን ከሁሉም ጋር ተቃቅፈን ለመስራት ያላደረግነው ጥረት ያልከሰርነው ኪሳራ የለም። ውጤቱ የሚያመልክተው ግን፣ አሁንም ገና ከስህተታችን ባለመማር ጊዜው ባለፈበትና በየካቲቱ 66 አብዮት ማግስት ከተለማመድነው ጨዋታና ጋጋታ የተለየ ያለመሆኑ ነው። ይህንን ጨዋታና ጋጋታ በተመለከተ እንናገር ከተባለ ጊዜውና ቦታው ስለማይበቃን፣ ታሪክ ሁሉንም ነገር አብጠርጥሮ እስኪያወጣው ድረስ፣ ይህንኑ ብቻ ጠቆም አርገን ማለፍ እንሻለን።

የተቃዋሚዎች ህብረት እንዲመሰረት በተለያዩ ጊዚያቶች የተደረጉት ጥረቶችና መከራዎች፣ አንድ አሳሳቢ ችግር በተፈጠረ ወቅት ነው። ለአብነት ያህል «የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት፣ (ኢዴኃቅ)» ለመመስረት የተቻለው ወያኔ አዲስ አበባን ሊወር በተቃረበበት ዋዜማ ነበር። እንደዚሁም «የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሕብረት፣ (ኢተፖድሕ) የተመሰረው ደግሞ፣ ማሌሊትና ሻዕቢያ በተጋጩ ማግስት ነው። ያለ ምንም ድብቅብቅ ለመናገር ከተፈለገ፣ ሁለቱም የህብረት ስብስቦች የተጨናገፉት ለስልጣን መቆጣጠር በተደረጉ ሽኩቻዎች አማካኝነት እንደሆነ መካድ አይቻልም።

ህብረቶቹ የመሰረቱ ድርጅቶች መሪዎች ለስልጣን ሽኩቻ የተዳረጉበት ምክንያትም ባለፉት ዘመናት ካካሄዷቸው ትግሎች አኳያ አብዛኛዎቹ እርስ በርስ ሲጠቃቁ የነበሩ ስለሆነ፣ ወደ አገር ቤት ሲመለሱ ከተጠያቂነትና ከሃላፊነት የመነጨ ስጋት ያለባቸው ይመስላሉ። ስለሆነም አዲስ አበባ ሲደርሱ በሚኖራቸው ስልጣንና ኃይል ተጠቅመው ከተጠያቂነት ለመዳን የሚያደርጉት መከራ ሊሆን ይችላል ብሎ ለመናገር ያስችላል። ስለዚህ፣ በቅርቡ ይካሄዳል ብለን በጉጉት የምጠብቀውና ዝግጅቱ እየተጠናቀቀ ባለው «የፖለቲካ ድርጅቶች ጉባኤ»፣ ይህንን ፍርሃት ለመቅረፍና የግለሰቦችን ስጋት ለማስወገድ፣ ለወደፊቱ በኢትዮጵያ ሊኖር ስለሚገባው የብሄራዊ እርቀሰላም ጥያቄ አጀንዳ ተይዞለት ውይይት ሊደረግበት ይገባል።

አሁን ሊካሄድ የታሰበው የህብረት ጉባኤ ልዩ የሚያደርገው ብዙ ምክንያቶች አሉት። ከሁሉም በላይ ግን፣ ያሁኑ ዝግጅት አብዛኛዎቹ ጠንካራ ድርጅቶች የተሳተፉበት፣ በራሳቸው ምክንያት በትጋት ለጉባኤው ዝግጅት የሚጠበቅባቸውን አስተዋፅኦ ባያደርጉም ከዝግጅቱ ጀምሮ ሌሎች ወሳኝ ናቸው የሚባሉ ድርጅቶችም በዝግጅቱ እንዲሳተፉ ተደጋጋሚ ጥሪ የተደረገበት፣ በዝግጅቱ የተሳተፉት ድርጅቶች ሰፋ ያለ ጊዜ ወስደው የመከሩበት፣ ካለፉት የህብረት መከራዎች ጠንካራና ደካማ ከሚባሉት ልምዶች የተገመገሙበት መሆኑ ነው። ይህ በጎና ተስፋ ሰጪ ክንዋኔ ስለሆነ ሊደገፍና ሊታቀፍ የሚገባው ነው።

በዚህ ወሳኝ ጉባኤ ላይ በሁሉም የኢትዮጵያ የውስጥ ችግሮች ዙሪያ ጠቃሚ ውይይት እንደሚከናወን የሚጠበቅ ነው። በተለይ የብሄር/ብሄረ ሰቦች ችግርና አብይ ጥያቄ በቂ ትኩረት ተሰጥቶት፣ በማያዳግም መንገድ እልባት እንዲያገኝ ስለሚቻልበት መንገድ በጥሞና ውይይት ተደርጎ ግልፅ አቋም እንዲወሰድበት መደረግ ይኖርበታል።

ከዚህ በተጨማሪ ጉባኤው ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያና በኤርትራ ህዝብ ፊት ተደቅኖ ያለው አደጋ በማስወገድ፣ የሁለቱም አገሮች ህዝቦች በቀጣዩ ተፋቅረውና ተረዳድተው በትስስር እንዲኖሩ

ለማድረግ በሚያስችላቸው ረገድ ከሚመለከታቸው ሁሉ ውይይት መጀመር እንዲቻል፣ ጉዳዩ በአጀንዳ ተይዞ ሊመክርበትና የመፍትሄ ሃሳብ ሊቀርብለት ይገባል እንላለን።

ከዚህ በተጨማሪ ጉባኤው የፖለቲካ ድርጅቶች ጉባኤ መሆኑ ቢታወቅም፣ በዚህ ጉባኤ ከተቻለ ባጠቃላይ በጉባኤው ሂደት መድረኮች፣ ይህ የማያመች ከሆነ ደግሞ ቢያንስ በጉባኤው የመክፈቻ መድረክ ወሳኝና ታዋቂ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ግለሰቦች፣ የአገር ሽማግሌዎችና የሁሉም ሃይማኖቶች ተወካዮች ተገኝተው እንዲሳተፉበት ወይም ቡራኬያቸው እንዲሰጡበት ቢደረግ መልካም ገፅታ እንዳለው ለማስታወስ እንወዳለን።

የፖለቲካ ድርጅቶች ጉባኤ ለመጠራት ዝግጅቱ እየተጠናቀቀ ባለበት ባሁኑ ወቅት፣ ከሁሉም በላይ በጭንቀት ተወጥሮ ያለው፣ በተቃማሚ ኃይሎች ህብረት ብቻ ድራሹ የሚጠፋ መሆኑን በሚገባ የሚረዳው የማሌሊቱ በታኝና ሽፍታ መንግሥት ነው። ዛሬ ማሌሊቶች በራሳቸው ደጋፊዎች ሳይቀር በተተፉበት ዘመን፣ ራሳቸው ተናግረውና አግባብተው የሚያሳምኑት ኢትዮጵያዊ የሚባል ሰው እንደሌለለ የሚታወቅ ነው። ስለዚህ የተቀረጠቿው የማሌሊቶች ምላስ ተናግራ ልታሳምን ስለማትችል፣ ያቿ የተከታተፈችው የማሌሊት ምላስ ተክተው የሚያወሩና የሚያስወሩ ሌሎች ምላሶች በውድ ዋጋ ተገዝተው ተዘጋጅተዋል።

ይህንን ጉባኤ ለማሰናከል የሚፈልጉት ማሌሊቶች ብቻ ሳይሆኑ፣ መድረኩን እኛ ካልተቆጣጠርነው ህብረቱም ሆነ ኢትዮጵያ ገደል ይግቡ የሚሉ፣ ከነሱ በቀር ኢትዮጵያ ሰው የሌላት ወይም ከነሱ በቀር ለአገርና ለህዝብ የሚቆረቆር ሰው የሌለ የሚመስላቸው የተደራጁና ያልተደራጁ ግለሰቦች መኖራቸውም ሊታወቅ ይገባል። ይሁን እንጂ ጉባኤው እነዚህ ነቀዞች ከሚገምቱት በላይ በህዝባችን ዘንድ ከፍተኛ ትኩረት እያገኘ ዝግጅቱ እየተፋጠነ ነው። ህዝቡ ራሱ ሁላችንም በዓይነ ቁራኛ እየተከታተለ ጉባኤው በተያዘለት ቀነ ቀጠሮ ተካሆዶ ስራዎቹን አጠናቆ ወደ ተግባር እንደሚሰማራም እምነታችን የፀና ነው። በዚህ የህብረት ትግል ምስረታ ሂደት ከሚጠበቁት ጠቃሚ ውጤቶች መካከል አንዱ፣ ተቃዋሚ ነን ከሚሉት መሃል ባሁኑ ጊዜ ማን ለአገርና ለህዝብ እንደቆመ፣ ማን ደግሞ ትግሉን በማደናቀፍ የማሌሊቶቹን ዕድሜና የኢትዮጵያ ህዝቦች የሰቆቃ ህይወት እንደሚያራዝም ኮለል ብሎ ለህዝብ ግልፅ የሚሆን መሆኑ ነው።

ይህንን ክፍል ከመቋጨታችን በፊት የምናስተላልፈው ተጨማሪ መልእክት ካለ፣ በተለያዩ የራሳቸው ምክንያቶች እስካሁን በጉባኤው ዝግጅት ያልተሳተፉ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ አሁንም በጉባኤው ለመገኘት ካዘጋጁ ኮሚቴ ጋር ተገናኝተው በጉባኤው እንዲሳተፉ፣ በተለያየ መንገድ መልእክታችንን እንዳስተላለፍንላቸው ሁሉ፣ በዚህ አጋጣሚም ደግመን እናስታውሳቸዋለን።

**ሰላምና ብልጽግና ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ህዝቦች!**
**ድል ለተባበረ የህዝብ ትግል!**

---

1 ኮሎኔል ታደሰ ሙሉነህን በተመለከተ ከጥቂት ቀናት በኋላ ራሱን የቻለ መጣጥፍ ይዤ እንደምቀርብ ለመጠቆም እወዳለሁ።

2 ቃለመጠይቁ እንዳለ በመጋቢት ወር 1995 ዓ.ም. ቅፅ 4 ቁጥር 045 በወጣው የ«ኢትዮጵ» ጋዜጣ ታትሞ ስለወጣ ከዚያው መመልከት ይቻላል።

3 ካሁን በፊት በኢትኦጵ መጽሄትና በሐዋርያ ጋዜጣ ታትመው የወጡት «የኤርትራ ፋይል ሲከፈት» እና «አስቸኳይ ማስጠንቀቂያ» የተሰኙ የኔ ጽሁፎች ይመልከቱ።

4 የብስራት አማረን የስለላ ስራዎች በተመለከተ ካሁን በፊት በማሌሊት የስለላ ስራ «የማዘናጊያ መረጃ» (disinformation) እንዴት እንደሚሰራ በቅርቡ አቀርበዋለሁ ባልኩት መጣጣፍ ላይ ይካተታል።

5 ባለፈው ጦርነት የኤርትራ ታጋዮች መካነ መቃብር በዘመተው የኢህአዴግ ሰራዊት መፈራረሱ ይታወቃል። ይህንን ያደረጉ ወገኖች እነማን እንደሆኑና፣ እነዚህ ወገኖች ይህንን በማድረግ ምን ለማከናወን እንደፈልጉ ለወደፊቱ እጽፍበታለሁ።

6 ስብሓት ነጋ የተባለ የስጋ ዘመዴ፣ ብስራት አማረ በተባለ ሌላ የስጋ ዘመዴ በመጠቀም አርጋዊ በርሄን እንዴት እንዳጠቃውና ታንድን ለማዳከም እንደሞከረ እኔ ራሴ ብዙ ተጉዤና ተከታትየ የደረስኩበትን ለወደፊቱ አስነብባለሁ።

7 ስለ «ኢአአነን» ምንነት ሌላ ጊዜ ይቀርባል።

8 አቶ በላይ አባይ ያርበኛው የክቡር ደጃዝማች አባይ ካሳ ልጅ ናቸው። የአቶ በላይ አባይ እህት፣ የመለስ ሰራተኛ የሆነው የዶክተር አሰፋ አብርሃ እናት ግን፣ ያቶ በላይ አባይ ግማሽ እህት እንጂ፣ የክቡር ደጃች አባይ ካሳ ልጅ አይደሉም። ይህን ለመግለጽ የተገደድኩት፣ «ተራራ ያንቀጠቀጠ ትውልድ» በሚባል መጽሓፍ

ውስጥ ማሌሊቶች የክቡር ደጃች አባይ ካሳን ታሪክ በውሸት ለማጉደፍ የጻፉትን ለማጋለጥ ስል በሌሎች ስራዎቼ ላይ፣ ክቡር ደጃች አባይ ካሳ፣ ከነ መለስ ጋር ወግነው ኢትዮጵያን በመሸራረፉ ተግባር የተሳተፉ ልጆች የሌላቸው መሆኑን ስለመዘገብኩ፣ ከዚሁ ጋር የሃሳብ ግጭት እንዳይኖር ለማድረግ ነው።

[9] ካሁን በፊት ባገር ቤት በ«ኢትኦጵ» መፅሔት፣ በውጭ አገር ደግሞ በ«ሐዋርያ» ጋዜጣ በተከታታይ የወጣው «የኤርትራ ፋይል ሲከፈት» በሚል ርእስ የቀረበውን የዚህ ጸሃፊ ስራዎች ይመልከቱ።

[10] ከላይ በተ/ቁ. 9 እንደተመለከተው።